ፍኖተ ስብከት
የስብከት መንገድ

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ከዓመት እስከ ዓመት በሚከበሩ በዓላት ታሪክ ላይ የተመሠረተ ትምህርታዊ ስብከት

አዘጋጅ፦ መ/ር አዲሱ ላቀው
በቅድስት ሥላሴ መንፈሳዊ ዩኒቨርሲቲ
ከሊጅ B.Th
በምስራቅ ሸዋ ሀ/ስብከት ም/የስብከተ ወንጌል
ክፍል ኃላፊና የናዝሬት ደብረሰላም ቅዱስ
ገብርኤል ካቴድራል ቤ/ክ የስብከተ ወንጌል
ክፍል ኃላፊ


- የመጀመሪያ እትም 2004
- ሁለተኛ 2005

© መብቱ በሕግ የተጠበቀ ነው

ዲን አዲሱ ላቀው
ታኅሣሥ 2005 ዓ.ም
አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ

የአዘጋጁ አድራሻ
✆ +251-911-659752
E-mail: Addissu 03@yahoo.Com

የመጽሐፉ ከሽር ዲዛይን
በወ/ሮ ሕሊና ተዘራ





ምስጋና

‹‹ሳትደክም ሁልን ትሸከማለህ
ሳታንድል ልሁሉ ትመግባለህ፣
ሳትነጥፍ ለዘሁሉ ታደርጋለህ፣
ሳትዘነጋ ሁልን ታስባለህ፣
ሳትተኛ ሁልን ትጠብቃለህ፣
ኸል ሳትል ሁልን ትሰማለህ፣
ሳትቀደል ልሁሉ ትተዋለህ።።።
(ቅዳሴ የፅጌሬ ወልደ ነገደጽድ)
ከብር እና ምስጋና ለእንተ ይደኃ።

ጊዜያቸውን በመስጠት የተባበራቸሁኝ፣

- መጋቢ ሐዲስ ይልማ ቸርነት፣ መጋቢ ምሥጢር ገብረ ሕይወት ፋንታሁን እና መ/ር ጋሻው ዘመነ እግዚአብሔር ጸጋችሁን ያብዛላችሁ።

- ለሃይማኖት ቤተሰቦቼ በሙሉ መልአከ ሕይወት አባ ገብረ ሕይወት በቀለ፣ መ/ር ዳዊት ጥበቡ፣ መ/ር ዘኪኤያስ ወ/ሚካኤል፣ መ/ር ጸጋዬ መኮነን፣ ቀሲስ ሰይፉ ውሂብ፣ እግዚአብሔር ይጠብቅልኝ።
- አቶ ያለው ውዴንና ቤተሰቦቹን ወ/ሮ ይካኑ አይቸውና ቤተሰቦቿን ወ/ሮ እታፈራሁ በተሳና ቤተሰቦቿን ከልብ የሆነ ምስጋዬን እያቀረብኩ እግዚአብሔር ኑሮአቸሁን ይባርክ።

ስጦታ

ከ _____

ለ _____

ቀን _____

መግቢያ

"የእግዚአብሔር በዓላት በየዘመናቸው የምታውጇቸው የተቀደሱ ጉባኤ ናቸው"። (ዘሌ.23+4)

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ሰማያዊውን አደንዛ ማዕከል ያደረገ፣ በጥቂቱ የደከመውን ትውልድ፣ ልብ የሚሰርፍ ዘመን ተሻጋሪና ማራኪ ሥርዓተ አምልኮ ያላት ጥንታዊትና ሐዋርያዊት ቤተክርስቲያን ናት።

አምልኮን በታልና በተግባር የምታሳየን እናት ቤተክርስቲያናችን የውስጥ ውብቷን የሚገልጹላት ልጆች ትፈልጋለችና እኔም የድርሻየን ለመወጣት ብፅፈን አነሣሁ።

ከሥርዓተ አምልኮዋ አንዱ የሆነው የበዓላትን አከባበር መጽሐፍ ቅዱሳዊ ይዘቱን በማስጠበቅ ለአገልጋዮች፣ ለሰንበት ትምህርት ቤት ወጣቶችና ለምዕመናን መማሪያና ማስተማሪያነት ያለሚል ዘንድ ፍኖተ ስብከት በሚል ርእስ ይህንን መጽሐፍ አዘጋጅቻለሁ። ቅድስት ቤተክርስቲያናችን በምታከብራቸው ዓመታዊ ክብረ በዓላት ታሪክ ላይ የተመሠረተ ትምህርትና ሥልእክት በዐሥራ ሦስት ንዑሳን ክፍሎች ከፋፍዬ በማዘጋጀት ለአንባብያን አበርክቻለሁ።

"ቀንን የሚያከብር ለጌታ ብሎ ያከብራል"

(ሮሜ.14+6)

ከአዘጋጁ

ማውጫ

ገጽ

ክፍል አንድ

መስከረም

አንድ፡ ዘመኑን እየዋጃችሁ በጥበብ ተመላለሱ 12
ሁለት፡ ለአንተ ልትሆን አልተፈቀደም..... 16
ዐሥራ ሰባት፡ የመስቀል እንቅፋት ተወግዷል..... 20
ሃያ አንድ፡ ትውልድ ሁሉ ብፅዕት ይሉኛል..... 25
ሃያ ዘጠኝ፡ ሴቶችም አስከሞት ድረስ ተደበደቡ.....25

ክፍል ሁለት

ጥቅምት

አምስት፡ የጸድቃን መታሰቢያ ለዘላለም ይኖራል.....27
ዐሥራ አራት፡ ከመከሰላቸው ውጡና የተለያችሁ ሁኑ..... ..27
ዐሥራ ሰባት፡ ሰማይ ተከፍቶ የእግዚአብሔርን ክብር አየ...30
ሃያ ሰባት፡ በአርሱም ተከል እኛ ተፈወስን 30

ክፍል ሦስት

ኅዳር

ስድስት፡ የሕፃኑን ነፍስ የሚፈልገው ሞቷልና....................31
ሰባት፡ እግዚአብሔር በቅዱሳኑ ላይ ድንቅ ነው....................32
አሥራ ሁለት፡ የማይረሳ ሌሊት....................34
ሃያ አንድ፡ ኢካቦድ 37
ሃያ አምስት፡ ከክርስቶስ ፍቅር ማን ይለየናል?....................39

ክፍል አራት

ታኅሣሥ

አንድ፡ እንደ እግዚአብሔርም ቃል አደረገ 42
ሦስት፡ ስለቴን ይዤ ወደ ቤትህ እገባለሁ....................45
አሥራ ዘጠኝ፡ ከእጁስ የሚያድናችሁ ማነው?....................47
ሃያ ሁለት፡ እንደ ቃልህ ይሁንልኝ....................50
ሃያ አራት፡ የቅናት ትውልድ ትባረካለች.................... 53
ሃያ ስምንት እና ሃያ ዘጠኝ፡ ዛሬ በዳዊት ከተማ መድኃኒት ተወልዶላችኋል 55

ክፍል አምስት

ጥር

አንድ፡ ይህንን ኃጢአት አትቁጠርባቸው....... 60
ስድስት፡ የማይመረመር አምላክ በሥጋ ተገለጠ 62
ሰባት፡ ባቢሎን 63
ዐሥራ አንድ፡ ጽድቅን ሁሉ መፈጸም ይገባናል....................65
ዐሥራ ሁለት፡ መልካሙን የወይን ጠጅ ለምን አዘገያችሁት? 67
ዐሥራ ስምንት፡ ዘወትር ለሞት ተላልፈን እንሰጣለን....................70
ሃያ አንድ፡ ከእንግዲህ ወዲህ በጌታ የሚሞቱ ብፁዓን ናቸው ሥራቸውም ይከተላቸዋል....................72

ክፍል ስድስት

የካቲት

ስምንት፡ ዓይኖቼ ማዳንህን አይተዋል 74
ዐሥራ ስድስት፡ ከመረጥኳቸው ጋር ቃል ኪዳኔን አደረኩ....................77

ክፍል ሰባት

መጋቢት

አምስት፡ የጻድቃን ሞት እኔ ልሙት ፍጻሜዬም እንደነ እርሱ ትሁን 79

ሆሳዕና፡ ፈትታችሁ አምጡልኝ 82
ሰሙነ ሕማማት፡ 85
ጸሎተ ሐሙስ፡....................86
ስቅለት፡ አንዱ ስለሁሉ ሞተ....................88
ትንሣኤ፡ እንደተናገረ ተነሥቷል 91

ክፍል ስምንት

ሚያዝያ

ሃያ ሦስት፡ እስከ ሞት ድረስ የታመንህ ሁን 94

ክፍል ዘጠኝ

ግንቦት

አንድ፡ ከሊባኖስ የሚፈስ ወንዝ ነሽ 96
ዕርገት፡ እያዩት ወደ ሰማይ ዐረገ 98
ዐሥራ አንድ፡ ለጌታ በልባችሁ ተቀኙና ዘምሩ 101
ዐሥራ ሁለት፡ እግዚአብሔር የጻድቃንን አጥንቶቻቸውን ሁሉ ይጠብቃል 103
ጰራቅሊጦስ፡ በባሪያዎቼ ላይ መንፈሴን አፈስሳለሁ....................104
ሃያ አንድ፡ ጌታ ካንቺ ጋር ነው 105

ክፍል ዐሥር

ሰኔ

ዐሥራ ሁለት፡ መላእክቱን ስለአንተ ያዝዛቸዋልና....................107
ዐሥራ ሰባት፡ እምነት ቢኖራችሁ ይህንን ተራራ ወደዚያ እለፍ ብትሉት ያልፋል 111
ሃያ እና ሃያ አንድ፡ መቅደሱን በአርያም አነፀ 113
ሠላሳ፡ አንተ ሕፃን ሆይ የልዑል ነቢይ ትባላለህ....................115

ክፍል ዐሥራ አንድ

ሐምሌ

አምስት፡ ስለ አንተ ቀኑን ሁሉ እንገደላለን 116
ሰባት፡ በፊትህ ሞገስ አግኝቼ እንደ ሆነ ባሪያህን አትለፈኝ?....................126
ዐሥራ ዘጠኝ፡ በእሳትና በውኃ መካከል አለፍን....................129

ክፍል ዐሥራ ሁለት

ነሐሴ

ሰባት፡ አንቺ ከሴቶች መካከል ተለይተሽ የተባረክሽ ነሽ....................131
አሥራ ሦስት፡ በዚህ መሆን ለኛ መልካም ነው 134
አሥራ ስድስት፡ አቤቱ ወደ ዕረፍትህ ተነሥ አንተና የመቅደስህ ታቦት 137
ሃያ አራት፡ የጻድቅ መታሰቢያ ለበረከት ነው 141

ክፍል ዐሥራ ሦስት

ጳጉሜን

ሦስት፡ መልአኬን በፊትህ እልካለሁ፡....................143

መስከረም አንድ

ርእሰ ዐውደ ዓመት

የዕለቱ የትምህርት ርእስ

"ዘመኑን እየዋጃችሁ በጥበብ ተመላለሱ" (ቆላ 4፥5)

ዓመታትንና ዘመናትን የሚያመላልስ፣ የሚያመጣ የሰከንድ፣ የደቂቃ፣ የሠዓታት፣ የዕለታት፣ የሳምንታት፣ የወራት፣ የዓመታትና የዘመናት ባለቤት እግዚአብሔር ሲሆን ይህ ዓለም ከመፍጠሩ በፊት የነበረ ዓለምን ፈጥሮ በፍቅር የሚገዛ ዓለምንም አሳልፎ የሚረር በማንም በምንም እንደ ዘመናት የማይፈራረቅና የማይለወጥ የማይቀየርም እርሱ እግዚአብሔር ብቻ ነው።

"አንተሰ አንተ ክመ ወዓመቲከኒ ዘኢየኃልቅ።"

"አንተ ግን ለዘላለም ያው ነህ የአድማህም ዘመን ወሰን ማከቂያ የለውም" (መዝ 102፥27)

ከአባታችን አዳም ጀምሮ ብዙ ትውልድ በዚህች ምድር ላይ ተመላልሷል። ወጥቷል ወርዷል አልፏል። ዘመን ሲያልፍ ዘመን ሲተካ ሰው ሲያልፍ ሰው ሲተካ ዛሬ ላይ ደርሰናል። ነቢየ እግዚአብሔር ቅዱስ ዳዊት በመዝሙሩ «ሰውስ ዘመኑ እንደ ሣር ነው እንደ ዱር አበባ እንዲሁ ያብባል። ነፋስ በነፈሰበት ጊዜ ያልፋል» (መዝ. 102፥15፡16)።

ይህም ቃል በአዳም ልጆች ሁሉ ላይ ሲሠራ ኖሮ ከአሁኑ ትውልድ ደርሷል። ቀሚ የቀየ የሚመስለው የአሁኑ ዘመን ትውልድ ግን ሊያስተውለው የሚገባ አንድ ዐቢይ ቁም ነገር አለ። ይኸውም ከእርሱ

በፊት የነበረው ትውልድ በታወን ለአሁኑ እንደለቀቀ ሁሉ ይኸኛውም ትውልድ በበኩሉ አላፊ /የሚያልፍ/ መሆኑ አይቀሬ ነው።

ትምህርት

- በሥጋ ፈቃድ የኖርንበትና የተመላለስንበት ዘመን ይበቃናል።

« እስምሩ ከመ በጽሐ ጊዜሁ ለንቂህ እምንዋም» «ከእንቅልፍ የምትነሡበት ሠዓት አሁን እንደደረሰ ዘመኑን እወቁ ካመንበት ጊዜ ይልቅ መዳናችን ዛሬ ወደኛ ቀርቦአል እንግዲህ የጨለማውን ሥራ አውጥተን የብርሃንን ጋሻ ጦር እንልበስ በቀን እንደምንሆን በአገባብ እንመላለስ።» (ሮሜ 13፥11)

- እግዚአብሔርን ባለመፍራትና ባለማወቅ የተመላለስንበት ዘመን ይበቃናል።

የአሕዛብን ፈቃድ ያደረጋችሁበት በመዳራት በሥጋ ምኞትም፣ በስካርም፣ በዘፈንም፣ ያለልክ በመጠጣት ነውርም ባለበት በጣዖት ማምለክ የተመላለሳችሁበት ያለፈው ዘመን ይበቃልና። (1ጴጥ.4፥3፤ዘፍ.19፥20፤ ገላ.5፥16፤ፊል.3፥13)።

- በዘፈንና በስካር የተመላለስንበት ዘመን ይበቃናል።

የሚሰክሩም በሌሊት ይሰክራሉ እኛ ግን ከቀን ስለሆንም የእምነትንና የፍቅርን ጥሩር የመዳንንም ተስፋ እንደ ራስ ቍር እየለበስን በመጠን እንኑር 1ተሰ 5፥7

- በዝሙትና በመዳራት የተመላለስንበት ዘመን ይበቃናል። (ሮሜ 13፥12-15)
- በክርክርና በቅናት የተመላለስንበት ዘመን ይበቃናል። (ሮሜ13፥14)
- ኃጢአታችን ይደመሰስ ዘንድ ንስሓ በመግባት ዘመኑን መዋጀት። (የሐዋ 3፥20)

አሁንስ ይላል እግዚአብሔር በፍጹም ልባችሁ በጾምም በለቅሶ በዋይታ ወደኔ ተመለሱ ልባችሁን እንጂ ልብሳችሁን አትቅደዱ (ት.ኢዩ 2፥12)

- በፍቅርና በሰላም ከሁሉም ሰው ጋር እየኖርን ዘመኑን መዋጀት

በሰዎችና በመላእክት ልሳን ብናገር ፍቅር ከሌለኝ ግን እንደሚጮኽ ናስ ወይም እንደሚንሽዋሽዋ ጸናጽል ሆኛለሁ (1ቆሮ.13፥1-13) ቢቻላችሁስ ከሰው ሁሉ ጋር በሰላም ኑሩ (ሮሜ.12፥18)

መልእክት

የዓመታትና የዘመናት ባለቤት ልዑለ ባሕርይ እግዚአብሔር ዘመናትን እያፈራረቀና እኛን እየጠበቀ ሌላው ዓመት ሲተካ አይተናል። በሥጋ ፈቃድ የተመላለስንበት ዘመን ይበቃናል። በጥበብና በማስተዋል ዘመኑን እየዋጀን እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ መመላለስ ይገባናል። እግዚአብሔርን ባለመፍራት ሕጉና ሥርዓቱን ባለመጠበቅ በሥጋ ሥራ በዘፈን፣ በሥካር፣ በዝሙት፣ በመዳራት፣በክርክርና፣ በቅናት፣ ርእስ በርእስ በመጠላላት የተመላለስንበት ዘመን ሊያከትም ይገባዋል።

አዲሱ ዓመት ከሀሰት ወደ እውነት ከጥላቻ ወደ ፍጹም ፍቅር ከክፋት፣ ከተንኰል ከምቀኝነት ከዘረኝነት ተላቀን መጪውን ዘመን ስንቀበል ያለፈው ማንነታችን መቀየር አለበት። ባለፈው ዓመት ሕግ እንደ ሌላቸው አሕዛብ ያለ ሕግ የተመላለስንበት ያ የኃጢአት ሕይወት ዛሬ በንስሓ ተወግዶ በፍጹም ተሰውጦ አዲስ ሰው የምንሆንበት ጊዜ ነው። ብዙ የምሕረት ዓመት አስቆጥረናል እኛም በግላችን በዚህ ምድር ላይ ብዙ የምሕረት ዓመታትን አሳልፈናል። በእውነት ግን ካሳለፍናቸው የምሕረት ዓመታት በስንቶቹ ተምረንባቸው ይሆን? በምሕረት ዓመታት የብርሃንን /የጽድቅን/ ሥራ ትተን የጨለማን /የኃጢአትን/ ሥራ ብቻ ሥንሠራ አሳልፈን ከሆነ ግን በአዲሱ ዓመት ይህንን ትተን ወደ እግዚአብሔር የምንቀርብበት የምሕረት ዓመት ሊሆን ይገባዋል።

ላያችን ርግበ ውስጣችን እባብ የነበረበት፣ በሰው ፊት ጻድቅ በእግዚአብሔር ፊት ግን ኃጥእ የሆንበት፣ ሃይማኖታችንን በገንዘብ የለወጥንበት፣ በማንኛውም መንገድ እግዚአብሔርን ያስከፋንበት ያ ያለፈው ዘመን አክትሞ መጪው ጊዜ አዲስ ሰው የምንሆንበት ሊሆን ይገባል። ቀናትን ሳምንታትን፣ ወራትን፣ ዓመታትንና ዘመን መቀየር ብቻ

ሳይሆን መጀመሪያ መለወጥና መቀየር ያለበት የእኛ ልብ ነው። በየዓመቱ አዲስ ዓመት እየቀየርን መኖር ብቻ ሳይሆን አዲስ ዓመት ወይም መጪው ዘመን የተጣላነን የምንታረቅበት፣ ከተለያዩ ሱስና ከዓለም ሽኩም የምንላቀቅበት ጊዜ ሊሆን ይገባል።

በኃጢአት ያደፈው ማንነታችን በንስሐ ተቀይሮ ቅዱስ ሥጋውንና ክቡር ደሙን ያልተቀበልን የምንቀበልበት የሰሙ ቀዳሽ፣ የመንግሥቱ ወራሽ ለመሆን እንድንበቃ አዲስ ሰው ለመሆን ያለፈው ዘመን ክፉ ሥራን መተው ነው። በምትኩም ለመልካም ሥራ መትጋት የመንፈስ ፍሬ ማፍራት ነው። «የመንፈስን ፍሬ ፍቅር፣ ደስታ፣ ሰላም፣ ትዕግሥት፣ ቸርነት፣ በጎነት፣ የውኃት፣ ራስን መግዛት ነው።» (ገላ.5፥22)።

እነሆ የመዳን ቀን አሁን ነው እና ኃጢአታችን በንስሓ ውኃ የምንታጠብበት፣ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በቀራንዮ በቀረሰልን ሥጋው ባፈሰሰልን ደሙ የምንታተምበት፣ ኃጢአተኛ የነበረውን ሰውነታችንን ለእግዚአብሔር ሕግ የምናስገዛበት የምሕረት ዓመት እንዲሆን እራሳችንን እንቀድስ በአዲስ ዓመት አዲስ ሰው እንሁን።

በአዲስ ዓመት አዲስ ሰው መሆንን ከፈለግንና ለማረጋገጥም ካሻን ትላንት በአንደበታችን ሰዎችን ክፉ በመናገር ያስቀየምን፣ የሰረቅን፣ የዋሸን፣ የገደልን፣ የሰው ንብረት ያለ አግባብ የወሰድን፣ በሀሜትና በዝሙት ኃጢአት የወደቅን፣ የሚሰርቅ፣ የጥልና የክርክር መንፈስ ያሰብን ወዘተ ሰዎች ሁሉ ራሳችንን ከሚጎዳ በስተቀር ምንም የማይጠቅመን መሆኑን ተገንዝበን ንስሐ ልንገባ ከእግዚአብሔር ጋር ልንታረቅ ይገባናል። ለዚህም የሰላም የፍቅር የምሕረት አምላክ እግዚአብሔር ይርዳን። አሜን።

የቅዳሴ ምንባብ

- ዋናው ዲያቆን 2 ቆሮ 6፥1-11
- ንፍቅ ያዕ 5፥8-13
- ካህን የሐዋ 5፥12-17

ምስባክ ፦ ወትባርክ አክሊለ ዓመተ ምሀረትከ
ወይጸግቡ ጠላተ ገዳም
ወይረውዩ አድባረ በድዉ
(መዝ .46+11)

ወንጌል ማቴ 11+ 1-20

(ቅዳሴ ዘሐዋርያት)

መስከረም ሁለት

ምትረተ ርእሱ ለቅዱስ ዮሐንስ

የዕለቱ የትምህርት ርእስ
«ለአንተ ልትሆን አልተፈቀደም»
(ማር.6+18)

የፍጥረታት ሁሉ ጌታና ንጉሥ የሆነው ኢየሱስ ክርስቶስ እኛን ለማዳን ወደዚህ ዓለም ከመምጣቱ በፊት መንገዱን ይጠርጉ ዘንድ ብዙ ነቢያትን አስቀድሞ ልኳል። መጥምቁ ዮሐንስም በበረሐ ተገድዶ ሳይሆን የጌታ ፍቅር እያቃጠለውና እየመሰከረ፣ እየጮኸ መልእክተኛ ሆኖ መጣ። <<እነሆ፥ መንገድህን የሚጠርግ መልእክተኛዬን በፊትህ እልካለሁ የጌታን መንገድ አዘጋጁ ጥርጊያውንም አቅኑ እያለ በምድረ በዳ የሚጮኽ ሰው ድምጽ ተብሎ በነቢዩ በኢሳይያስ እንደ ተጻፈ>> (ኢሳ.40፡3፣ማር.1፡2-3)።

ሚልክያስ "የጌታ መልእክተኛ" ብሎ የጠራው ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለድኅነተ ዓለም ከመምጣቱ በፊት ሕዝቡን በንስሐ መንገድ እየጠረገ ስለነበር ነው። (ሚል.3፡1)። ከዚህም በተጨማሪ ጌታን ለመጀመርያ ጊዜ ያየው በሥጋ ማርያም ሳይሆን በእምነት ነበረ። ምንም እንኳን በእናቱ ማሕፀን ውስጥ የነበረ ቢሆንም ጌታውን በእምነት ሲመለከተው ግን በደስታ ዘሏል /ሉቃ.1፡44/።

ጠርጠሉስ የተባለ የሁለተኛው ክፍለ ዘመን ምሁር እንደተናገረው መዝሙረኛው ዳዊት <<ለቀባሁትም ሰው መብራትን አዘጋጃለሁ»እንዳለ <<መጥምቁ ዮሐንስ መልእክተኛ ብቻ ሳይሆን መብራትም ነበረ» ብሏል። በእርግጥም መስማትን ለሰሙት ወገኖች ሻማ ነበረ።

ኢሳይያስም ዮሐንስን ‹በምድረ በዳ የሚጮህ ድምጽ› ብሎታል። እርሱ አዳኙን ክርስቶስን ለመግለጥ እንደ ተላከ የምሕረት መልአክ፣ እንደ አንበሳ በበረሐ እየጮኸ በኃጢአት የጠነከረውን ልባችንን ይሰብር ዘንድ የመጣ መልእክተኛ ነውና። ሰውነታችን መልእክተኛ ለሆነለት ለእግዚአብሔር በግ ለክርስቶስ ማኅደር እንድንሆን ያዘጋጅ ዘንድ የመጣ ነቢይ ነውና።

«ዓምደ ተዋሕዶ» የተባለው ታላቁ ሊቅ ቅዱስ ቄርሎስ መጥምቁ ዮሐንስን ‹ከንጋቱ ኮከብ በፊት የነበረ ፀሐይ› ብሎታል። ምክንያቱም ዮሐንስ ፀሐየ ጽድቅ ኢየሱስ ክርስቶስ እስኪመጣ ድረስ የሚያበራ ፋና ነበረና። በጨለማ ውስጥ ይመላለሱ ለነበሩት ሁሉ ወደ እውነተኛው ብርሃን ይደርሱ ዘንድ ያዘጋጅ ነበረና።

ዮሐንስ ያዘጋጀ የነበረው ጥርጊያ የጌታን ወንጌል ነበረ። የትምህርቱ መሠረታዊ ዓላማም እያንዳንዱ ሰው የንስሐ ፍሬ እንዲያፈራ ማድረግ ነበር። የንስሐ ፍሬ ሲባልም የሠሩትን ኃጢአት መተው ብቻ ሳይሆን ፍሬም ጭምር ማፍራት ነው። ለምሳሌ፦ በሰረቁበት እጅ አለመስረቅ ብቻ ሳይሆን በዚያ ወደ መስጠት፣ በዘፈኑበት ከንፈር ዘፈንን መተው ብቻ ሳይሆን በዚያ መዘመር፣ አመንዝረን እንደ ሆነም ይኸን መተው። መጥምቁ ዮሐንስ በቃል ብቻ ሳይሆን በልብሱም ጭምር ይሰብክ ነበር። ምግባራችን እንደ ሞተ እንስሳ ቁርበት ጠፍር፣ ኃጢአታችንም እንደ ግመል ጠጉር ለሆነብን ለእኛ ክብር ይግባውና የእግዚአብሔር በግ እርሱ ክርስቶስ ይቀበልልን ዘንድ እንደ መጣ ይመሰክር ነበር።

እኛ ሁላችን ወደ ገዛ መንገዳችን ስናዘነብል፤ በከንቱም የማይበላውን በልተን ስንሞት እርሱ በ30 ብር ተሽጦ እኛን ግን በማይተመን ዋጋ ገዝቶ ከዓለቱ ማር በልተን እንደሚያጠግበን ያውጅ ነበረ (መዝ.81+16)።

መስከረም ዐሥራ ሰባት

መስቀል

የዕለቱ የትምህርት ርእስ
የመስቀል እንቅፋት ተወግዷል
(ገላ. 5+11)

የዓለምን መድኃኒት ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስን አይሁድ በምቀኝነት ሰቅለው ገደሉት፤ ከገደሉት በኋላ ሕግ መተላለፋቸውንና አንዳች በደል ያልተገኘበትን ጌታ በመግደላቸው ሕግ ተላልፈው ጻድቁን ገደሉት ይሉናል በማለት እና የመስቀሉን ተአምራት በማየት ክርስቲያኖች እንዳይድኑበት መስቀሉን ጉድጓድ ቆፍረው ቀበሩት።

ከሦስት መቶ ዓመት በኋላ ክርስቶስ እንደተሰቀለ ሆኖ በልቧ የተሳለው ሁሉም የመስቀሉ ፍቅር የሚያቃጥላት ንግሥት ዕሌኒ በ319 ዓ.ም መስቀሉን ፍለጋ ከሮም ወደ ኢየሩሳሌም መጣች። ከንጉሥ ቆንስጣ የወለደችው ንጉሡ ቆስጠንጢኖስ አስፈላጊውን ሁሉ አደረገላት፤ ምክንያቱም የመስቀሉን ኃይል በዓይኑ አይቷልና። ጠላት ሲነሳበት በወታደሮቹ መለዮ(ኮፊያ)፣ በመሳሪያቸው፣ በጦር መያዣቸው፣ በፈረስ ልጓሞቻቸውና በልብሳቸው የመስቀል ምልክት እንዲያደርጉ ትእዛዝ እያስተላለፈ ድልን ይጎናፀፍ ነበር። ከዚህም የተነሳ ዓለምን አንድ አድርጋ ትገዛ በነበረችው ሀገር በሮም ኢጣልያ የሚነግሡ ዓላውያን ነገሥታት እነ ኔሮን ቀሳር፣ ዳርዮስ፣ ዲዮቅልጥያኖስ፣ መክስሚያኖስ፣ ትራጃን ወ.ዘ.ተ. ለጣዖት ስገዱ ሃይማኖት ካዱ በማለት በክርስቶስ ያመኑትን ወገኖች ይጨፈጭፏቸው ነበር። አብያተ ክርስቲያናት እንዲዘጉና አብያተ ጣዖታት እንዲከፈቱ አዋጅ አስነግረው ነበር። ነገር ግን ንጉሥ ቆስጠንጢኖስ አዋጁን በአዋጅ በመሻር አብያተ ክርስቲያናት እንዲከፈቱ አደረገ። ለእግዚአብሔር ምስጋና ይሁን።

የዛሬው በዓል የደመራ በዓል በመባል ይጠራል። የበዓሉ ባለቤት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ስትሆን በዓሉ አገር አቀፋዊ ብቻ ሳይሆን ዓለምአቀፋዊ በዓልም ነው።
ወደ ኢየሩሳሌም ያመራችው ንግሥት ዕሌኒ ኢየሩሳሌም ደርሳ ስለ ነገረ መስቀሉ ስትመረምር ኪራኮስ የሚባል አረጋዊ ሽማግሌ መስቀሉ ያለበትን እንዲህ ሲል ነገሯታል «ከሦስቱ ተራራዎች በአንዱ ነው ያለው ይባላል» ብሏታል።
እርሷም ሱባኤ ገብታ ስትጸልይ የእግዚአብሔር መልአክ ዕሌኒ ዕሌኒ ብሎ ጠርቶ በእራይ ነገሯት ካህናትን ሰብስባ ጸሎት እንድታስደርስ፣ ጸሎት ዕጣን የተጸለየበት እጣን በመያዝ ደመራ ሠርታ በእሳት እንድትለኩሰው አዘዛት። የደመራውም ጭስ መስቀሉ ያለበትን ቦታ በዛሬው ዕለት መስከረም 16 ቀን አመለከታት።
ከዚህ በኋላ መስከረም 17 ቀን ማስቆፈር ጀምራ መጋቢት 10 ቀን ከተቀበረበት አውጥታዋለች። መስቀሉ ሲወጣ እንደ ፀሐይ ዓለምን አበራ። አብሮ የተቀበረው ወንበዴዎቹ ተሰቅለውበት የነበረው መስቀልም ተገኝቷል። ግን ኃይል አልነበረውም፤ ዛሬም የጌታን መስቀልና የወንበዴዎቹን መስቀል መለየት ያስፈልጋል።
መጋቢት 10 ቀን መስቀሉን ያገኘችው ንግሥት ዕሌኒ በኢየሩሳሌም ታላቅ ቤተ መቅደስ አሠርታ አስቀመጠችው። በዓለም የሚኖሩ ክርስቲያኖች ሁሉ ወደ ኢየሩሳሌም በመሄድ ከመስቀሉ በረከትን ማግኘት ጀመሩ። ይህንን የተመለከቱ አሕዛብ(በመስቀሉ ያላመኑ) ክርስቲያኖች እንዳይድኑበት እንደ ቀድሞው እንደ አይሁድ አህዛብ የተባሉት ፋርሶች ኢየሩሳሌምን ወርረው መቅደሱን ሰብረው መስቀሉን ዘርፈው ወሰዱት። ከዚህ በኋላ የቢዛንታይን ንጉሥ የነበረው ሕርቃል ምእመናን በጸሎት እና በምህላ እንዲረዱት ጠይቆ ወደ ፋርስ በመዝመት ድል አድርጎ መስቀሉን ይዞ ተመለሰ። ቅዱስ መስቀሉም ለ714 ዓመታት በኢየሩሳሌም ከቆየ በኋላ ወደ ግሪክ ወስደው የዓለም ክርስቲያን ነገሥታት ለበረከት ተካፍለውታል። የጌታችን ቀኝ እጅ ያረፈበት መስቀልም ለአፍሪካ ደረሰ። ከአፍሪካም ለግብጽ።

መጥምቁ ዮሐንስ በነበረው ታማኝ አገልጋይነት የማይገባ ሥራ የሚሠሩትን በመገሠጹ ለጌታው የተወደደ መሥዋዕት ሆኖ ተሰይፏል። ጨካኞች ስለ ልደት በዓላቸው ደስታ ብለው ንጹሑን ገደሉት። እንገቱንም ስለ ዘፈን ብለው ቆረጡት። እርሱ ስለ እነርሱ ጥቅም ብሎ ሊመክራቸው እነርሱ ግን ስለ ክፋታቸው ሰየፉት።

ትምህርት

* እንደ መጥምቁ ዮሐንስ ምስክር መሆን (ማቴ.14+3)
* በዘፈን አለመማረክ (ማቴ.14+5)
* የምንለምነውን ማወቅ (ማቴ.14+9 ፤ ማቴ 20+22)

መልእክት

ከዚህ ምን እንማራለን? የዛሬዋ ሄሮድያዳ ማን ትሆን? የዛሬው ዮሐንስስ ማን ነው? የምናከብረውስ በዓል የማንን ልደት ነው? የእነ ሄሮድስ ወይስ ... ?

ብዙዎች ይህን አጸያፊና ክብራችንንም የሚያዋርድ ተግባር በየሠርግ ቤቱ፣ በየጭፈራ ቤቱ፣ እንዲሁም በተለያየ ቦታ ያደርጉታልና እናንተ ቀነጃጅት እናንተም ባለ ትዳር ሴቶች ሆይ ይህን አድምጡ!! ብዙዎች ይህ በስካር መንፈስ የተመላውን ድርጊት በመከተል ይሄዳሉና ክፉው ወደ ጥልቁ እንዳይጥላችሁ እናንተም ጉብዛዝት ሆይ ይህን አድምጡ!! በሌላ ዓመት ወደ እግዚአብሔር ቤት ከመሔድ ይልቅ ወደ እንደዚህ ዓይነት የክፋት ሸለቆ ብትሄዱ የመንግሥቱን እኩሌታ እንኳን እንደሚሰጣችሁ ቃል በመግባት ያጠምዳችኋልና እወቁበት /ማር.6፡23/።

ሁላችንም ወደ እንደዚህ ዓይነቱ የጥፋት ጉብኝት ከመሄድ ተቆጥበን ለእነ ሄሮድያዳና እርሷን ለሚመስሉ እኅቶቻችን እናልቅስላቸው። ምንም እንኳን ዛሬ ዮሐንስ ባይታረድም የክርስቶስ ልጆች ግን ከዚሁ ክፉ ሁኔታ በየቦታው እየታረዱ ነው። ነገር ግን እንደ ዮሐንስ አንገታቸውን ሳይሆን

ነፍሳቸውን በእነ ሄሮድያዳ ልጆች ዘፈን በዘመናችን እየተቀረጠ ነው። /1ቆሮ.6፡15/።

ዛሬ እነ ሄሮድያዳ በአካል ባይኖሩም እኅቶቻችንን በየጭፈራ ቤቱ የሚያስጨፍረው የወንድሞቻችንንም የነፍስ እንገት የሚቆርጠው ዲያብሎስ ሥራውን ያለመታከት እየሠራ ነው።

በነጻነት እንኖር ዘንድ ክርስቶስ ነጻ አውጥቶን ሳለ አሁን ወደ እነ ሄሮድስ ድግስ እየሄድን ክርስቲያኖች መባል እንኳን ይገባን ይሆን? ወደሲኦል የሚያመሩ መንገዶችስ "የሐሰት አፍላጋት ናቸው" እያልን ራሳችንን የምናስተው እስከ መቼ ይሆን?

የቅዳሴ ምንባብ

1ቆሮ 6፤1-11

1ዮሐ 3፤10-16

የሐዋ 13፤24-28

ምስባክ ፦ ወይርአዩ አሕዛብ በቅድመ አዕይንቲነ
በቀለ ደሞሙ ለአግብርቲከ ዘተክዕወ
ይባእ ቅድሜከ ገዐሮሙ ለሙቁሓን /መዝ 78፤10-11/

ወንጌል ማርቆስ 6፤14-30

ቅዳሴ ዘወልደ ነጎድጓድ /ጎሐ/

እንዴት ወደ ኢትዮጵያ ገባ?

በኢትዮጵያ አጼ ዳዊት በነገሡበት ዘመን ግብጻውያን በክርስቲያኖች ላይ ስልጣነው ግብጽ ሀገር አፍሪንጅ ተብሎ በሚጠራው አካባቢ ይኖሩ የነበሩ ክርስቲያኖችን ጨፈጨፉ።
አጼ ዳዊት ጭፍጨፋው ካላቆመ ወደ ግብጽ ወታደሮችን እንደሚያዘምቱና የዓባይን ወንዝም እንደሚገድቡባቸው ትእዛዝ አስተላለፉ። በዚህ ጊዜ የግብጽ መንግሥት ዲፕሎማቶቹን የወርቅ፣ የብርና የዘሆን ጥርስ ሉሎችንም ገጸ በረከቶች በማስያዝ አጼ ዳዊትን እንዲማፀኑ ላካቸው።
አጼ ዳዊትም ወርቅና ብር እንደማይፈልጉ የክርስቲያኖች ጭፍጨፋ እንዲቆም ነገር ግን ግብጽ የተቀመጠውን ግማደ መስቀልና ቅዱስ ሉቃስ የሳላትን የእመቤታችንን ስዕለ አድኅኖ እንደሚፈልጉ ነገረው መለሷቸው።
ከዚህ በኋላ ግማደ መስቀሉን እና የእመቤታችንን ቅዱስ ሉቃስ የሳላትን ምስለ ፍቁር ወልዳ ስዕል ከግብጽ ተረከቡ። እሳቸውም በሱዳንና በኢትዮጵያ ድንበር አካባቢ ልዩ ስሙ ስናር ከሚባል ቦታ ሲደርሱ መንገድ ላይ አርፈዋል። ልጃቸው አጼ ዘርአያዕቆብም መስቀሉን «አንብር መስቀልየ በዲበ መስቀል» በተባሉት መሠረት በዳግማዊት ጎልጎታ ግሸን ደብረ ከርቤ አስቀምጠውታል።

የመስቀል ደመራ በዓል አጀማመር

ደመራ የሚለው ቃል - ደመረ፣ ጨመረ፣ አንድ አደረገ፤ ከሚለው የግእዝ ቃል የተወሰደ ሲሆን መቀላቀልን፣ መገናኘትን፣ መሰብሰብን፣ መጣመርን፣ መዋሐድን በአጠቃላይ ሱታፌን፣ አንድነትን እና ኅብረትን ያመለክታል። ቅዱስ መስቀሉ በተገኘበት ቦታ የደመራ ዕንጨቶች የሚደመሩበት የበዓለ መስቀል ዋዜማ ነው።ቤተ ክርስቲያናችን ከምታከብራቸው ከዘጠኙ የጌታችን ንዑሳን በዓላት አንዱ በዓል ነው።

መስቀል ኢየሱስ ክርስቶስ የሰውን ልጆች ለማዳን የዘለዓለም ሕይወትን ለመስጠት መስዋዕትነት የከፈለበት ቅዱስ ሥጋውን ክቡር ደሙን ያፈሰሰበት መንበር፥ ሲሆን እምነታችንን የምንመሰክርበት መስታወት ነው።

ይህ ዕለት ከ300 ዓመታት በላይ ጠፍቶ የነበረውን ቅዱስ መስቀል በንግሥት ዕሌኒ አማካኝነት መገኘቱን የምንዘክርበት በዚህም ደስ የምንሰኝበት ዕለት ነው።

በዓለ መስቀል፣ በክርስትና ሃይማኖት ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በቀራንዮ የተሰቀለበት መስቀል በአይሁድ ከተቀበረበት ሥፍራ መገኘቱን ማስታወሻ በዓል ሲሆን በምዕራብም በምስራቅም አብያተ ክርስቲያናት ይሄንን መታሰቢያ መስከረም 3 ቀን ሲያከብሩት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ደግሞ በየዓመቱ መስከረም 17 ቀን ታከብራለች።

ትምህርት

* በመስቀሉ ድነናል ፤(ኤፌ 1+7 ፤ 1ኛጴጥ1+19)
* በመስቀሉ ክርስቶስ ወደ ራሱ አቅርቦናል፤ (የሐ 12+32)
* በመስቀሉ ሠላምን አግኝተናል፤ (ሮሜ 5+10፣ ቆላ 1+20)
* በመስቀል ላይ በፈሰሰው ደሙ ጽድቅን ቅድስናን እና ቤዛነትን አግኝተናል (ሮሜ5+2 ፣1ኛቆሮ 1+31፤ ዕብ 10+10)፤
* በመስቀሉ የእዳ ደብዳቤያችን ተደምስሷል። (ቆላ.2+14)
* በመስቀሉ ወደ ቅድስተ ቅዱሳኑ ለመግባት ሞገስን አግኝተናል (ዕብ.10+19)
* መስቀል ኃይላችን እና መመኪያችን እንደሆነ ተረድተናል።
  * በመስቀሉ አዲስ ኪዳን ተመስርቶልናል (ሉቃ.22+20) ስለዚህ እንመካበታለን፤
  * ስለ እኛ በመስቀል ላይ መከራ የተቀበለውን የክርስቶስን ፍለጋ መከተል፤(1ኛጴጥ.1+20)
  * የተሰቀለውን ክርስቶስን መስበክ፤(1ኛቆሮ.1+23)
  * ሞቱን እስከ ዳግም ምፅዓት ማወጅ፤ (1ኛቆሮ.11+26)
  * በመስቀሉ ላይ ለድኅነት የፈሰሰውን ቅዱስ ምስጢር በእምነት መቀበል ከኛ ይፈለጋል፤ (ማር.14+22)

መልእክት

የመስቀሉ ነገር በብዙዎች ዘንድ የጥበብ ተቃራኒ የሆነ ሞኝነትን መስሎ መሰናከል ሆኗል። ለሚያምኑት ግን የእግዚአብሔር ኀይልና ጥበብ ነው። ዓለም በጥበቡና በዕውቀቱ፣ በኀይሉም አልዳነም። ምክንያቱም እግዚአብሔር የዓለምን ኀይል፣ ጥበብና ዕውቀት ሞኝነት በመሰለው በመስቀል ነገር ከንቱ አድርጎታል። ስለሆነም በድካምና በሞኝነት ማለት በመስቀል ስብከትና በእምነት ዓለምን ለማዳን የእግዚአብሔር ፈቃድ ሆኗል። ስለ መስቀልና በመስቀል ስለተሰቀለው ክርስቶስ መስበክ በማያምኑት ዘንድ ሞኝነት፣ ድካምና መሰናከል ቢመስልም በምእመናን ዘንድ ግን የእግዚአብሔር ኀይል ሆኖ ይታያል። ምክንያቱም በሰው ዘንድ ሞኝነት ሆኖ የታየው የእግዚአብሔር ሥራ ከሰው ጥበብ ይልቅ ስለሚጠበብ ነው። በሰው ዘንድ ድካም ሆኖ የታየው የእግዚአብሔር ሥራም ከሰው ኀይል ይልቅ ስለሚበረታ ነው። እንግዲህ ቅዱስ መስቀል በሚያምኑና በማያምኑ መካከል መለያ ምልክት ነው፤ መስፈሪያ ሚዛንም ነው። ለእኛ ለምናምን ቅዱስ መስቀል ወደ ሰማይ የምንደርስበት መሰላል ነው። ለማያምኑ ግን ወደ ሰማይ እንዳይደርሱ የሚሰናከሉበት እንቅፋት ነው።

በክርስቶስ አምናለሁ የሚል ሁሉ እንደ አይሁድ «መስቀሉን አይቅበር» ነገር ግን እንደ ቅድስት ዕሌኒ መስቀሉን ይፈልግ፤ መስቀል ከሁሉ ነገር በላይ ነውና።

እግዚአብሔር በመስቀሉ ኃይል ይጠብቀን። አሜን!!

የቅዳሴ ምንባብ

1ጢሞ 5፣9-16
ያዕቆ 3፣11
የሐዋ 5፣26-33

ምስባክ ፦ ወወሀብኮሙ ትእምርተ ለእለ ይፈርሁከ
ከመ ያምስጡ እምገጸ ቅስት
ወይድኀኑ ፍቁራኒከ መዝ 59፣3-5 /131፣6-7/
ወንጌል ማቴ 8፣16 ዮሐ19፡25 (እግዚእ)

መስከረም ሃያ አንድ
የብዙኃን ማርያም
ጉባኤ ኒቅያ

የዕለቱ የትምህርት ርእስ
ትውልድ ሁሉ ብፅዕት ይሉኛል። (ሉቃ.1+48)

መስቀሉ ወደ ግሸን ደብረ ከርቤ የገባበት ዕለት
የመስከረም 17 ታሪክ ይመልከቱ

መስከረም ሃያ ዘጠኝ
ዕረፍታ ለቅድስት አርሴማ

የዕለቱ የትምህርት ርእስ
ሴቶችም እስከሞት ድረስ ተደበደቡ

(ዕብ11+35)

ቅድስት አርሴማ ሰማዕት። በአርመንያ ታኅሣሥ 6 ቀን ሐሙስ ዕለት ተወለደች። አባቷ ቁምድርስ እናቷ አትናስያ ይባላሉ። የበረችበት ዘመን ዘመነ ሰማዕታት በመባል ይታወቃል። ዲዮቅልጥያኖስ ቆንጆ ሴት ፈልጋችሁ አምጡልኝ ብሎ ሠራዊቱን በየሀገሩ ላከ አምጡልኝ ሲላቸው አርሴማ በተራራ ተቀምጣ ነበር፤ እርሷም የእግዚአብሔር መንፈስ ተገልጦላት ወደ አርመንያ ሄደች። ይህንን ሰምቶ ለንጉሡ ለድርጣድስ አስፈልጋህ ላክልኝ ብሎ ላከበት አስፈልጎ አገኛት እርሷም መልክ መልካም

ከንግሥታት ወገን የሆነች ሚስት አጨላቸው ወደ ጽርዕ በመሄድ ገዳመ ዳውናስ ገቡ አበምኔቱ አባ ዲሜጥሮስ ፈቃደ እግዚአብሔር መሆኑን አውቆ ማዕረገ ምንኩስና ሰጥቷቸዋል።

ከዘመዶቻቸውም ለምንቱ ዜናቸውን ሰምተው እንደሳቸው ዓለምን ትተው ገዳም ገብተው በምንኩስና ተወስነው ኖረዋል። እናታቸውም ንግሥት እድና ዜናቸውን ሰምታ ልትጠይቃቸው መጥታ ልጄ አንተ በሕጻንነትህ የናቅከውን ዓለም ለኔስ ምን ያደርግልኛል አለቻቸው ደስ አላቸው ማዕረገ ምንኩስና አሰጥተው በምኔት እንድትኖር አስቀመጧቸው።

ከ12 ዓመት በኋላ በአንድነት ከባልደረቦቻቸው ጋር ለብሕትውና ለጸሎት የማይመቻቸው ቢሆን አባ አረጋዊ ከዘመዶቻችን መለየታችን ዓለምን ትተን መውጣታችን በጾምና በብሕትውና ልንኖር አይደለምን? ብለው አባ ሊቃኖስ ደብረ ቆናጽል፤ አባ ጰንጠሌዎን ሁለት ምዕራፍ ያህል እርቀው አባ ይስሐቅ (ገሪማ) መደራ፤ አባ ጽሕማ ፣ሊዱጌያ አባ ይምአታ ፣ገርዓልታ አባ አፍጼ፣ ይሐ አባ አሌፍ፣ አሕሰአ ፣ሁሉም በዓት ሰርተው በምናኔ ተቀምጠዋል።

አባ አረጋዊ እናታቸውን ቅድስት እድናን ደቀ መዝሙራቸው ማትያስን አስከትለው እግረ መንገዳቸውን እያስተማሩ ሕሙማንን እየፈወሱ ደብረ ዳሞ ደረሱ። ለተከተሏቸው ብዙ ሴቶች ከተራራ ሥር ገዳም ገድመውላቸው እናታቸውን እመምኔት አድርገው ሾመውላቸዋል። ከተራራው ሥር ሆነው ይህንን ተራራ በምን ልውጣው እያሉ ሲያወጡ ሲያወርዱ የታዘዘ ዘንዶ 60 ክንድ በሚያህል ጅራቱ ጠምጥሞ ይዞ ቅዱስ ሚካኤል የእሳት ሰይፍ ይዞ እየጠበቃቸው ከተራራው ጫፍ አድርሷቸዋል። ሃሌ ሉያ ለአብ ሃሌ ሉያ ለወልድ ሃሌ ሉያ ለመንፈስ ቅዱስ ብለው አመስግነዋል ገዳሙ ደብረ ሃሌ ሉያ የተባለው በዚሁ ምክንያት ነው።

አባ አረጋዊ የተባሉበት ምክንያት የተጣሉትን ሽማግሌ ሆነው በማስታረቃቸው በአጠቃላይ መንፈሳዊ ሥራቸው ሁሉ እንደሽማግሌ

ስለሆነ አረጋዊ (ሽማግሌ) ተብለዋል። ለመጀመሪያ ጊዜ ምንኩስና በኢትዮጵያ የተጀመረው በደብረ ዳሞ ነው።

ትምህርት
▪ ከማያምኑት መካከል ተለይቶ መውጣት
« ርኩስን ነገር አትንኩ ከመካከላቸው ውጡና ንጹሐን ሁኑ» (ኢሳ.52+11)
▪ ዓለምን ስለ እግዚአብሔር ብሎ መተው ።
« ዓለምን ወይም በዓለም ያሉትን አትውደዱ »
(1ዮሐ 2+16 ያዕ 4+ 4)

መልእክት

ጻድቁ አባታችን አቡነ አረጋዊ ዓለምን ስለ እግዚአብሔር ጥለው ከቤተሰቦቻቸው የተዘጋጀላቸውን ምድራዊ ሥልጣን አላፊ መሆኑን ተረድተው ከቤተሰቦቻቸው ተለይተው ወጡ። ከአቡነ አረጋዊ ሕይወት የምንማረው ይህ ዓለም ጊዜያዊና ጠፊ መሆኑን አውቀን የማያልፈውን የእግዚአብሔርን መንግሥት ለመውረስ እንድንችል ራሳችንን ለእግዚአብሔር በመስጠት፣ ከእምነታችን ከሚለዩን ነገሮች ርቀን ወደ እግዚአብሔር መቅረብን ነው። «ሐሆ በልዎ ለእግዚአብሔር ወእንበየ በልዎ ለሰይጣን» እግዚአብሔርን እሺ በሉት ወደ እናንተም ይቀርባል ሰይጣንን እምቢ በሉት ከእናንተም ይርቃል። ለክብር እንድንበቃ አምላካችን እግዚአብሔር ይርዳን። የጻድቁ አማላጅነት አይለየን አሜን።

የቅዳሴ ምንባብ

1ቆር 7፣36
ዕብ 2፣18
የሐዋ 8፡27

ምስባክ ፦ አልቦ ነገር ወአልቦ ነቢብ ዘኢተሰምዐ ቃሎሙ
ውስተ ኩሉ ምድር ወጽአ ነገሮሙ ወእስከ አጽናፈ ዓለም
በጽሐ ነቢቦሙ /መዝ 18፣3/
ወንጌል ማቴ 19፣26 ቅዳሴ ቅዳሴ / ዘሐዋርያት/

ሴት መሆኗን አይቶ ይህችንስ ለማንም አላሳልፍ አልሰጥም ብሎ ዶርታንን ለምኚልኝ አላት ለመንግሥተ ሰማያት የታጨሽ ነሽና ይህ አላዊ እንዳያረክስሽ አለቻት መልኳን አይቶ በሰማት ተሸንፎ ሀሎ ያለት ከእግዚአብሔር ኃይልመንፈሳዊ ተሰጥቷታልና ትትታ ከመሬት ጣለችው። በሰይፍ መስከረም 29 ቀን አስቆረጣት በ27 ዓመቷ በሰማዕትነት በዚህ ዕለት አረፈች።

ትምህርት

• በእምነት መጽናትን
እስከመጨረሻ የሚጸና ግን እርሱ ይድናል። (ማቴ.24+13)
• ከሥጋዊ ደስታ ይልቅ መንፈሳዊ ነገር መምረጥ
ሰው ዓለሙን ሁሉ ቢያተርፍ ነፍሱንም ቢያጎድል ምን ይጠቀመዋል? (ማቴ.19+26)
• የሚበልጠውን ዋጋና ክብር ማየት
በኃጥአን ድንኳን ከመቀመጥ ይልቅ በቤትህ መጣል ይሻለኛል የሚበልጠውን ክብር አይቶ እምቢ ማለትን «ሙሴ የፈርዖን የልጅ ልጅ እንዳይባል በእምነት እምቢ አለ» (ዕብ 11+24)

መልእክት

ሰማዕት ቅድስት አርሴማ በምድራዊና በሚጠፋ ነገር ያልተንበረከከች ታላቅ ሰማዕት ናት። እኔ የክርስቶስ ሙሽራ ነኝ በማለት የንጉሡን ዙፋን ሳትፈራ መስክራለች። እኛም በዚህ ዘመን የምንኖር ክርስቲያኖች በጽናት የክርስቶስ ነኝ ልንል ይገባናል። የክርስቶስ ከሆንን ከክርስቶስ ማንም ሊለየን አይችልምና (ሮሜ 8+35) እንደ ቅድስት አርሴማ በእምነታችን እንጽና። የሰማዕቷ የቅድስት አርሴማ በረከትና አማላጅነት አይለየን አሜን ።

የቅዳሴ ምንባብ

ገላ 4፣11-12
ዮሐ 1፣1
የሐዋ 3፣1-12

ምስባክ
እግዚአብሔር ይቤለኒ ወልድየ አንተ
ወአነ ዮም ወለድኩከ
ሰአል እምኔየ እሁበከ አሕዛበ ለርስትከ
ወንጌል ሉቃ 21፡21
ቅዳሴ ዘእግዚእ

ጥቅምት አምስት
አቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስ ቃል ኪዳን የተቀበሉበት

የዕለቱ የትምህርት ርእስ
የጻድቃን መታሰቢያ ለዘላለም ይኖራል (መዝ.112+6)
የመጋቢት 5 ታሪክ ይመልከቱ

ጥቅምት ዐሥራ አራት
አቡነ አረጋዊ

የዕለቱ የትምህርት ርእስ
ከመካከላቸው ውጡና የተለያችሁ ሁኑ !

(2ቆሮ 6+ 17)

አቡነ አረጋዊ ከዘጠኙ ቅዱሳን አንዱ ናቸው። የመጀመሪያ ስማቸው ዘሚካኤል ሀገራቸው ሮም /ጣሊያን/ አባታቸው ይስሐቅ እናታቸው እድና ይባላሉ። ጥበብ መንፈሳዊ ሲማሩ አድገው 14 ዓመት ሲሆናቸውም

ጥቅምት ዐሥራ ሰባት ቅዱስ እስጢፋኖስ ቃል ኪዳን የተቀበለበት ዕለት

የዕለቱ የትምህርት ርእስ
ሰማይ ተከፍቶ የእግዚአብሔርን ክብር አየ (የሐዋ 7+55)
የጥር 1 ታሪክ ይመልከቱ

ጥቅምት ሃያ ሰባት መድኃኔዓለም

የዕለቱ የትምህርት ርእስ
በእርሱም ቍስል እኛ ተፈወስን (ኢሳ.53+5) የመጋቢት 27 ታሪክ ይመልከቱ

ኅዳር ስድስት ቁስቋም

የዕለቱ የትምህርት ርእስ
የሕፃኑን ነፍስ የፈለጉት ሞተዋልና ተነሣ

(ማቴ.2+20)

ኅዳር 6 ቀን እመቤታችን ጌታን ይዛ ከግብጽ /ከስደት/ ወደ ደብረ ቁስቋም መመለሷ ይታሰባል። «ሄሮድስም ከሞተ በኋላ እነሆ የጌታ መልአክ በግብጽ ለዮሴፍ በሕልም ታይቶ የሕፃኑን ነፍስ የፈለጉት ሞተዋልና ተነሣ

ሕፃኑንና እናቱን ይዘህ ወደ እስራኤል ሀገር ሂድ አለው። ዮሴፍም ተነስቶ ሕፃኑንና እናቱን በመያዝ ወደ እስራኤል ምድር ተመለሰ፤ ነገር ግን አርኬላዎስ በአባቱ ፈንታ በይሁዳ መንገሡን በሰማ ጊዜ ወደዚያ መሄድ ፈራ፤ በሕልምም ተረድቶ ወደገሊላ ሀገር ሄደ፤ በነቢያት ናዝራዊ ይባላል የተባለው ይፈጸም ዘንድ ናዝሬት ወደምትባል ከተማ መጥቶ ኖረ» /ማቴ. 2+19-23/።

ወንጌላዊው ቅዱስ ማቴዎስ ወደ ናዝሬት የሄዱበትን ሰላም ምክንያት ይነግረናል፤ ትንቢት። «በነቢያት ልጁ ናዝራዊ ይባላል የተባለው ይፈጸም ዘንድ ናዝሬት ወደምትባል ከተማ መጥቶ ኖረ» /ማቴ.2-23/

ትምህርት

▪ የመከራና የስደት ዘመን ፍጻሜ እንዳለው ማመን
(2ኛጢሞ.3+12)
▪ የኃጥአን ሩጫ በሞት እንደሚገታ ማወቅ
(መዝ.36+35)

የቅዳሴ ምንባብ

2ቆሮ 8፣1
2ዮሐ 1፣9
የሐዋ 1212

ምስባክ፦ ርኢክዎ ለኃጥእ ዐቢየ ወተለዐለ ከመ ዕፀ ሊባኖስ
ወሶበ እኀልፍ ኃጣእክዎ

ኀሠሥኩ ወኢረከብኩ መካኖ /መዝ 37፥35/
ወንጌል ማቴ 2፥19 ቅዳሴ ዘእግዚእ

መልእክት

በክርስትና ሕይወት ስንኖር መከራና ስደት የሚገጥመንን አስቀድሞ አምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስ ተሰዶ ስደትን ባርኮልናል። ስለዚህ ክርስቲያን በመሆናችን ምክንያት የሚመጣብንን ስደት መከራ በትእግስት በመወጣትና በጸጋ መቀበል ይገባናል።

ኀዳር ሰባት
ቅዱስ ጊዮርጊስ በአንዲት መበለት ቤት የታሰረበት ዕለት

የዕለቱ የትምህርት ርእስ

መንክር እግዚአብሔር በላዕለ ቅዱሳኒሁ (መዝ 67፥35)

እግዚአብሔር በቅዱሳኑ ላይ ድንቅ ነው

በዚህ ዕለት ንጉሡ ዱድያኖስ ሰማዕቱ ቅዱስ ጊዮርጊስን በረሀብ እንዲሞት አዘዘ በቤቷ ምንም የምትቀምሰው የምትልሰው ከሌላት ከአንዲት መበለት ቤት አስገብቶ ከቤቷ ምሰሶ ቢያስረው ቅዱስ ጊዮርጊስ የታሰረበት ምሰሶ ለምልሟል።

ትምህርት

- እግዚአብሔር በቅዱሳኑ ላይ ድንቅ ነገር ማድረጉን «ምስክሮችህ ድንቆች ናቸው ስለዚህ ነፍሴ ፈለገቻቸው» (መዝ 115፥129)
- ቅዱስ ጊዮርጊስ የታሰረበት የመበለቲቱ የቤቷ ምሰሶ መለምለሙን
- የታመመው ልጇ መፈወሱን
- ቤቷ በበረከት መሞላቱን

መልእክት

ሰማዕቱ ቅዱስ ጊዮርጊስ በወጣትነት ጊዜው ከባላቂያን ነገሥታት ሹመትና ሽልማት ይልቅ በእግዚአብሔር ፊት ምንበርና ከበሬታን መረጠ የእኛስ ምርጫ ምን ይሆን? ሹመት፣ ገና ፣ ክብር ...... ወይስ.....?የሰማዕቱ አማላጅነት አይለየን።

የቅዳሴ ንባብ

ኤፌ 5፥23

1ጴ 4፥12

የሐዋ 28፥1

ምስባክ፦ ወይርአዩ አሕዛብ በቅድመ አዕይንቲነ መዝ 78፥10

ወንጌል ማቴ 10፥16

ቅዳሴ /ዘባስልዮስ/

- ፈርዖንና ሠራዊቱ በኤርትራ ባሕር የሠጠሙበት (ዘጸ.14፥28)
- በበጉ ደም ሕዝበ እስራኤል ከሞተ በኩር የዳኑበት (ዘጸ.12፥23)
- የግብጻውያን አማልክት የተዋረዱበት
- የእግዚአብሔር አስደናቂ ተአምር የታየበት (ዘጸ.14፥14)
- እስራኤላዊያን የተደሰቱበት (ዘጸ.15፥2)

መልእክት

ከ430 ዓመታት በኋላ እስራኤላውያን ከፈርዖን የባርነት አገዛዝ ነፃ ወጥተዋል። እኛም በዘመናችን ከዲያብሎስ ባርነት መላቀቅ ይገባናል። «በነጻነት ልንኖር ክርስቶስ ነጻ አውጥቶናልና» (ገላ.5፥1) እኛም የማንረሳው ሌሊት ከሞት ወርደት የተገነነበት ሌሊት ቃሉን በምስጋና ተሞልተን ለመዘምር ያደርገበትን ሌሊት ልንረሳው አይገባንም።

የእግዚአብሔር ቸርነት አይለየን አሜን

የቅዳሴ ምንባብ

ሮሜ 9፥17
ይሁዳ 1፥9
የሐዋ 20፥28

ምስባክ ፦ ይትዐየን መልአከ እግዚአብሔር ዐውዶሙ
ለእለ ይፈርህዎ ወያድኅኖሙ
ጠዐሙ ወታእምሩ ከመ ኄር እግዚአብሔር /መዝ 33፥7/

ወንጌል ማቴ 18፥15

ቅዳሴ /ዘባስልዮስ/

ኀዳር ሃያ አንድ
ጽዮን

የዕለቱ የትምህርት ርእስ

ኢካቦድ

የእግዚአብሔር ታቦት ተማርካለችና ክብር ከእስራኤል ለቀቀ ማለት ነው (ሳሙ.4፥21)

ካህኑ ዔሊ ከሀነትን ከምስፍና ጋር አስተባብር ይዞ በነበረበት ጊዜ ሁለቱ ልጆቹ አፍኒንና ፊንሐስ እግዚአብሔርን የሚያስቆጣ በደል ፈጹሙ ለእግዚአብሔር የሚቀርበውን መስዋዕት እየቀሙ ለራሳቸው. በሉት ለእግዚአብሔር ክብር ባለመስጠት በመገናኛው ድንኳን ያመነዝሩ ነበር።

ከፍልስጥኤማውያን ጋር ሲዋጉ ወደ ጦር ሜዳ ወጡ። አራት ሺህ ከእስራኤላውያን ወገን በፍልስጥኤማውያን ተገደሉ። የእግዚአብሔር የቃል ኪዳኑን ታቦትንም ለምን አናመጣም? ብለው ከሴሎ የቃልኪዳኑን ታቦት አመጡ። አፍኒንና ፊንሐስም በዚያ ነበሩ ፍልስጥኤማውያንም በግብጽ የሆነውን ሰምተዋልና «ወዬ ለነ፣ወዮልን» አሉ። ፍልስጥኤማውያንም እስራኤላውያንን ገጠሟቸው፤ ከእስራኤል ሠላሳ ሺህ ሰዎች ሞቱ፤ የእግዚአብሔርም ታቦት ተማረከች የካህኑ የዔሊ ልጆች አፍኒንና ፊንሐስም ሞቱ።

አንድ ብንያማዊ ሰው ከሰልፍ እየሮጠ ልብሱን ቀድዶ በራሱም ላይ ትቢያ ነስንሶ ወደ ሴሎ መጣ ዔሊም ስለታቦቱ ልቡ ተናውጦ ነበርና በመንገድ ዳር ላይ በድንኳን ውስጥ ተቀምጦ ይጠባበቅ ነበር ሰውየውም መጥና ለዔሊ ነገረው ዔሊም የዘጠና ስምንት ዓመት ሽማግሌ ነበር። ከሰልፍ የመጣሁ እኔ ነኝ እስራኤል ከፍልስጤማውያን ፊት ሸሹ አፍኒንና ፊንሐስም ሞተዋል። የእግዚአብሔርም ታቦት ተማርካለች አለ ካህኑ

ኀዳር ዐሥራ ሁለት
ቅዱስ ሚካኤል ሕዝበ እስራኤልን እየረዳ ከግብጽ ያወጣበት ዕለት

የዕለቱ የትምህርት ርእስ

የማይረሳ ሌሊት (ዘጸ 12፥42)

በዚህ ዕለት የሚከበረው በዓል እስራኤል ዘሥጋ ለ430 ዓመት በግብጽ ከኖሩ በኋላ በዛሬው ዕለት የወጡበት በዓል ይታሰባል። እስራኤል ወደ ግብጽ ከከነዓን ወጥተው የገቡት በረሀብ ምክንያት ሲሆን ወንድማቸው ዮሴፍንም አስቀድመው ሸጠውት ነበር።

ከከነዓን ተሰደው በረሀብ ምክንያት ወደ ግብጽ 70 ቤተሰብ ሆነው ገቡ። ከብዙ ዘመን በኋላ ዮሴፍን የማያውቅ ፈርዖን ተነሣ። እስራኤል ከእኛ ይልቅ በዝተዋል ጠላት ቢነሳብን ተደርበው ያጠፉናል ብሎ መከራና አገዛዝ አጸናባቸው መከራ እየተቀበሉ ሲሰቃዩ ኖሩ ወንድ ልጆች ሲወለዱ በአዋላጆቻቸው እንዲገደሉ ትዕዛዝ ተሰጠ ራሄል የምትባል ዕብራዊት ባሏ ርቤል ሞቶባት የባሏንም ሥራ ደርበሽ ሥሪ ተብላ ጭቃ ስትረግጥ ምጥ ያዛት ጥቂት ልረፍ አለች የሚያሠራው ግብጻዊ እርጉዟ ብሎ አስገደዳት በማኅፀኗ የነበሩት መንታ ሕጻናት ከእግሯ ሥር ወደቁ የልጅ ደም ግንብ ያጠነክራል ብሎ ከጭቃው ጋር አርገጫቸው አሳት እንባዋን ወደ ሰማይ ረጨች "ቃል ተሰምዐ በራማ ወሰቆቃው ወገዓር ራሔል እንዘ ትበኪ በእንተ ውሉዳ ወአበየት ተናዝዞ ወነጊረ ላሁ" (ኤር.31፥15፣ማቴ.2፥17)

ከዚህ በኋላ እግዚአብሔርም ለሙሴ ፈርዖንን ሕዝቤን ልቀቅ ይልሃል በለው አለው። ፈርዖንም መልሶ እስራኤልን እለቅ ዘንድ እግዚአብሔር ማነው? በማለት የፈርዖን ልብ ደንድኖ አልሰማም አለ በዘጠኝ መቅሰፍት በአሥረኛው ሞተ በኩር ግብጻውያንን መታቸው እግዚአብሔርም ለሙሴ

እንዲህ አለው ጫማችሁን በእግራችሁ በትራችሁንም በእጃችሁ አድርጋችሁ እንዲህ ብሉት እርሱም የእግዚአብሔር ፋሲካ ነው። እኔም በዚያች ሌሊት በግብጽ አገር ከሰው እስከ እንስሳ ድረስ በኩርን ሁሉ እገድላለሁ በግብጽ አማልክት ሁሉ እፈርድባችኋለሁ እኔ እግዚአብሔር ነኝ ደሙም ምልክት ይሆናችኋል። (ዘጸ.11፥11)

እግዚአብሔርም ሙሴን "ሕዝቡን ከባርነት ከግብጽ የወጣችሁበት ይህንን ቀን አስቡ" አለው። (ዘጸ.13፥1)

እንዲህም ሆነ እኩለ ሌሊት በሆነ ጊዜ እግዚአብሔር በዙፋኑ ከተቀመጠው ከፈርዖን በኩር ጀምሮ በግዞት እስካሉት እስከ ምርኮኞቻቸው ድረስ የግብጻውያኑን በኩር መታ። ሕዝቡንም ነፃ አወጣ።

ትምህርት

- **ሁሉን የሚያደርግ እግዚአብሔር ብቻ መሆኑን ማወቅ**
  «እግዚአብሔር ስለእናንተ ይዋጋል እናንተም ዝም ትላላችሁ» (ዘጸ.14፥14)
- **የነፃነት ቀን መዘከር**
  «ከባርነት የወጣችሁበትን ይህን ቀን አስቡ» (ዘጸ.13፥1)
- **ድል ከእግዚአብሔር መሆኑን**
  «እግዚአብሔር ተዋጊ ነው ስሙም እግዚአብሔር ነው» (ዘጸ 15፥3)
- **የዝማሬ ቀን መሆኑን**
  «በክብር ከፍ ከፍ ብሎአልና ለእግዚአብሔር ዘምሩ» (ዘጸ15፥21)

ዔሊም ይህንን በሰማ ጊዜ ከወንበሩ ወድቆ አንገቱ ተሰብሮ ሞተ። (1ሳሙ.4፥14)

ፍልስጥኤማውያን ታቦተ ጽዮንን ማርከው ወስደው በቤተ ጣዖታቸውም ዳጎን ከላይ ታቦተ ጽዮንን ከሥር አድርገው አስቀመጧት።

በማግስቱ የጣዖቱ ካህናት ሲመጡ ዳጎን በታቦተ ጽዮን ፊት ወድቆ አገኙት ከቦታው መልሰውት ሄዱ ሲመለሱ እጅ እግሩ ተቆራርጦ ደረቱ ለብቻው ቀርቶ አገኙት ሰዎችም በእባጭ ተመቱ የአዛጦን ሰዎች የእግዚአብሔር ታቦት በእኛና በአምላካችን በዳጎን ጠንክራብናለችና የእስራኤል አምላክ ታቦት ከእኛ ላይ አይቀመጥ እሱ መቅሰፍቱም ቢጸናባቸው ወደጌት ወሰዱት። የጌት ሰዎችም በመቅሰፍት ተመቱ። ወደ አስቀሎና ቢወስዱት ሊታስረፉን ነውን፤ መልሱን አሏቸው ከ7 ወር በኋላ የበደል መሥዋዕት ይዘው ወደ ቤተሳሚስ በሠረገላ አድርገው አመጡት ለታቦቱ ክብር ባለመስጠታቸው ከመካከላቸው 5ሺህ ሰዎች ሞቱ ፈርተውም ወሰዱልን ወደ ቂርያትይዓርም ላኩ ወስደውም በአሚናዳብ ቤት አስቀመጡት። (1ሳሙ.7፥2)

ትምህርት

- **ለእግዚአብሔር ታቦት ክብር መስጠት (2ሳሙ.6፥11)**
- **የእግዚአብሔር ታቦት (ጽዮን) ድል ያደረገችበት**
  «ዳጎን በእግዚአብሔር ታቦት ፊት በምድር ላይ በግንባሩ ወድቆ ነበር» (1ሳሙ 5፥4)
  «ከእግዚአብሔር ጋር የሚጣሉ ይደቃሉ» (1ሳሙ 2፥10)

መልእክት

ለእግዚአብሔር ክብር ያልሰጡ የካህኑ ዔሊ ልጆች አፍኒንና ፊንሐስ በጠላት እጅ ተገድለዋል። ክብርም ከእስራኤል ለቀቀ ዔሊም ከወንበሩ ወድቆ ሞቷል ታቦተ ጽዮንም ተማርካለች ዛሬስ በዘመናችን ከእግዚአብሔር

ክብር ይልቅ ለራሳችን ክብር የምንሮጥ ስንቶቻችን ነን? በክብር በንጽህና በቅድስና እራሳችንን እየጠበቅን እግዚአብሔርን በማገልገል ላይ የምንገኝስ ስንቶቻችን ነን? ኢካቦድ ክብር ከቤተክርስቲያናችን፣ ከሀገራችን፣ ከሰፈራችን፣ ከቤታችን የለቀቀ አይመስልም? ለምን ይሆን ....?

የድንግል ማርያም አማላጅነት አይለየን አሜን ።

የቅዳሴ ምንባብ
2ቆሮ 6፥12
1ጴ 2፥5
የሐዋ 7፥44

ምስባክ ፦ እስመ ኀረያ እግዚአብሔር ለጽዮን
ወአብደራ ከመ ትኩን ማኅደር
ዛቲ ይእቲ ምዕራፍየ ለዓለም /መዝ 131፥13/

ወንጌል ማቴ 21፥42
ቅዳሴ /ጐሥዓ/

ኀዳር ሃያ አምስት
ዕረፍቱ ለቅዱስ መርቆሬዎስ

የዕለቱ የትምህርት ርዕስ

«ከክርስቶስ ፍቅር ማን ይለየናል?» (ሮሜ 8፥35)

ሰማዕቱ ቅዱስ መርቆሬዎስ ሀገሩ ሮም (ጣሊያን) አባትና እናቱ አረማዊያን ነበሩ። መርቆሬዎስ ሲወለድ አምነው ተጠምቀዋል የመርቆሬዎስ ስመ ጥምቀቱ ፒሉፓዴር ነው ትርጉሙም «ገብረ እግዚአብሔር» ማለት ነው። እግዚአብሔርን በመፍራትና በማክበር ነው ያደገው። አባቱ ሲሞት የአባቱን

ሹመት ወሰደ ዘመኑ ዘመነ ሰማዕታት ስለነበር ንጉሡ ዱኪዮስ የሮ ቄሳር ጣዖትን የሚያመልክና በክርስቲያኖች ላይ መከራና ስቃይን የሚያ ስለነበር በጠላትነት ተነሳበት መልአክ እግዚአብሔር ከአንተ ጋር ነ ጠላትህን ታሸንፋለህ ድል ባደረክ ጊዜ ግን አምላክህን እግዚአብሔርን አት አለው መርቆሬዎስ ኃይል ተሰጥቶት ጠላቶቹን አሸንፎ ሲመጣ መልአክ ስለ ምን የረዳህ አምላክህን ረሳህ? አለው ንጉሡ ዱኪዮስ ቢጠራው ሹመት ሽልማቱ ይቅርብኝ አልፈልግም ብሎ የምስፍናውን ልብስ አውልቆ ጥሎ አምላኬን ነው የማመልከው አለው እርሱም በጅራፍ አስገረፈው ፈርቶ ይመስላል ብሎ ነበር።

መርቆሬዎስ ግን ከእግዚአብሔር ፍቅር ማን ይለየኛል በማለት አልፈራም። በብረት አልጋ አስተኝቶ ከስሩ እሳት አስነደደበት ደሙ ሲንጠባጠብ እሳቱ ጠፍቷል ዐስር ወደ ቂሳርያ ሰደደው ብዙ ታምራት አድርጓል ዑልያኖስ የሚባል ከሀዲ ንጉሥ በምእመናን መከራ አጸናባቸው አብያተ ክርስቲያናትን አቃጠለ መጻሕፍትን ቀደደ የቂሳርያው ሊቀ ጳጳስ ባስልዮስ በዚህ አዝኖ አምላክ ቅዱስ መርቆሬዎስ እያለ ሲማጸን ይኖር ነበር። ሰማዕቱ ቅዱስ መርቆሬዎስ በጥቁር ፈረስ ሆኖ ከሀዲው ዑልያኖስን በጦር ወግቶ ሲገድለው አየ። ሲነጋ ወደ ስዕሉ እጅ ለመንሳት ቢሄድ ብሉ ደም ፈስሶ አገኘ አንተ ቅዱስ ሰማዕት በውኑ ዑልያኖስን ገደልከውን? አለ ስዕሉ አንገቱን ዘንበል አድርጎለታል።

ዛሬም በሀገራችን በሰሜን ሸዋ አርማንያ ሲታወቅ ወረብ ሲዘምሩ የቅዱስ መርቆሬዎስ የፈረሱ ስዕል ይዘላል።

ትምህርት

- በእምነት እየፀናን ከክርስቶስ ፍቅር ማን ይለየናል ማለትን «ከክርስቶስ ፍቅር ማን ይለየናል» (ሮሜ 8፡35)
- ከሰዎች ሹመት ይልቅ ሰማያዊ ሹመት መፈለግ (ማቴ10፥28)

መልዕክት

ሰማዕቱ ቅዱስ መርቆሬዎስ ከማያምኑ ቤተሰብ ቢወለድም ቤተሰቦቹም በእርሱ መወለድ አመኑ ከዘመኑ ሥልጣን ይልቅ የእግዚአብሔር ልጅ መሆን መረጠ ከክርስቶስ ፍቅር ማንም አይለየኝ በማለት መከራ በሰማዕትነት በዚህ ዕለት አርፏል። የሰማዕቱ የቅዱስ መርቆሬዎስ ምርጫ እግዚአብሔር ነበር። የኛስ ምርጫ ምን ይሆን? ሥልጣን፣ ሹመት፣ የተመቻቸ ኑሮ፣ ወይስ እንደ ሰማዕቱ ቅዱስ መርቆሬዎስ ከክርስቶስ ፍቅር ማን ይለየናል ማለት? በዚህ ዓለም ስንኖር በዓለም ከንቱ ብልጭልጭ ነገር ተታለን ከአምላካችን እንዳንለይ አምላክ መርቆሬዎስ እግዚአብሔር ይርዳን። የሰማዕቱ የቅዱስ መርቆሬዎስ በረከት አይለየን አሜን።

የቅዳሴ ምንባባት

2ኛ ቆሮ.7፥4
1ኛ ጴጥ.4፥12
የሐዋ. 6፥11

ምስባክ፦ ልሳነ ከለባቲከ ላዕለ ጸላዕትከ
አስተርአየ ፍናዊከ እግዚኦ
ፍናዊሁ ለአምላክየ ለንጉሥየ ዘውስተ መቅደሱ መዝ.67፥23

- በቀርሜሎስ ተራራ መስዋዕት አቅርቦ እግዚአብሔር መስዋዕቱን ተቀብሎታል፤ ካህናተ ጣዖትንም አሸንፏል። (1ነገ.15፥6)

ትምህርት

- ስለ እውነት በነገሥታቱ ፊት መመስከር (1ነገ.20፥19)
- ለተጠራንበት ዓላማ መቆም (1ጴጥ.1፥15)
- ስለ እግዚአብሔር ክብር መቅናት «ለሠራዊት አምላክ ለእግዚአብሔር እጅግ ቀንቻለሁ» (1ነገ.19፥10)

መልእክት

ነቢዩ ኤልያስ ስለ እግዚአብሔር ክብር በመቅናት ናቡቴ በግፍ ተገደለ በማለት በአክዓብና በኤልዛቤል ፊት በመቆም እውነትን በመናገር መሰከረ። እኛስ በዘመናችን በነገሥታቱ ፊት ድሆች በግፍ ተገደሉ በማለት ድምጻችንን አሰምተን የምናውቅ ስንቶቻችን እንሆን? ነቢዩ ኤልያስ የሚያስተምረን ስለ እውነት መቆም ነውና እኛም ስለ እውነት እንድንቆም አምላካችን ይርዳን አሜን።

የቅዳሴ ምንባብ
ሮሜ 11፥16
ያዕ 5፥16
የሐዋ 3፥19

ምስባክ ፦ ወገሥጸ ነገሥተ በእንቲአሆሙ
እትገሥሡ መሲሓንየ
ወኢታሕሥሙ ዲበ ነቢያትየ /መዝ 104፥14/
ወንጌል ሉቃ 4፥25
ቅዳሴ /ጎሥዓ/

ታኅሣሥ ሦስት

በዓታ ለማርያም ውስተ ቤተ መቅደስ

እበውዕ ቤተከ ምስለ መባእየ

ስእለቴን ይዤ ወደ ቤትህ እገባለሁ

(መዝ 65፥13)

የእመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም አባቷ ኢያቄም እናቷ ሐና ይባላሉ። የተወለደችው በእግዚአብሔር ፈቃድ በብሥራተ መልአክ ነው። አባትና እናቷ እግዚአብሔርን ልጅ ብትሰጠን ብለው ተስለው ነበር ሦስት ዓመት ሲሆናት ኢያቄም ለሐና ይህች ልጅ አንድ ነገር ብትሆን ከእግዚአብሔር ከልጃችንም ሳንሆን እንዳንቀር ሆኗ ዘመድ ሳይወድ እሷ እህል ሳይለምድ ወስደን እንስጥ ብለው መባ ጨምረው ወደ ቤተ መቅደስ ይዘዋት ሄዱ ሊቀ ካህኑ ዘካርያስ ይባላል ደወል መትቶ ሕዝቡን ሰብስቦ የምግቧ ነገርስ? አለ ሊቀ መላእክት ቅዱስ ፋኑኤል ኅብስት ሰማያዊ ጽዋዕ ሰማያዊ ይዞ ረቦ ታየ። ዘካርያስም ለርሱ የመጣ መስሎት ከእርሱ ሊቀበል ተነሣ ወደ ሰማይም ራቀበት ከእርሱ ቀጥሎ ያለው ሊቀ ካህንም ሊቀበል ሲቀርብ ራቀበት። ካህናቱም ሕዝቡም በየተራ ቢቀርቡ ራቀባቸው ምን አልባት ለዚህች ብላቴና የመጣ እንደሆን እንይ አሉ። ሐናን ትተሻት እልፍ በይ አሏት። ትታት እልፍ አለች ድክድክ እያለች እናቷን ስትከተል መልአኩ ፈጥኖ ወርዶ አንድ ክንፉን እንጥፎ አንድ ክንፉን ጋርዶ በሰው ቁመት ልክ ከመሬት ከፍ አድርጎ መግቧት ዐረገ። ሊቀ ካህኑ ዘካርያስ

ታኅሣሥ አንድ

ልደቱ ለኤልያስ

የዕለቱ የትምህርት ርእስ

«እንደ እግዚአብሔርም ቃል አደረገ»

(1ነገ.17፥5)

በዚህ ዕለት ነቢዩ ኤልያስ የተወለደበት ዕለት ነው። አባቱ ኢያቤዝ እናቱ ቶና ይባላሉ። ሀገሩ ቴስቢያ ዘገለዓድ ነው ኤልያስ ማለት ፀ ዘይት ማለት ነው። ነቢዩ ኤልያስ ቀናኢ ከቀደምት ነቢያት ነው ።

ንጉሡ አክዓብና ንግሥቲቱ ኤልዛቤልን ስለ እውነት ብሎ የገሰጸ ስለ እግዚአብሔር ቀንቶ ሦስት ዓመት ከስድስት ወር ዝናብ እንዳይዘንብ በጸሎት እግዚአብሔርን ጠይቆ ዝናብ ሳይዘንብ ቀርቷል። (1ነገ.17፥17) ኤልዛቤል ልታስገድለው ስታስፈልገው የእግዚአብሔር መልአክ ሄድ አለው ተነስቶም በዮርዳኖስ ትይዩ ባለው በካራት ፋፋ ውስጥ ተሸሸገ ቁራዎችም የሚበሉውን ያመጡለት ነበር (1ነገ.17፥6)። እግዚአብሔር ተነስተህ በሲዶና አጠገብ ባለችው ወደ ሰራፕታ ሂድ አለው። በመበለቲቱ ቤት ሲገባ ቤቷን በበረከት ሞላው።

ካህናተ ጣዖቱን እንዳስፈጀ ኤልዛቤል ስትሰማ ነገ በእንዲህ እንዳንዱ ሳላደርገው ብላ ዛተች ከእግዚአብሔር የታዘዘ መልአክ ከኤልዛቤል ጋር ተጣልተህ እንዴት እዚህ ተቀምጠሃል አለው ተነስቶ ሲሄድ ደክሞት ከዛፍ ሥር ተኝቶ ሳለ የእግዚአብሔር መልአክ ቀስቅሶት ከሰማይ ኅብስት በእንግልግል ይዞ መቶ ቀስቅሰውና ተነስተህ ብላ አለው።

ሁለተኛም እንደዚሁ ለሦስተኛ ጊዜም ቀስቅሶ ብላ እስከ ትጸግብ እስመ ርሑቅ ፍኖትከ መንገድህ ሩቅ ነውና እስከትጠግብ ብላ አለው። ያንን በልቶ ሕመም ድካም ሳይሰማው 40 ቀን 40 ሌሊት ተጉዞ ደማስቆ ደረሰ የሣፋጥን ልጅ ኤልሳዕንም አገኘው። ተከተለኝ ሲለው በሬዎቹን አርዶ ሥጋቸውንም በበሬዎቹ እቃ ቀቅሎ ለሕዝቡም አብልቷቸው መስዋዕትም አቅርቦ ተከትሎታል። (1ኛ ነገ.14፥2)

በመጨረሻም ጊዜ ዕርገቱ ሲደርስ ደቀ መዝሙሩ ኤልሳዕን እግዚአብሔር ወደ ቤቴል ልኮኛል በዚህ ቆይ አለው። ኤልሳዕም መልሶ አልለይህም በማለት ተከትሎት ቤቴልም ሲደርሱ ወደ ኢያሪኮ እሔዳለሁ በዚህ ቆይ አለው። ከአንተ አልለይም አለው ተከትሎ ዮርዳኖስን በመጎናጸፊያው ከፍሎ ተሻገሩ ከአንተ ሳልለይ የምትሻውን ለምን አለው። ነቢዩ ኤልያስ በእሳት ሠረገላ በዚያ ሲያርግ አይቶ አባቴ ሆይ አለ ልብሱንም ከሁለት ተረተረው ከኤልያስም ያስቀረውን መጎናጸፊያ አንስቶ ወደ ዮርዳኖስ ወንዝ ሄደ። ውኃውን ቢመታው ለሁለት ተከፈለ፤ ኤልሳዕም ዮርዳኖስን ተሻገረ። (2ነገ.2፥14)

ነቢዩ ኤልያስ ተአምራት ያደርግ ነበር፤

- ለ42 ወራት ዝናብ እንዳይዘንብ አድርጓል
- በቁራዎች ተመግቧል (1ነገ.17፥17)
- የመበለቲቱን ቤት በበረከት ሞልቷል (1ነገ.17፥4)
- ከሰማይ እሳት አውርዷል (1ነገ.18፥30-32)
- የመበለቲቱን ልጅ ከሞት አስነሥቷል (1ነገ.17፥17)

የምግቧ ነገር ከተያዘ ብሎ ከመካከ ደናግል አስገብቷታል። ከመዝ ነበርኪ. ውስተ ቤተ መቅደስ ወመላእክት ያመጽኡ ወትረ ሲሳየኪ. 'ከመዝ ነበርኪ. ዐሥርተ ወክልኤተ ዓመተ እንዘ ትትናዘዚ እምኅበ መላእክት እንዳለ። ኅብስት ሰማያዊ ጽዋዕ ሰማያዊ እየተመገበች መላእክት እየጎበኟት 12 ዓመት በቤተ መቅደስ ኖረች።

ትምህርት

- ኢያቄምና ሐና ስእለታቸውና ልመናቸው መሰማቱን «እግዚአብሔር የልመናዬን ድምፅ ሰምቶአልና ወደድኩት» (መዝ114፥1)
- ስእለትን ማክበር

ተስለህ የማትፈጽም ብትሆን ባትሳል ይሻላል። (መክ.5፥5)

መልእክት

የሰው ልጆችን ልመና የሚያስቀር አምላክ የኢያቄምንና የሐናን ጸሎት ሰምቶ የሰጣቸውን አንዲት ልጅ ነቢያት በብዙ ምሳሌ ትንቢት የተናገሩላትን እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያምን በገቡት ቃል ኪዳን መሠረት ለልጃቸው ሳይሳሱ በሦስት ዓመቷ ወደ ቤተ መቅደስ ይዘዋት ሔዱ። እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ሐርና ወርቅ እየፈተለች ሰማያዊ መና እየተመገበች በንጽሕና በቅድስና ኖረች። በዚህ ዘመን የምንኖር እኛም እግዚአብሔርን በጸሎት መጠየቅ ዘወትር ከመቅደሱ ሳንለይና በንጽሕና በቅድስና እንድንኖር የእናታችን የቅድስት ድንግል ማርያም አማላጅነትና ጸሎት አይለየን አሜን።

የቅዳሴ ምንባብ

ዕብ 9፥1

2ኛ ጴጥ 1፥5

የሐዋ 1፥12

ምስባክ ፦ ስምዒ ወለትየ ወርእዪ ወአጽምዒ እዝነኪ
ርሥዒ ሕዝበኪ ወቤተ አቡኪ
እስመ ፈተወ ንጉሥ ሥነኪ /መዝ 44፥10/

ወንጌል ሉቃ 1፥39-57

ቅዳሴ /ጎሥዓ/

ታኅሣሥ ዐሥራ ዘጠኝ

ቅዱስ ገብርኤል ዘአድኃኖሙ ለሠለስቱ ደቂቅ እም እቶነ እሳት

የዕለቱ የትምህርት ርእስ

መኑ ዘያድኅነክሙ እም እዴየ

« ከእጄስ የሚያድናችሁ ማን ነው?»

(ት፡ዳን 3፥16)

ገብርኤል ማለት እግዚእ ወገብር ማለት ነው። ሰይጣን መላእክትን እኔ ፈጠርኳችሁ ብሎ በተናገረ ጊዜ «ንቁም በበኅላዌነ እስከ ንረክቦ ለአምላክነ» ፈጣሪያችንን እስክናገኝ ድረስ፣ በያለንበት ጸንተን እንቁም

በማለት በመላእክት ዓለም መረጋጋት እንዲኖር ያደረገ ኃያል መልአክ ነው።

ከእግዚአብሔር እየተላከ በብሉይ ኪዳንና በሐዲስ ኪዳን የሰው ልጆችን እየተራዳና እያገዘ በአማላጅነቱ የሚያምኑትን የሚረዳና የሚታደግ መልአክ ነው።

ወደ እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ተልኮ የእግዚአብሔር አብ የባሕርይ ልጅን እንደምትወልድ ያበሠረ መልአክ ነው። በዚህ ዕለት ደግሞ ከእስራኤል አገር ናቡከደነፆር ማርኮ ወደ ባቢሎን ከወሰዳቸው መካከል አናንያ፣ አዛርያና ሚሳኤል የተባሉ ንጉሡ በባቢሎን አውራጃዎች ሹሟቸው ነበር።

ንጉሡም 60 ክንድ ቁመት ያለው 6 ክንድ ያህል ስፋት ያለው የወርቅ ምስል አሰርቶ በዱራ ሜዳ ላይ አቁሞ ለዚህ ያልሰገደ ሁሉ ይቀጣል ብሎ አዋጅ አሳወጀ። ሁሉም የመለከቱንና የእንቢልታውን፣ የመሰንቆውን፣ የክራሩን፣ የበገናና የዋሽንቱን የዜማውንም ሁሉ ድምፅ በሰማችሁ ጊዜ ተደፍታችሁ ንጉሡ ናቡከደነፆር ላቆመው ለወርቁ ምስል እንድትሰግዱ ታዝዛችኋል። ተደፍቶም የማይሰግድ በዚያን ጊዜ በሚነድድ እሳት ውስጥ ይጣላል አለ። ሁሉም ሰገዱ።

አናንያ፣ አዛርያና ሚሳኤል ግን አንተ ላቆምከው ምስል አንሰግድም አሉ። ንጉሡም የፊቱ መልክ ተለወጠባቸው በእቶኑ እሳት ይነድ ከነበረው ሰባት እጥፍ አድርገው እንዲያነዱት ከሠራዊቱ ውስጥ ከነበሩት ኃያላን አዘዘ። እያሰሩ በሚነደው እሳት ውስጥ ሲጨምሯቸው የእሳቱ ወላፈን የሚጨምሯቸውን ሰዎች ከነዲዱ ብዛት የተነሳ ገደላቸው።

ከዚህ በኋላ ንጉሡ ሦስት ሰዎች በእሳት ውስጥ ጨምረን አልነበረምን?አለ አማካሪዎቹም እውነት ነው ብለው ለንጉሡ መለሱለት እነሆ የተፈቱ በእሳት መካከል የሚመላለሱ አራት ሰዎች አያለሁ ምንም አላቆሰላቸውም። የአራተኛውም መልክ የአማልክትን ልጅ ይመስላል።

ንጉሡም ናቡከደነፆር እናንተ የልዑል አምላክ ባሪያዎች ሲድራቅ ሚሳቅ አብድናጎ ከእሳቱ መካከል ውጡ ብሎ ተናገራቸው።

ትምህርት

- ፍጹም እምነትን
  «የምናመልከው አምላካችን ከእሳቱ እቶን ያድነን ዘንድ ይችላል ባያድነንም እንኳን አንተ ላቆምከው ምስል አንሰግድም» (ዳን.3+17)
- ጽናትን
  «ያለህን አጽንተህ ያዝ» (ራዕ.3+11)

መልእክት

ሦስቱ ወጣቶች በእምነት በመጽናታቸው ንጉሡ ላቆመው የወርቅ ምስል ሁሉም ሲሰግድ አንሰግድም በማለታቸው በሚነድ እሳት ውስጥ ተጨመሩ እምነታቸውና ጽናታቸው አዳናቸው እኛም ዛሬ የምንማረው ፍጹም እምነትና ጽናት እንዲኖረንና ለጣዖትም እንዳንሰግድ ከሦስቱ ወጣቶች ሕይወት ልንማር ይገባናል። መልአኩ ቅዱስ ገብርኤል ከእግዚአብሔር ተልኮ እንዳዳናቸው እኛም በመንገዳችን፣ በሥራችን ሁሉ ከሚነደው የእሳት ወላፈን በአማላጅነቱ ይጠብቀን። አሜን።

የቅዳሴ ምንባብ

2ተሰ 1፥6
ይሁዳ 1፥20
የሐዋ 7፥30
ምስባክ ፦ ብቅድመ መላእክቲሁ እዜምር ለከ
ወእሰግድ ውስተ ጽርሐ መቅደስከ
ወእገኒ ለስምከ /መዝ 137፥1/
ወንጌል ሉቃ 1፥11
ቅዳሴ /ጐሥዐ/

ማደሪያውም ትሆነው ዘንድ ወዷልና እንዲህም ብሎ ይህቺ ለዘላለም ማረፊያ ናት» (መዝ131+13)

- ርህራሄን
  ለተጠማ ውሻ ማጠጣቷ
- ትህትናን
  «እንደ ቃልህ ይሁንልኝ እኔ ለእግዚአብሔር ባሪያው ነኝ» (ሉቃ1+38)

መልእክት

እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም መመረጧ ለአምላክ ማደሪያነት ነው። በዚያን ዘመን ብዙ ሰዎች ልጆቻቸውን ክርስቶስ ከእኛ ዘር እንዲወለድ እያሉ ሴት ልጆቻቸውን በድንግልና ያሳድጉ ነበር ነገር ግን እግዚአብሔር በሁለት ወገን ድንግል የሆነች እመቤታችንን ለማደሪያነት መረጣት፣ ምክንያቱም የሌሎቹ ሴቶች ድንግልና የሥጋ ብቻ ስለነበር ነው።

የእመቤታችን አማላጅነት አይለየን አሜን ።

የቅዳሴ ምንባባት
2ኛ ጢሞ 1+8
1ኛ ዮሐ 4+9
የሐዋ 12+7
ስብክ ፦ ሀይንተ አበዊኪ ትወልዱ ለኪ ደቂቅ
ወትሰይሚዮሙ መላእክተ ለኩሉ ምድር
ወይዘክሩ ስመኪ በኩሉ ትውልደ ትውልድ (መዝ 44+16)
ወንጌል (ሉቃ 1 +39)

ማሳሰቢያ ፦ ታሪኩ የተፈጸመው መጋቢት 29 ነው።

ታኅሣሥ ሃያ አራት
ልደቱ ለአቡነ ተክለሃይማኖት

የዕለቱ የትምህርት ርእስ

የቅኖች ትውልድ ትባረካለች

(መዝ 111+2)

የጻድቁ ተክለሃይማኖት አባታቸው ጸጋ ዘአብ እናታቸው እግዚእ ኃረያ ይባላሉ። ተክለሃይማኖት ማለት ተክለ አብ ተክለ ወልድ ተክለ መንፈስ ቅዱስ ማለት ነው አባትና እናታቸው ልጅ አጥተው ሲያዝኑ ይኖሩ ነበር መጋቢት 23 ቀን ለ24 አጥቢያ አባታችን ተክለ ሃይማኖት ተጸነሱ። በዚህ ዕለት ታኅሣሥ 24 ተወለዱ።

ትምህርት

- ቅንነት
  «እግዚአብሔርን መፍራት ወደ ሕይወት ይመራል» (ምሳ19፥23)
- ተስፋ አለመቁረጥ (ዕንባ 3+16)
- የእግዚአብሔርን ጊዜ መጠበቅ (ምሳ.27+18)

ታኅሣሥ ሃያ ሁለት
በዓለ ብሥራት

የዕለቱ የትምህርት ርእስ
ይኩነኒ በከመ ትቤለኒ
«እንደ ቃልህ ይሁንልኝ»

(ሉቃ 1+38)

እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም አሥራ አምስት ዓመት ሲሆናት አይሁድ ተመቅኝተው ሊቀ ካህኑ ዘካርያስን «ናሁ ወርዘወት ወለተ እስራኤል፤ ይቺ ብላቴና ቆነጃጅ እሷን ሲሉ ጎርምሶች ቤተመቅደሳችን እንዳያረክሱብን ትውጣልን» አሉት። ዘካርያስ ንብቱ እንደምን ትሆኚ አላት ከእግዚአብሔር በታች ያለህ አባቴም እናቴም አንተ ነህ አንተ ወደ እግዚአብሔር አመልክትልኝ እንጂ እኔ ምን አውቃለሁ አለቻቸው። ወደ እግዚአብሔር ቢያመለክት ከነገደ ይሁዳ ሚስቶቻቸው የሞቱባቸውን አስቆጥረህ በትራቸውን ሰብስበህ በቀዳማይ ሰዓተ ሌሊት ከቤተ መቅደስ አስገብተህ በቀዳማይ ሰዓተ መዓልት አውጣው ምልክት አሳይሃለሁ አለው። 1985 በትር ሰበሰበ በቀዳማይ ሰዓተ መዓልት ቢያወጣው የዮሴፍ በትር ለምልማ ተገኘች በበትሩም ላይ «ኦ ዮሴፍ ዕቀባ ለማርያም ፍህርትከ ለማርያም፤ ዮሴፍ ሆይ እጮኛህ ማርያምን ጠብቃት» የሚል ጽሑፍ ተገኝቷል። እጣም ቢጣጣሉ ለዮሴፍ ደረሰቸው ርግብም መጥታ በራሱ ላይ አረፈችበት። ዮሴፍም ወደ ቤቱ ወሰዳት።

እመቤታችንም በእጭር ታጥቃ ማድጋዋን ነጥቃ ውኃ ልትቀዳ ሄደች። ቀድታ ስትነሣ የተጠማ ውሻ እያለከለከ መጣ በዚያ የነበሩ ሴቶች ሲያባርሩት እመቤታችን ግን ምንው ፍጡር አይደለም። አያሳዝናችሁምን? አለቻቸው። አንቺ አለባለሽም የሥራ ፊት ይመስላል አንቺ አጠጪው አሏት። በወርቅ ጫማዋ አድርጋ አጠጥታዋለች ሴቶቹም ዘብቀባት ያጎደለችውም ውኃ በተአምራት ሞልቶላታል ስትመለስ ቅዱስ ገብርኤል

«ትጸንሲ» አላት ዘር ብትል አማችው አባቱ አዳምንና እናቱ ሔዋንን ያሳታቸው ጠላት ይሆናል ብላ ዝም ብላ ሄደች ከቤት ደርሳ ማድጋዋን ስታስቀምጥ ዳግመኛ «ትጸንሲ» አላት። ይህ ነገር ደጋግመኝ እንዲህ ያለውን ነገር ቤተመቅደስ ሄጄ ልረዳ ብላ ወደ ቤተ መቅደስ ሄዳ ወርቅና ሐር እያስማማች ስትፈትል ቅዱስ ገብርኤል ተገልጦ "ጸጋን የተሞላሽ ሆይ ደስ ይበልሽ በእግዚአብሔር ዘንድ ባለሟልነትን አግኝተሻልና አትፈሪ እነሆ ትጸንሻለሽ ወንድ ልጅም ትወልጃለሽ ስሙንም ኢየሱስ ትይዋለሽ (ሉቃ.1+31)አላት ማርያምም መልአኩን ምድር ያለ ዘር ዕፀን ታበቅል ዘንድ ሴትም ያለ ወንድ ዘርን ታስገኝ ዘንድ እንዴት ይቻላል? ወንድ ስለማላውቅ ይህ እንዴት ይሆናል? አለችው። መልአኩም «መንፈስ ቅዱስ ይጠብቅሻል የልዑል ኃይልም ያድርብሻል ስለዚህም ደግሞ ከአንቺ የሚወለደው ቅዱሱ የእግዚአብሔር ልጅ ይባላል። እነሆም ዘመድሽ ኤልሳቤጥ እርስዋም ካረጀች ከሸመገለች በኋላ ወንድ ልጅ ጸንሳለች እርሷም መካን ትባል ለነበረችው ይህ ስድስተኛው ወር ነው ለእግዚአብሔር የሚሳነው ነገር የለምና» አላት እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያምም «እንደ ቃልህ ይሁንልኝ እኔ ለእግዚአብሔር ባሪያው ነኝ» አለችው። ይህን ቃሏን ምክንያት አድርጎ ወልድ ዋሕድ ኢየሱስ ክርስቶስ በማኅፀኗ አደረ። መልአኩ ቅዱስ ገብርኤል እመቤታችንን ያበሠራት መጋቢት 29 ቀን ነው። በዚሁ ዕለት እንዲከበር የሆነበት ምክንያት የጥምቀትያው ኢሊስ ቀዳስ ቅዱስ ደቅስዮስ ስለዘዘ ነው። እመቤታችንን በፍጹም ልብ ይወዳት ስለ ነበር ከመወደዱ የተነሳ ብዙ አንክተ ቀለም በጥብጦ ብራና ጣምጦ ዕለት ዕለት ተአምሯን ይጽፍ ነበር። እመቤታችንም ተገልጣ ዛሬ ይህንን በዓል በማክበርህ ተአምሬንም በመጻፍህ ብላ የሚለብሰው ልብስና የወርቅ ወንበር ማንም የማይቀመጥበት ሰጥታዋለች።

ትምህርት

- የእመቤታችን የቅድስት ድንግል ማርያም መመረጥ
  «አሕመ ኃረያ እግዚአብሔር ለጽዮን ወአብደራ ከመ ትኩኖ ማኀደር ዛቲ ይእቲ ምዕራፍየ ለዓለም፤ እግዚአብሔር ጽዮንን መርጧታልና፤

መልእክት

እግዚአብሔርን የፈሩና ያከበሩ ጸጋ ዘአብና እግዚእ ኃረያ ተስፋ ሳይቆርጡ በቅድስና በንጽሕና ኖረው ጻድቅና ደግ ልጅ የኢትዮጵያን ሐዋርያ በዛሬው ዕለት ወለዱ።

እኛስ በዘመናችን ደግ፣ ተስፋ የማንቆርጥ የእግዚአብሔርን ጊዜ የምንጠብቅ ሰንቶች ነን ....?

የቅዳሴ ምንባብ

ኤፌ 4፥11

1ዮ 1፥13

የሐዋ 19፥11

ምስባክ ፦ እምአፈ ደቂቅ ወሕፃናት አስተዳሎከ ስብሐተ
በእንተ ጸላኢ
ከመ ትንሥቶ ለጸላኢ ወለገፋዒ /መዝ 8፥2/
ወንጌል ማቴ 18+1
ቅዳሴ ዘሐዋርያት

ታኅሣሥ ሃያ ስምንት እና ሃያ ዘጠኝ
ልደቱ ለእግዚእነ (ገና)

የዕለቱ የትምህርት ርእስ

«ዛሬ በዳዊት ከተማ መድኃኒት... ተወልዶላችኋል»

(ሉቃ 2+11)

እግዚአብሔር አምላክ ዓለምንና በውስጧ ያሉትን ሁሉ ፈጠረ (ዘፍ.1+1) ሌሎች ፍጥረታት ለአንክሮ ለተዘክሮ ሲፈጠሩ ሰውና መላእክት ግን ፍቅሩን ክብሩን ይወርሱ ዘንድ ተፈጠሩ። የሰው ልጅን /አዳምን/ፈጥሮ የሚያስፈልገውን አዘጋጅቶ፣ዕውቀትንና ሥልጣን ሰጥቶ፣ በጸጋ አምላክነትን ሸሞ፣ መመሪያ ሰጥቶ፣ በክብር እንዲኖር ፈቀደለት። ዲያብሎስ አምላክነት በመሻቱ ተዋርዶ ሳለ አዳምንም በተዋረደበት ምቀኝነት ፍላጎት እንዲወድቅ ክብሩን እንዲያጣ ከአምላኩም እንዲለይ አደረገው። እግዚአብሔርን፣ ጸጋውን፣ ሹመቱን አጣ።

አዳም ከእግዚአብሔር በመለየቱና ክብሩን በማጣቱ ተጸጽቶ ንስሐ በመግባቱ ለሥርየተ ኃጢአት የሚሆን መስዋዕትም በማቅረቡ፣እግዚአብሔር አምላክ ልመናውንና መስዋዕቱን ተቀብሎ እርሱንና ዘሩን ለማዳን እንደሚመጣ ቃል ኪዳን ገባለት "መልዓትንና ሌሊትን ዓመታትን በዚህ ምድር ላይ ሠራሁልህ፡፡ይኸውም እነርሱ እስኪፈጸሙ ድረስ በምድር ላይ ትኖርና ትመላለስ ዘንድ ነው።

የፈጠረችህና የተላለፍኸት ከንት ያወጣችህና በወደቅህም ጊዜ የምታነሳህ ዳግመኛም አምስት ቀን ተኩል ሲፈጸም የምታድንህ ቃሌን እልክልሃለሁ"

ብሎ እግዚአብሔር ለአዳም ነገረው አዳምም አምስት ቀን ተኩል የሚለውን ቃል ከእግዚአብሔር በሰማ ጊዜ የእነዚህን ታላላቅ ነገሮች ትርጓሜ ሊያስተውል አልቻለም። ስለዚህም እግዚአብሔር አምስት ቀን ተኩል ማለት አምስት ሺህ አምስት መቶ ዓመታት መሆናቸውን ገልጾ አርአያውና አምሳያው ለሆነው ለአዳም በቸርነቱ ተረጎመለት ያንጊዜ እርሱንና ዘሩን ለማዳን እንደሚመጣ ተስፋ ሰጠው።

አዳምም ይህንን ተስፋ ለልጆቹ አስተማራቸው ልጆቹም ተስፋው የሚፈጸምበትን ጊዜ ለማወቅ በፀሐይ፣ በጨረቃና በከዋክብት ዘመናትን እየቆጠሩ ከልጅ ልጅህ ተወልጄ አድንሃለሁ ያለውን አዳኝ ጌታ መወለድ በትንቢታቸው ይናገሩ ይጠብቁም ነበር። ከእነርሱም ውስጥ:-

◆ ሱባኤ ሔኖክ

ሔኖክ ሱባኤውን ሲቆጥር የነበረው በአበው ትውልድ ሲሆን ሰባቱን መቶ ዓመት አንድ እያለ ቆጥሯል። በስምንተኛው ሱባኤ ኢየሱስ ክርስቶስ እንደሚወለድ ትንቢት ተናግሯል። አቆጣጠሩም ከአዳም ጀምሮ ነው።

ትንቢቱም እንዲህ ይላል። "በስምንተኛይቱ ሰንበት ጽድቅና ኩነኔ የሚታወቅባት ሱባኤ ናት። ሰይፍም ለርሱዋ ይሰጣታል ታላቁ ንጉሥ የሚመሰገንበት ቤትም በርሱዋ ይሰራል። ምሥጋናውም ዘላለማዊ ነው።" (ሔኖክ 35+1-2 ክፍል 91) በማለት ሲተነብይ መተርጉማን እንዲህ ይመልሱታል ለርሱዋ ሰይፍ ይሰጣታል ማለቱ ጽድቅና ኩነኔ የሚታወቅበት ወንጌል ያን ጊዜ በዓለም ሁሉ ትሰበካለች ማለት ነው። የታላቁን ንጉሥ ቤት ይሠራል ማለቱ የነገሥታት ንጉሥ ኢየሱስ ክርስቶስ የሚመሰገንበት ቤተክርስቲያን ትሠራለች ማለት ነው። ምስጋናውም ዘላለማዊ ነው ማለቱ ሰውና መላእክት በአንድነት ሆነው "ስብሐት ለእግዚአብሔር በሰማያት ወሰላም በምድር" እያሉ ዘወትር ያመሰግናሉ ማለት ሲሆን ስምንተኛይቱ ሰንበት ለክርስቲያኖች የተሰጠችበትን ዕለት ልደተ ክርስቶስ ናት ይሏታል።

◆ ሱባኤ ዳንኤል

ስለ ጌታችን ሰው መሆን ጊዜ ወስኖ ሱባኤ ቆጥሮ የተናገረው ዳንኤል ነው። የዳንኤል ሱባኤ የሚቆጠረው በዓመት ነው። ዳንኤል ሰባው ዘመን በተፈጸመ ጊዜ እንግዛችኋለሁ ተብሎ በኤርምያስ የተነገረውን ትንቢት እያስታወሰ ሲጸልይ መልአኩ ቅዱስ ገብርኤል በሰው አምሳል ተገልጾ እንዲህ ብሎታል። "እግዚአብሔር ልመናህን ሰምቶሃልና እነግርህ ዘንድ መጥቻለሁ። አሁንም ነገሩን መርምር ራእዩንም አስተውል ኃጢአት የሚሰረይበትን ቅዱሰ ቅዱሳን ጌታም የባሕርይ ክብሩን ገንዘብ የሚያደርግበት ዓለው ሰባው ሲደርስ ሲፈጸም ነው ብለህ ወገኖችህን ቅጠራቸው ብሎታል።" (ዳን.9+22-25፣ኤር.29+10)

ሰባ ሱባኤ አራት መቶ ዘጠና ዓመት ነው (70X7= 490) ይህ ጊዜ ከሚጠት እስከ ክርስቶስ መምጣት ያለው ጊዜ ነው (ትርጓሜ ሕዝ.4+6)

◆ ሱባኤ ኤርምያስ

ኤርምያስ ከባቢሎን እንደተመለሰ በፈረሰው ቤተ መቅደስ ውስጥ ሆኖ ሲጸልይ ሳለ ራእይ አየ በሦስተኛው ቀንም እንዲህ ብሎ ትንቢት ተናገረ። "ፈጣሪያችንን በአንድ ቃል አመስግኑ የአብ የባሕርይ ልጅ ኢየሱስ ክርስቶስን አመስግኑ ከዚህ በኋላ ሰው ሊሆን ሥጋ ሊለብስ ወደዚህ ዓለም ሊመጣ የቀረው 333 ሱባኤ ዕለት ነውና እርሱ ወደዚህ ዓለም ይመጣል ዐሥራ ሁለት ሐዋርያትንም ይመርጣል...።" (ተረፈ ኤር.11፣37፣38፣42-48 ኤርምያስ ሱባኤውን የጀመረበትን ትንቢቱን የተናገረበት ራእዩን ያየበት

ምክንያት ከልባችን ያወጣነውን የሁላችንንም አምላክ ዛሬም በልባችን እንዲወለድ ያስፈልጋል።

የቅዳሴ ምንባብ

ሮሜ 8፡3
1ዮሐ 4፡1
የሐዋ 3፡22
ምስባክ፦ የሐዩ ወይሁብዎ እምወርቀ ዓረብ
ወዘልፈ ይጼልዩ በእንቲአሁ
ወኩሎ አሚረ ይድኀርዎ /መዝ 71፡15/
ወንጌል ሉቃ 2+1-21
ቅዳሴ /ጎርጎርዮስ/ ኅልአ

ጥር አንድ
ዕረፍቱ ለቅዱስ እስጢፋኖስ

የዕለቱ የትምህርት ርእስ
ይህንን ኃጢአት አትቁጠርባቸው

(ሐዋ.7+60)

እስጢፋኖስ ማለት አክሊል ማለት ነው። ሐዋርያት መንፈስ ቅዱስን ከተቀበሉ በኋላ በኢየሩሳሌም ሲያስተምሩ ጊዜ ቢያንሳቸው ለተልዕኮ ማዕድ ሰባት ዲያቆናትን መርጠዋል። ከነዚህ በቀዳሚነት የተመረጠው እስጢፋኖስ ነው። (ሐዋ.6+15)

ጸጋ ሰማያዊ ኃይል መንፈሳዊ ተሰጥቶት ተግቶ ሲያስተምር አይሁድ በምቀኝነት ተነሳስተው እግዚአብሔርን ሲሰድብ ሙሴን ሲያቃልል ሰማነው ኦሪትንም ይሽራል ብለው ከሸንጎ ፊት አቆሙት ሊቃነ ካህናቱ ሰምን እንዲህ አደረግህ አለው። እናንተ ልበ ደንዳኖች ዘወትር መንፈስ ቅዱስን ስትቃወሙ ትኖራላችሁ። አባቶቻችሁ ነቢያትን እንዳሳደዱ እናንተም ጌታን ጠልታችሁ ሰቀላችሁት አላቸው አይሁድም ይህንን በሰሙ ጊዜ በልባቸው በጣም ተቆጡ ጥርሳቸውንም አፋጩበት። በመንፈስ ቅዱስም ተሞልቶ ወደ ሰማይ ትኩር ብሎ ሲመለከት የእግዚአብሔርን ክብር ኢየሱስንም በእግዚአብሔር ቀኝ ቆሞ አየሁ አለ (ሐዋ.7+56)

ከከተማ ወደ ውጭ አውጥተው በድንጋይ ደብድበው ገደሉት በዚሁ ዕለት አርፏል።

ትምህርት

- ለጠራን ለእግዚአብሔር ታማኝ መሆን
  «በኔ ተማምኗልና አስጥለዋለሁ ስሜንም አውቋልና እጋርደዋለሁ» (መዝ.90+14)
- በንጽሕና እግዚአብሔርን ማገልገል
  «ልበ ንጹሖች ብፁዓን ናቸው እግዚአብሔርን ያዩታልና» (ማቴ.5+8)

መልእክት

ሰማዕቱ ቅዱስ እስጢፋኖስ በመንፈስ ቅዱስ ተሞልቶ ሲያስተምር አይሁድ ተመቅኝተው በግፍ ቢገድሉትም ባለማወቃቸው ስለሠሩት ሥራ ምሕረትን ለምኖላቸዋል ዛሬ በአገልግሎታችን እንደ ቅዱስ እስጢፋኖስ በመንፈስ ቅዱስ ተሞልተን ይሆን? የምናገለግል ወይስ በሥጋ መንፈስ ተሞልተን? የቅዱስ እስጢፋኖስ ምልጃ አይለየን አሜን።

ዘመን ዓለም በተፈጠረ በ5 ሺህ 54 ዓመት ነው። ስለዚህ ትንቢቱ ከተነገረበት እስከ ክርስቶስ ልደት ያለው ጊዜ 446 ዓመት ነው።

ይኸውም በኤርምያስ ሱባኤ አንዱ 490 ዕለት ነው
መላው ሱባኤ 490X333 = 163,170 ዕለት ሲሆን
ወደ ዓመት ሲለወጥ 163, 170÷365 =446 ዓመት
ኤርምያስ ሱባኤውን መቁጠር የጀመረበት ዘመን...5054 ዓመት ዓለም
ትንቢቱ ከተነገረበት ዓመት እስከ ክርስቶስ ልደት 446 ዓመት
በተነገረው ትንቢት በተቆጠረው ሱባኤ መሠረት 5500 ዓመት ሲፈጸም ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ መወለዱ በዚህ ይታወቃል።

- ዓመተ ዓለም የቤተ ክርስቲያን ሊቃውንት በእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱሳት መጻሕፍትን መርምረው ሱባኤያትንና ሰንበታትን አውቀው ከአዳም እስከ ክርስቶስ ያለውን ዘመን ቁጥር 5500 ዓመት መሆኑን አረጋግጠዋል።

ይኸውም

- ከአዳም እስከ ኖኅ ...... 2256 ዓመት
- ከኖኅ እስከ ሙሴ .... 1588 ዓመት
- ከሙሴ እስከ ሰሎሞን..... 593 ዓመት
- ከሰሎሞን እስከ ክርስቶስ 1063 ዓመት

በአጠቃላይ 5500 ዓመት ይሆናል

ትምህርት

- የምሕረት ዓመት መታወጁ
- የምስጋና ዕለት መሆኑ

(ሉቃ.2+14)

- የነቢያት ትንቢት መፈጸሙ
  (ሚክ. 5+21)
- የማይመረመር አምላክ በሥጋ መገለጡ
  (ሉቃ.2+7)
- የመላእክት ምስጋና በቤተልሔም መሰማቱ
  (ሉቃ.2+14)

መልእክት

እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያምና አረጋዊ ዮሴፍ ለመቆጠር፣
ቅዱሳን መላእክት ለምስጋና
እረኞች የተወለደውን መድኃኒት ለማየት
የግብፅ ሰዎች (ሰብአ ሰገል) ቁባፂና መንፈሳዊ ስጦታን ይዘው
የሄሮድስ ወታደሮች ለመግደል
እኛስ ለምን ይሆን የምንመጣው?..........

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በተነገረው ትንቢት በተቆጠረው ሱባኤ መሠረት 1ዓመት ኩነኔ 1ዓመት ፍዳ) አምስት ቀን ተኩል (5500 ዓመት) ሲፈጸም (በእግዚአብሔር ዘንድ 1000 ቀን እንደ አንድ ቀን ናት። 2ኛ ጴጥ.3+8) በ5501 ዓመት ማክሰኞ ታኅሣሥ 29 ቀን ተወለደ። "ስብሐት ለእግዚአብሔር በሰማያት ሥምረቱ ለሰብእ" አምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስ የዘመኑ ፍጻሜ (የገባው ቃል ኪዳን! የተነገረው ትንቢት! የተቆጠረው ሱባዔ) ሲደርስ ከእመቤታችን ቅድስት ቅዱሳን ድንግል ማርያም የተወለደው ያጣነውን ልጅነት ሊመልስልን! ከተቀማነው ርስት ሊያስገባን! የገባንበትን እዳ ሊከፍልልን እንደሆነ ሁሉ በየዓመቱ የአምላካችንን የኢየሱስ ክርስቶስን የልደት በዓል ስናከብር ፍቅሩን እያሰብን በኃጢያታችን

የቅዳሴ ምንባብ

ዕብ 11፡32
1ዕ 4፡12
የሐዋ 7፡51
ምስባክ፦ እስመ በጺሖ በበረከት ሠናይ
ወአንበርከ አክሊለ ዲበ ርእሱ ዘእምእንቍ ክቡር
ሐተወ ሰአለከ ወሀብከ /መዝ 20፡3/
ወንጌል ማቴ 21፡33
ቅዳሴ ዘወልደ ነጐድጓድ

ጥር ስድስት
ግዝረት

የዕለቱ የትምህርት ርእስ

የማይመረመር አምላክ በሥጋ ተገለጠ

(ሉቃ.2+21)

ግዝረት ማለት መገረዝ ማለት ነው። ግዝረት የተጀመረው በአባታችን በአብርሃም ነው። (ዘፍ.17+9)። በዘመኑ ብሉይ አማንያን ከአሕዛብ የሚለዩበት ነበር። በአዲስ ኪዳን ግን በግዝረት ፈንታ ጥምቀት ተተክቷል። አምላካችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሕገ ኦሪትን ሊሽር አልመጣም። (ማቴ.3+17) ከእመቤታችን ከቅድስት ድንግል ማርያም ተወልዶ በ8ተኛው ቀን እንደ ኦሪቱ ሕግ ወደ ቤተ ግዝረት ሄዷል። በመንፈስ ቅዱስም ተገዝሮ ስለተገኘ ደሙ አልፈሰሰም።

ትምህርት

◆ ሕገ ሰጭው ሕግን በመፈጸሙ አርአያ መሆኑን

መልእክት

የማይታየው አምላክ በሚታይ ሥጋ ተገልጦ አርአያና ቤዛ ሆኖናል። ይህንን ውለታ በማሰብ ትእዛዙን በማክበር ልንኖር ይገባል።

ጥር ሰባት ቅድስት ሥላሴ

የዕለቱ የትምህርት ርእስ
ባቢሎን

(ዘፍ.11+9)

ባቢሎን ማለት ድብልቅልቁ የወጣ ማለት ነው፤ ከማየ አይኅ በኋላ ናምሩድ በተባለ አለቃቸው ከምሥራቅ ተነስተው በሄዱ ጊዜ በሰናዖር ምድር አንድ ሜዳ አገኙ። በዚያም ተቀመጡ ርእስ በርሳቸውም ኑ ጡብ እንሥራ በእሳትም እንተኩሰው ታላቅ ግንብ ሠሩ ሞትን የሚያመጡብን ሥላሴ ናቸው ብለው በሠሩት ግንብ ላይ ሆነው ጦር እየሰበቁ ይወረውሩ ጀመር። «ንዑ ንረድ ወንከዐው ሕንባሆሙ ወንዘርዝር ነገሮሙ ለከሳውያን፣ ኑ እንውረድ አንዱ ያንዱን ነገር እንዳይሰማው ቋንቋቸውን እንደበላልቅባቸው» (ዘፍ.11+9)

ትምህርት

- የባቢሎን ሰዎች እግዚአብሔርን ባለመፍራታቸው ምክንያት ቋንቋቸው ተደበላለቀ
- ምድራዊ ዝናና ክብር በመፈለጋቸው ጠፍተዋል።

መልእክት

የባቢሎን ሰዎች በአለታቸው በናምሩድ አማካኝነት በምድር ላይ ሳንበተን ስማችንን እናስጠራው በማለት በድፍረት ተነሱ ሕንፃቸው ፈራረሰ። ለመጀመሪያ ጊዜም የሰው ልጅ ቋንቋ በምድር ላይ ተደበላለቀ።

እኛስ በምንኖርበት ዓለም ምን እየሠራን ይሆን? ለገና? ለክብር? ስማችንን በሰዎች ከፍብሎ እንዲጠራ ነው የምንፈልገው? ዛሬ ላይ ያለው ዓለም የቋንቋ መደበላለቅ የባቢሎን ሰዎች በኃጢአታቸው የፈጠሩት ውጤት ነው።

ባቢሎን በዓለማችን፣ በአገራችን፣ በቤተ ክርስቲያናችን፣ በመንደራችን፣ በቤታችን እና ሁላችንም በባቢሎን ዓለም ውስጥ ብንኖርም ከክፉ አሰራር ግን ልንለይ ይገባል። አምላካችን እግዚአብሔር ይርዳን አሜን።

የቅዳሴ ምንባብ

ቆላስ 2፡10

1ዮሐ 2፡25

የሐዋ 22፡17

ምስባክ፦ የሐዩ ወይሁብም እምወርቀ ዐረብ

ወዘለፈ ይጼልዩ በእንቲአሁ

ወኩሉ እሚረ ይድኀርም /መዝ 71፡15/

ወንጌል ማቴ 2፡21

ቅዳሴ /ዘእግዚእ/

ጥር ዐሥራ አንድ ጥምቀት

የዕለቱ የትምህርት ርእስ

"ጽድቅን ሁሉ መፈጸም ይገባናል"።
(ማቴ.3+15)

በዚህ ዕለት አምላካችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከእመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም በነቀም ድንግልና ተጸንሶ በነቀም ድንግልና ተወልዶ ሕግ መጽሐፍዊና ሕግ ጠባያዊ ሲፈጽም አድጎ በሠላሳ ዓመቱ በእደ ዮሐንስ ለመጠመቅ ከገሊላ ወደ ዮርዳኖስ ሔደ። ዮሐንስም መልሶ "እኔ ሆይ እኔ በአንተ ልጠመቅ ይገባኛል እንጂ አንተ በኔ በባሪያህ ልትጠመቅ አይገባህም" እያለ ሲከራከር "አሁንስ ፍቀድልኝ ጽድቅን ሁሉ መፈጸም ይገባናል" አለው (ማቴ 3፡16) "እንግዲያውስ በማን ስም ላጥምቅህ አለው"? "ወልዱ ለበሩክ ኩኑቱ ብርሃን ተማህለን እያልክ አጥምቀኝ" አለው ወደ ዮርዳኖስ ወንዝ ወረዱ ባሕርይ ርእየት ወንተት ወርዮርዳኖስ ገጸ ድኀሬሁ ወሆችም ተናወጡ ተራሮች ሽቀብ እንደጊደር ዘለሉ በአምላክነቱ አጽንቷቸዋል ቅዱስ ዮሐንስም ወልዱ ለበሩክ ኩኑቱ ብርሃን ተማህለን እያለ አጥምቆታል።

ትምህርት

- የቅዱስ ዮሐንስ ምስክርነት
  ከእኔ በኋላ የሚመጣው ከእኔ እጅግ ይበልጣል
  (ማቴ.3+11)
- የአምላካችን ፍጹም ትሕትና
  ኢየሱስም ከገሊላ ናዝሬት መጥቶ በዮሐንስ እጅ በዮርዳኖስ

ይህን የምልክቶች መጀመሪያ በገሊላ ቃና አደረገ። ክብሩንም ገለጠ ደቀመዛሙርቱም በእርሱ አመኑ።

ትምህርት

- አምላካችን የሚያዝንን ማድረግ
  (ዮሐ.2+5)
- የቅድስት ድንግል ማርያም ምልጃ ዋጋ ያለው መሆኑን ያወቅንበትና የተረዳንበት (ዮሐ.2+11)

መልእክት

በድንግል ማርያም አማላጅነት ውኃው ወደ ወይን ጠጅ የተቀየረው በምትሐት አይደለም፤ ተንጠፍጥፎ አልቋል ዶኪማስ አንገቱን ደፍቷል እመቤታችን ግን በአማላጅነቷ ከኀፍር ኃዘን ከውርደት አድንቃለች። ዛሬ የምናከብረው በዓል ሁላችንም የምንለወጥበት መሆን አለበት በድንግል ማርያም አማላጅነት በዶኪማስ ቤት ነውር፣ ኃዘን፣ ኃፍረት ተወግዷል። ውኃው ወደ ወይን ተቀይሯል፤ የምርፋቁ አሳዳሪ እስከ መገረምና መደነቅ ደርሷል ይህ የመጀመሪያው ተአምርና ምልክት በዶኪማስ ቤት ሲደረግ ብዙዎች በአምላካችን አምነዋል።

በዚህ ዘመን የኛ ሕይወት ተቀይሮ ይሆን? ባዶነትስ እየተሰማን ይሆን? እንግዲያውስ ወጣቱ ሕይወቱ የሚለወጥበት ርካታ ላጣው ዓለም ሰላም የሚያገኝበት በዓል ነውና እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያምን

በዶኪማስ ቤት እንደተገኘች ሁሉ የኛንም ቤታችንና ጎደሎ ማንነታችንን በአማላጅነት ታስለውጥልን አሜን።

የቅዳሴ ምንባብ

ሮሜ 9፡1

ይሁዳ 1፡9

የሐዋ 10፡34

ምስባክ፦ ወምስካይን እምላኩ ለያዕቆብ

ንዑ ትርአዮ ግብረ ለእግዚአብሔር

ዘገብረ መንክረ በዲበ ምድር መዝ 45፡78

ወንጌል ዮሐ 1፡44

ቅዳሴ ዘኤጲፋንዮስ

ማሳሰቢያ

ታሪኩ የተፈጸመው የካቲት 23 ነው።

ተጠመቀ (ማር 1+9)

- የተዘጋው የምህረት (ገነት) በር ተከፈተ
- መንፈስ ቅዱስ በርግብ አምሳል መገለጡ።
  "የእግዚአብሔርም መንፈስ እንደርግብ ሲወርድ በእርሱ ላይ ሲመጣ አየ" (ማቴ 3፡16)

መልእክት

በጥምቀቱ የዕዳ ደብዳቤችን ስለደመሰሰልን ባርነታችንን ስላስገደልን የተሰጠንን ነፃነት ጠብቀን ልጅነታችንን አክብረን ውለታውን እያሰብን ልንኖር ይገባል።

የቅዳሴ ምንባብ

ቲቶ 3፡4

1ዮሐ 5፡5

የሐዋ 10፡34

ምስባክ፦ ርእዩከ ማያት እግዚኦ

ርእዩከ ማያት ወፈርሁ

ደንገፁ ቀላያተ ማያት ወደምፀ ማያቲሆሙ /መዝ 76፡16/

ወንጌል ሉቃ 3፡21

ቅዳሴ /ዘዲዮስቆሮስ/

ጥር ዐሥራ ሁለት ቃና ዘገሊላ

የዕለቱ የትምህርት ርእስ

"መልካሙን ወይን ለምን አዘገያችሁት"?
(ዮሐ 2+10)

በሦስተኛውም ቀን በገሊላ አውራጃ በቃና ሠርግ ነበረ፤ እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ኢየሱስ ክርስቶስና ደቀመዛሙርቱ ወደ ሠርጉ ቤት ታደሙ የወይን ጠጅም ባለቀባቸው ጊዜ የወይን ጠጅ እኮ የላቸውም? አለችው "አንቺ ሴት ካንቺ ጋር ምን አለኝ ጊዜዬ ገና አልደረሰም አለ እናቱም ለአገልጋዮቹም የሚላችሁን አድርጉ አለቻቸው አይሁድ እንደሚያደርጉት የመንጻት ልማድ ስድስት የድንጋይ ጋኖች በዚያ ተቀምጠው ነበር እያንዳንዳቸውም ሁለት ወይም ሦስት እንስራ ይይዙ ነበር። ኢየሱስም ጋኖቹን ውኃ ሙሉአቸው አላቸው እስከ አፋቸውም ሞሉአቸው "አሁን ቀድታችሁ ለአሳዳሪው ስጡት" አላቸው ሰጡትም አሳዳሪውም የወይን ጠጅ የሆነውን ውኃ በቀመሰ ጊዜ ከወዴት እንደመጣ አላወቀም ውኃውን የቀዱት አገልጋዮች ግን ያውቁ ነበር አሳዳሪውም ሙሽራውን ጠርቶ ሰው ሁሉ አስቀድሞ መልካሙን የወይን ጠጅ ያቀርባል? ከሠከሩም በኋላ መናኛውን አንተስ መልካሙን የወይ ጠጅ እስከ አሁን አቆይተሀል፤ መልካሙን ወይን ለምን አዘገኸው አለው። ኢየሱስም

ጥር ዐሥራ ስምንት
ዝርወተ አጽሙ ለቅዱስ ጊዮርጊስ

የዕለቱ የትምህርት ርእስ

ዘወትር ለሞት ተላልፈን እንሰጣለን
(2ቆር. 2+11

ሰማዕቱ ቅዱስ ጊዮርጊስ የዱዲያኖስን ቀጣና ሰይፍ ሳይፈራ በሕማሙ በሞቱ የማያምኑትን እያሳመነ ሰባት ዓመት ተጋድሏል። በዚህም ዕለ የሚታሰበው የዱድያኖስ ወታደሮች በሰይፍ አንገቱን ቀርጠው በእሳ አቃጥለው ከጉድጓድ ውስጥ ጥለውት የማይሞት ቢሆን ሥጋው በመንኰራኩር አስፈጭተው ደብረ ይድራስ ተራራ ላይ ቢበትኑት እን ጤስ ተኖ እንደ ትቢያ በኖ ሥጋው በመንኰራኩር ተፈጭቶ የተበተነ ሥጋው ሰው በማይመረምረው በጥበበ እግዚአብሔር ተሰብስቦ አንድ አካ ሆኗል እንደ ቀድሞው ሆኖ ያመነው ጌታም አሥነስቶታል በዚህ ዕለ ታስቦ ይውላል።

ትምህርት

- እውነተኛ ምስክር መሆን
  «ሰው በልቡ አምኖ ይጸድቃል በአፉም መስክሮ ይድናል» (ሮ 10+10)
- ስለ እውነት ብንሞትም የሚያሥነሳን አምላክ እንዳለ ማመን

«በሕይወት ሆነን ብንኖር ለጌታ እንኖራለን ብንሞትም ለጌታ እንሞታለን» (ሮሜ 5+4)

መልእክት

ሰማዕቱ ቅዱስ ጊዮርጊስ የእምነት አርበኛ በመሆን አካሉ በመንኰራኩር ተፈጭቶ በተራራ ላይ ቢበተንም ያመነውና የመሰከረለት ጌታ ከሞት አሥነስቶታል። እንደ ቅዱስ ጊዮርጊስ የዘመናችን ሰማዕት ማን ይሆን ....?

የሰማዕቱ አማላጅነት አይለየን አሜን።

የቅዳሴ ምንባብ

ሮሜ 8፡35

1 3፡1

የሐዋ 17፡30

ምስባክ፦ ወእምኩሉ ያድኅኖሙ እግዚአብሔር

እግዚአብሔር የዐቅብ ኩሎ አዕፅምቲሆሙ

ወኢይትቀጠቀጥ አሐዱ እምውስቴቶሙ /መዝ 33፡19/

ወንጌል ማቴ 5፡42

ቅዳሴ ዘወልደነጎድጓድ

ጥር ሃያ አንድ
በዓለ ዕረፍታ ለቅድስት ድንግል ማርያም

የዕለቱ የትምህርት ርእስ

ከእንግዲህ ወዲህ በጌታ የሚሞቱ ብፁዓን ናቸው። ከድካማቸውም ያርፉ ዘንድ ሥራቸውም ይከተላቸዋል። (ራእ.14+13)

እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ከአባትና ከእናቷ ጋር 3 ዓመት በቤተ መቅደስ 12 ዓመታት ከልጇ ጋር 33 ዓመት ከ3 ወር ጌታ ከዐረገ በኋላ 15 ዓመት ከዮሐንስ ጋር · በድምሩ እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም 64 ዓመት በዚህ ዓለም ኖራ ጥር 21 ቀን በ49 ዓመተ ምሕረት በዕለተ እሁድ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እልፍ አእላፋት መላእክትን አስከትሎ እናቴ ሆይ ከዚህ ዓለም ድካም ላሳርፍሽ መጣሁ አላት። ልጄ ሰማይና ምድር የማይወስኑህን ዘጠኝ ወር ከአምስት ቀን በማኅፀኔ ተሸክሜ በድንግልና ወልጄህ እሞታለሁን? አለችው በሲኦል ወስዶ የሚሰቃዩ ነፍሳትን አሳያት እነዚህ በሲኦል የሚሰቃዩት ነፍሳት ከማርከልኝ በእነርሱ ፋንታ ይሁን አለችው። ጌታም ሲምርላት ቃል ኪዳን ገብቶ ቅዱስ ሥጋዋን ከክብርት ነፍሷ ለይቶ በቃለ አቅርንት በዝማሬ መላእክት አሳረጋት በሲኦል የሚሰቃዩ ነፍሳት ከሞት ጉድጓድ ወጥተዋል፤ የእናታችን የድንግል ማርያም ዕረፍቷ መድኃኒት ሆኗቸዋል። ሐዋርያትን ከያሉበት በደመና ጠቅሶ ካለችበት አድርሷቸው እመቤታችሁን ቅበሩ

አሏቸው የእመቤታችን ቅዱስ ሥጋዋን በክብር አድርገው ወደ ጌቴሴማኒ ይዘዋት ሲሄዱ አይሁድ አየ ከዚህ በፊት ልጇን ተነሣ፣ ዐረገ እያሉ ሲያውኩን ይኖራሉ አሁን ደግሞ እሷን ተነሣች፣ዐረገች እያሉ ሊያውኩን አይደለምን? «ኑ ናውጺ ሥጋሃ ለማርያም»፣ የማርያምን ሥጋዋን እናቃጥላት» ብለው በምቀኝነት ተነሱ። ከመካከላቸው ታውፋንያ የተባለ በድፍረት ዘሎ የአልጋዋን ሸንኮር ያዘ ከእግዚአብሔር የታዘዘ መልአክ ሁለት እጁን በሰይፍ ቀጣው በድያለሁ ማረኝ ብሎ ቢማፀናት አዛኝ ናትና ቀና ብላ ቅዱስ ሊጥርስን እንደነበረው አድርገለት አለችው ቢመለሰው እንደነበረ ሆኖለታል። ዮሐንስን ጨምሮ ከመካከላቸው ነጥቆ በዕፀ ሕይወት ሥር አስቀምጧታል።

ትምህርት

- በጌታ ያመነች ብፅዕት እናታችን ስለሆነች ብታርፍም ሥራዋ እንደሚከተላት ማመን (ራእ.14+13፣ ሉቃ.1+47)
- በድፍረት የእመቤታችን ሥጋዋን ለማቃጠል የመጣ ታውፋንያ መቀጣቱ
- የእመቤታችን ፍቅር ሰይፍ ይዞ ለመጣው ምሕረትን ማድረጓ

መልእክት

እግዚአብሔርን አምኖ መሞት ለክብር ያበቃል። የእመቤታችን ዕረፍት እንጂ ሞት አይደለም። እንዳመንን ኖረን ብንሞት እንከብራለን እና እርሱን በማምለክ እንጽና።

የድንግል ማርያም አማላጅነት አይለየን አሜን!

መልእክት

አረጋዊ ስምዖን ለሰው ልጆች ሁሉ መድኃኒት የሆነውን አምላክ ካየ በኋላ ዐይኖቼ ማዳንህን አይተዋልና ባሪያህን በሠላም አሰናብት ብሎ ጠየቀ። አምላክን ከማየት የበለጠ ትልቅ ነገር የለምና እኛም ዘወትር እንደ አረጋዊ ስምዖን ከቤተ መቅደስ ልንለይ አይገባንም።እኛ ወደ እግዚአብሔር እንቅረብ እንጂ የምንፈልገውን ሁሉ እስከምንጠግብ ድረስ በበረከት ያትረፈርፈናል። የማዳን ሥራውንም ያሳየናል። አምላካችን እግዚአብሔር በቸርነቱ ይጠብቀን አሜን።

የቅዳሴ ምንባብ

የዕለቱ የቅዳሴ ምንባብ

1ኛ ጢሞ.5+5

ያዕ.5+13

ሐዋ. 3+17

ምስባክ፡- ጉሥዐ ልብየ ቃለ ሠናየ።

ወአነ አየድዕ ግብርየ ለንጉሥ።

ከመ ቀለመ ጸሐፊ ዘጠበጠበ ይጽሕፍ ልሳንየ

መዝ.44+1

ወንጌል፡- ሉቃ.2+22

ቅዳሴ፡- ዘዲዮስቆሮስ

የካቲት ዐሥራ ስድስት

ኪዳን ምሕረት

የዕለቱ የትምህርት ርእስ

ከመረጥኳቸው ጋር ቃል ኪዳን አደረኩ

(መዝ 88+3)

በዚህ ዕለት አምላካችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለእመቤታችን ለቅድስት ድንግል ማርያም ቃል ኪዳን ገብቶላታል ።

የእግዚብሔር ቃል ኪዳን

- ኪዳን አዳም
  ከልጅ ልጅህ ተወልጄ አድንኃለሁ (ዘፍ 3+17)
- ኪዳን ኖህ
  ከዚህ በኋላ ምድርን በንፍር ውኃ አላጠፋም (ዘፍ 9+1-17)
- ኪዳን አብርሃም
  የምድር አሕዛብ በዘርህ ይባረካሉ (ዘፍ 22+18)
- ኪዳን ያዕቆብ
  (ዘፍ28+14)
- ኪዳን ሙሴ
  (ዘጸ33+23)
- ኪዳን ዳዊት

የቅዳሴ ምንባብ

ገላ 4፣1

2ዮሐ 1፣1

የሐዋ 7፡30

ምስባክ፡- በከመ ሰማዕነ ከማሁ ርኢነ

በሀገረ እግዚአ ኃያላን በሀገረ አምላክነ /መዝ 47፣8/

እግዚአብሔር ሣረራ ለዓለም

ወንጌል ሉቃ 1፡47

ቅዳሴ /ዘእግዝእትነ/.

የካቲት ስምንት

ስምዖን

የዕለቱ የትምህርት ርእስ

ዓይኖቼ ማዳንህን አይተዋል።

(ሉቃ 2፡37)

እንደ ኦሪቱ ሕግ ወንድ ልጅ በ40 ቀኑ ሴት ልጅ በ80 ቀኗ እንዲ ርግብ ዘውገ ማዕነቅ ይዘው ወደ ቤተመቅደስ እንዲገቡ ታዝዟል። (ዘሌ.2+2) በዚሁም መሠረት ጌታችን አምላካችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስም

ሕገ ኦሪትን ሊፈጽም እንጂ ሊሽር አልመጣምና (ማቴ.5+17) እናቱ ቅድስት ድንግል ማርያም ከአረጋዊ ዮሴፍ ጋር በ40 ቀኑ ወደ ቤተ መቅደስ ይዘውት ሄዱ። በዚያን ጊዜም ጻድቅና ትጉሕ የሆነ ስምዖን የሚባል ሰው በኢየሩሳሌም ይኖር ነበር፤ እርሱም የእስራኤልን መጽናናት የሚጠባበቅና መንፈስ ቅዱስ በላዩ ያደረ ሰው ነበር። ደግሞም የጌታን መወለድ ሳያይ እንደማይሞት በመንፈስ ቅዱስ ተገልጦለት ይጠባበቅ ነበር፤ በዚህ ጊዜ በመንፈስ ቅዱስ ተመርቶ ወደ ቤተ መቅደስ ገባ፤ ሕጻኑን ጌታችንን አምላካችንን እና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስን ዐቀፈው። ወዲያውም ጌታ ሆይ በገባኸው ቃል መሠረት ባሪያህን በሠላም አሰናብተው፤ ዐይኖቼ በሰው ሁሉ ፊት ያዘጋጀኸውን ማዳንህን አይተዋልና ብሎ ተናገረ።

ትምህርት

- ለስምዖን የተነገረው ተስፋ መፈጸሙ

  «አሁን እንደ ቃልህ ባሪያን በሠላም ታሰናብታዋለህ» (ሉቃ.2+29)
- በቅድስና እግዚአብሔርን እያከበሩ መኖር
  (ሉቃ. 2+35)
- የእግዚአብሔር የማዳን ሥራ ማየት
  (መዝ. 47+8)

(መዝ 88+35)

የእነዚህ ቅዱሳን አባቶቻችን ሁሉ ቃል ኪዳናቸው ፍጻሜ ያገኘው በአምላካችን በኢየሱስ ክርስቶስ ነው ።

ትምህርት

- የእመቤታችን ቃል ኪዳን (ሉቃ 1+28)
- የኢየሱስ ክርስቶስ እናት ስለሆነች (ሉቃ2+1)
- ለሰው ልጅ ሁሉ የምታማልድ ስለሆነች ቃል ኪዳን ተሰጥቷታል ።(ዮሐ2+5)
- ጸጋን የተሞላች እናታችን ስለሆነች ቃል ኪዳን ተሰጥቷታል። (ሉቃ1+3)

መልእክት

እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ስም መታሰቢያዋን ማድረግ፤ ለድሆች፤ ለነዳያን መስጠት የታሠሩትን መጠየቅ ፤የተራቡትን ማብላት በእውነት በምልጃዋ ለሚያምን ሁሉ ምሕረትን የምታሰጥ እናት በምልጃዋ ከሥጋ መከራ እንድታማልደን ቃል ኪዳን ተሰጥቷታል። ሳባ ስምንት ነብስ የጨረሰው በላኤሰብ እንኳን በተሰጣት ቃል ኪዳን በዛሬ ዕለት አማልዳ አስምራዋለች። በእመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም አማላጅነት ማመን ይገባናል። በረከቷና ረድኤቷ፤ በተሰጣት ቃል ኪዳን በምልጃዋ

ዘወትር አትለየን። ፍጹም ፍቅሯን ጣዕሟን በልባችን ያሳድርብን አሜን ።

ገላ 4፣1

2ዮሐ 1፡4

የሐዋ 1፡13

ምስባክ

እስመ ትቤ ለዓለም አሐንጽ ምሕረተ

በሰማይ ጸንዐ ጽድቀከ

ኪዳን ተካየድኩ ምስለ ኅሩያንየ /መዝ 88፣2/

ወንጌል ሉቃ 1፡39-57

ቅዳሴ /ዘእግዝእትነ/

መጋቢት አምስት

ዕረፍቱ ለአቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስ

የዕለቱ የትምህርት ርእስ

የጻድቃንን ሞት እኔ ልሙት ፍጻሜዬም እንደነ እርሱ ፍጻሜ ትሁን (ዘኁ.23+10)

በዚህ ዕለት የጻድቁ አቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስ የዕረፍታቸው በዓል በቤተ ክርስቲያናችን ታስቦ ይውላል። ጻድቁ አባታችን አገራቸው ከግብፅ (ግብፅ) ነው። አባታቸው ስምዖን እናታቸው አቅሌስያ ይባላሉ። ልጅ አጥተው ለ30 ዓመት ሲያዝኑ ኖረዋል ኃዘናቸውንና ልመናቸውን እግዚአብሔር ሰምቶ መጋቢት 29 ቀን ተጸንሰው ታኅሣሥ 29 ቀን ተወለዱ በተወለዱበት ዕለት ብዙ ተአምራት ታይቷል በአገራቸው 300 ዓመት ከቆዩ በኋላ ወደ ኢትዮጵያ ሂድ አላቸው ቅዱስ ገብርኤል በሠረገላ ነፋስ ጭኖ ወደ ኢትዮጵያ አምጥቶአቸዋል።

በዝቋላ ደብረ ቅዱስ (ምድረ ከብድ) በንጽሕና፣ በጾምና በጸሎት ተወስነው 262 ዓመት በኢትዮጵያ ኖረው በተወለዱ 562 ዓመታቸው መጋቢት 5 ቀን ከእግዚአብሔር ቃል ኪዳን ተቀብለው በዕለተ እሁድ አርፈዋል። የጻድቁ በረከት አይለየን።

ትምህርት

- ራስን ለእግዚአብሔር መስጠትን
- የእግዚአብሔርን ጥሪ መስማትና መታዘዝ
- እንደ ጻድቁ አባታችን የጾምና የጸሎት ሰው መሆን
  «እሺ ብትሉ ለኔም ብትታዘዙ የምድርን በረከት ትበላላችሁ» (ኢሳ.1+19)
- የቅዱሳን የዕረፍታቸው በዓል በእግዚብሔር ፊት የከበረ መሆኑን (መዝ. 116+15)

መልእክት

ጻድቁ አባታችን የእግዚአብሔርን የጥሪ ድምፅ በመስማት ከተወለዱበት ሀገራቸው ወደ ኢትዮጵያ በ11ኛው መቶ ክፍለ ዘመን በመምጣትና በማስተማር በጾምና በጸሎት በመትጋት ኖረው በዛሬው ዕለት በክብር በምድረ ከብድ አርፈዋል።

የጻድቅ መታሰቢያ ለበረከት ነውና። (ምሳ.10+7) መታሰቢያቸውን ስናደርግ በረከትን እናገኛለን።
የጻድቁ በረከት አይለየን።

የቅዳሴ ምንባብ

ሮሜ 14+1
1ኛ ጴጥ. 4+1
ሐዋ. 17+19
ምስባክ፡- ክቡር ሞቱ ለጻድቅ በቅድመ እግዚአብሔር።
እግዚኦ አነ ገብርከ።
ገብርከ ወልደ ዓመትከ።
መዝ.116+15

ወንጌል፡- ማቴ.14+19
ቅዳሴ፡- [illegible] (ግሩም)

መጋቢት
ሆሳዕና

የዕለቱ የትምህርት ርእስ
«ፍትሕዎ ወአምጽእዎ ሊተ»
«ፈትታችሁ አምጡልኝ»

(ማቴ 21+2)

በዚህ ዕለት ታስቦ የሚውለው አምላካችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በዘመነ ሥጋዌው ከቤተ ፋጌ ሁለቱን ደቀመዛሙርት የታሰረችውን አህያ ፈትታችሁ አምጡልኝ ማንም ሰው ቢጠይቃችሁ ለጌታ ያስፈልጉታል በሉ አላቸው። በነቢዩ ዘካርያስ የተነገረው የትንቢት ቃል ይፈጸም ዘንድ (ዘካ.9+9) ከቤተ ፋጌ በአህያ ተቀምጦ ወደ ቤተ መቅደስ ገባ።

ትምህርት

• ትህትና

በተናቀች አህያ አምላካችን ተቀምጦ ወደ ቤተ መቅደስ ገባ ከእስራታችን ይፈታን ዘንድ የተናቀችውን አህያ እንዳልናቀ ምንም ኃጢአተኞች ብንሆንም በንስሓ ወደ እርሱ እንድንቀርብ ከእስራታችን ሊፈታን የታመነ ነው።

• የምስጋና ዕለት

ሕፃናት የዘንባባ ዝንጣፊ ይዘው ለአምላካችን ሆሳዕና በአርያም በእግዚአብሔር ስም የሚመጣ የተባረከ ነው እያሉ ምስጋና ያቀረቡበት ዕለት ነው። እኛም ቤተ ክርስቲያን ስንመጣ ለጸሎት ልንመጣ ይገባናል እንጂ ለመነካከስ፣ ለመወነጃጀል፣ ለመነቃቀፍ ልንመጣ አይገባም።

- ቤተ መቅደሱን በስልጣኑ ያጸዳበት ዕለት (ማቴ.21+13)

ታላቁ ቤተመቅደስ ለምስጋና መሆኑ ቀርቶ ሻጮችና ለዋጮች የንግድ ማዕከል አድርገውት ነበር። አምላካችንም «ቤትየሰ ትሰመይ ቤተ ጸሎት፣ ቤቴ የጸሎት ቤት ትባላለች እናንተ ግን የወንበዴዎች ዋሻ አደረጋችሁት» በማለት በጅራፍ እየገረፈ አስወጣቸው። በዚህ ዘመን ወደ መቅደሱ ጌታ ቢመጣ ስንት ያልፀዳ ነገር አለ? በዘረኝነት፣ በክፋት፣ በሐሜት፣ በጥላቻ፣ በመነቃቀፍ የተሞላ መቅደስ አካላችንን በንስሓ አጽድተን እንጠብቅ።

- ለበሽተኞች ፈውስንና ዕረፍትን የሰጠበት ዕለት (ማቴ.21+14)
- የፈሪሳውያን ቅናት የተገለጠበት ዕለት

አምላካችን ከቤተ ፋጌ ወደ ኢየሩሳሌም በታላቅ ምስጋና ሲገባ ፈሪሳውያን ወደ እርሱ ቀርበው ሕጻናቱን ዝም እንዲሉ አድርግ አሉት። በዚህ ዘመን ማስወገድ ያለብን ክፉ ቅናትና ምቀኝነትን ነው ስንቱ በወንድሙ በእህቱ ይቀናል መቅናት ካለብን መንፈሳዊ ቅናት እንቅና።

መልእክት

ፈትታችሁ አምጡልኝ በብዙ ነገር የታሰርን መፈታት ያስፈልገናል በቅናት መንፈስ የታሰርን ይህ መንፈስ ክፉ መንፈስ ነውና መፈታት ያስፈልገናል። ትህትናን፣ ምስጋናን፣ ገንዘብ አድርገን ከታሰርንበት እስራት ሁሉ እንፈታ። ሆሳዕና የመፈታት፣ የምስጋና፣ ቤተመቅደሱ የፀዳበት፣ በሽተኞች ጤና ያገኙበትና የአይሁድ ቅናት ከንቱ የሆነበት ዕለት ነውና ከታሰርንበት እስራት ተፈትተን ለጌታ እናስፈልገዋለንና ወደ ቤተ ክርስቲያን እንምጣ።

አምላካችን እግዚአብሔር ይርዳን አሜን።

የቅዳሴ ምንባብ

ዕብ 9+11

1ጴጥ 4+1-12

የሐዋ 28+11-22

ምስባክ ፡- እም አፈ ደቂቅ ወሕፃናት አስተጸሎክ ስብሐተ

በእንተ ጸላኢ

ከመትንስቶ ለጸላዒ ወለገፋዒ (መዝ 8+2)

ወንጌል የሐ 5+11-13

ቅዳሴ ጎርጎርዮስ

ሰሙነ ሕማማት

ዓመተ ፍዳና ዓመተ ኩነኔ የሚታሰብበት ሲሆን በዚህ ሳምንት ያሉት ዕለታት እንደሚከተለው ቀርበዋል።

ሰኞ
የበለስዋ መረገምና መድረቅ

(ማቴ.21+18)

አምላካችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከኢየሩሳሌም በማለዳ ወደ ቢታንያ መጣ፤ በማለዳ ከከተማ ሲመለስ ተራበ፤ በመንገድም አጠገብ በለስ አይቶ ወደ እርሷ መጣ ቅጠል ብቻ እንጂ ፍሬ አልተገኘባትም ለዘለዓለም ፍሬ አይገኝብሽ አላት በለሲቱም ደረቀች። በዚህ ዘመን አምላካችን ወደኛ መጥቶ ቢጠይቀን ከኛ የሚያገኘው ምንድነው? ፍቅር ከኛ አያገኝም፣ አምላካችን የተራበው ፍቅር ነው ቅጠል ብቻ ነው ያገኘው ፍሬ ግን የለም በዚህ ዘመንም ያለው ቅጠል እንጂ ፍቅር ከሰዎች ጠፍቷል ተራበ ተራበ ተራበ ምን? ፍቅር ፍቅር ፍቅር መቼ ይሆን በፍቅር የምንኖረው? የመንፈስ ፍሬ ፍቅርን ሳናፈራ ጥላቻን ይዘን ለሚያልፈውና ለሚቀረው ዓለም በመድከም ወደ መቃብር እንዳንወርድ በፍቅር እንኑር።

ማክሰኞ
አምላካችን ጥያቄ የተጠየቀበት ዕለት

(ማቴ.21+23-27)

ክብር ምስጋና ይግባውና አምላካችን ወደ ቤተ መቅደስ ገብቶ ሲያስተምር የካህናት አለቆችና ፈሪሳውያን ጥያቄ ጠየቁት በምን ስልጣን...እነዚህን

ታደርጋለህ? ለጥያቄዎቻችን ሁሉ መልስ የሚሰጠን አምላክ ተጠየቀ። ጥያቄያቸውንም በጥያቄ በመመለስ ድል አደረጋቸው።

ረቡዕ
አምላካችንን አሳልፎ ለመስጠት የመከሩበት ዕለት

(ማቴ 26+1)

በሊቀ ካህኑ በቀያፋ ግቢ ተሰበሰቡ፤ ኢየሱስንም በተንኮል ሊይዙት ሊገድሉትም ተማከሩ፤ ነገር ግን በሕዝብ ዘንድ ሁከት እንዳይነሳ በዓሉ ይለፍ አሉ። ሰውን ለመክራ፣ አሳልፎ ለመስጠት፣ ለመስቀል ሞት እያሰብን በሰዎች ሞት እኛ ደስ የምንሰኝ፣ በሰዎች ስቃይ እኛ በዓል የምናከብር ከሆነ ከአይሁድ የተለየ ሕይወት የለንም። አምላካችን እግዚአብሔር ከጥላቻ፣ ከክፋት፣ ከምቀኝነት፣ ከተንኮል፣ በግብዝነት ከተሞላ ሕይወት ይጠብቀን አሜን።

ጸሎተ ሐሙስ

የዕለቱ የትምህርት ርእስ
«ሁላችሁ ንጹሓን አይደላችሁም»

(ዮሐ13+11)

ይህ ዕለት ብዙ ስያሜ አለው

- **ጸሎተ ሐሙስ ይባላል፡-** ወደፈተና እንዳትገቡ ተግታችሁ ጸልዩ ብሎ ስላስተማረ (ማቴ 26+36)

- **ትዕዛዘ ሐሙስ ይባላል፡-** እኔም ለእናንተ እንዳደረግሁ እናንተም ደግሞ እንዲሁ አድርጉ ስላለ (ዮሐ13+15)
- **ሕጽበተ እግር ሐሙስ ይባላል፡-** የደቀመዛሙርቱን እግር ስላጠበ (ዮሐ13+3)
- **አረንጓዴው ሐሙስ** ይባላል ለምለም ዛፍ በነበረበት በጌቴ ሴማኒ ስለጸለየ (ማቴ.26+35)
- **የአዲስ ኪዳን ሐሙስ፡-** የብሉይ ኪዳንን መስዋዕት ሽሮ ራሱንመስዋዕት አድርጎ ስላቀረበ (ማቴ.26+20-36)
- **የነፃነት ሐሙስ**
  "ከእንግዲህ ባሮች አይደላችሁም" (ዮሐ.15+15)

መልእክት

በዚህ ዕለት አምላካችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የደቀ መዛሙርቱን እግር አጠበ ይሁዳንና ጴጥሮስን ዮሐንስንም ያዕቆብንም እግራቸውን ሲያጥባቸው ይሁዳ ነገ ትሸጠኛለህ ጴጥሮስ ትክደኛለህ ዮሐንስም ነገ መስቀል ላይ ወዳጅ ነህ እያለ አይደለም ያጠባቸው። እርሱ ጌታና አምላክ ሲሆን የደቀ መዛሙርቱን እግር ማጠብ እጅግ የሚያስገርም ትሕትና ነው።

በዚህ ዘመን ብዙ ይሁዳዎች አሉ ኪሮጃቸውን ይዘው ገንዘብ ብቻ የሚሰበስቡ ስለ በጎቹ ምንም በጎ ሕሊና የሌላቸው እንዲሉ ቢሰማንም ይሁዳ እኮ ቢታጠብም ንፁህ ስላልሆነ ማንም ውጣ ሳይለው ከታላቁ ጉባኤ ተለይቶ ወጥቷል። እኛ ግን ከአምላካችን እንደተማርነው ሁሉንም ሰው በፍቅር ዓይን እንድናይ ማንንም እንዳንገፋ እንጠንቀቅ።

መጋቢት ሃያ ሰባት

ስቅለት

የዕለቱ የትምህርት ርእስ
አንዱ ስለ ሁሉ ሞተ

(2ኛ ቆሮ.5+14)

ከጌታችንና ከአምላካችን ከመድኃኒታችን ከኢየሱስ ክርስቶስ በፊት መስቀል የወንበዴ መቅጫ መግደያ ነበር። ሰውን በመስቀል ላይ መቅጣት የተጀመረውም በፋርስ ነው። ፋርስ የዛሬዋ ኢራን ናት። የፋርስ ሰዎች "አርሙዝድ" የተባለ "የመሬት አምላክ" ያመልኩ ነበር። ከዚህም የተነሣ "ወንጀለኛው ቅጣቱን በመሬት ላይ የተቀበለ እንደሆነ አምላካችን ይረክሳል!" ብለው ስለሚያምኑ ወንጀለኛውን ከመሬት ከፍ አድርገው በመስቀል ላይ ይቀጡት ነበር። ይህም ቅጣት ቀስ በቀስ በሮማ ግዛት ሁሉ የተስመደ ሕግ ሆነ። ከዚህም ሌላ በኦሪቱ ሥርዓት ቅጣታቸውን በመስቀል ላይ የሚቀበሉ ሰዎች ርጉማንና ውጉዛን ነበሩ። ይህንንም እግዚአብሔር ለሙሴ "ማንም ሰው ለሞት የሚያበቃውን ኃጢአት ቢሠራ እንዲሞትም ቢፈረድበት፥ በእንጨትም ላይ ብትሰቅለው፥ በእንጨት ላይ የተሰቀለ በእግዚአብሔር ዘንድ የተረገመ ነውና ሬሳው በእንጨት ላይ አይደር!" ሲል ነግሮታል። (ዘዳ.21+22)።

ትምህርት

"በመስቀል ላይ ተሰቅሎ የሚሞት የተረገመ ከሆነ ለምን ጌታችን በመስቀል ተሰቅሎ ሞተ?"

- ቅጣታችንን ተቀብሎ ሞተ፦ የሁላችንንም በደል በራሱ ላይ አኖረ። (ኢሳ.53+6)
- የእኛን ሞት ሞተ፦ በአንድ ሰው ምክንያት ሞት ወደዓለም ገባ ተብሎ እንደተጻፈው (ሮሜ 5+15)
- ፈውስ እናገኝ ዘንድ ሞተ፦ በእርሱ ቁስል እኛ ተፈወስን። (ኢሳ.53+5)
- ገነትን እንወርስ ዘንድ መርገማችንን ወስዶ ሞተ፦ በእንጨት የተሰቀለ የተረገመ ነው። ተብሎ እንደተጻፈው (ዘዳ.21+23)
- ሙታንን ያነሣ ዘንድ ሞተ
- የዲያብሎስን ምክር ያፈርስ ዘንድ ሞተ።

አንዱ ስለ ሁላችን ሞቶ ምን አገኘን?

ሕይወትን አገኘናል!

በኃጢአት ምክንያት ሞት ገዝቶን ሞት ነግሦብን እንኖር ነበር። ኃጢአት በዘር እየተላለፈም ሁላችንም በአዳም ኃጢአት ምክንያት እንሞት ነበር። በመሆኑም ሞት ከአዳም እስከ ሙሴ ድረስ በሰው ልጆች ሁሉ ላይ ነግሶ (ሮሜ.5+12)። ከክርስቶስ ሞት በኋላ ግን በክርስቶስ ሞት ስለተሻረ አጥተነው የነበረውን ሕይወት አገኘናል። "ሁሉ በአዳም እንደሚሞቱ ሁሉ በክርስቶስ ደግሞ ሕያዋን ይሆናሉና!"(1ኛ ቆሮ. 15+22)። በተጨማሪም "እኛ ሁላችን ደግሞ፥ በሥጋ ምኞት እንኖር ነበር፤ እንደሌሎቹም ደግሞ ከፍጥረታችን የቁጣ ልጆች ነበርን። ነገር ግን እግዚአብሔር በምሕረቱ ባለጠጋ ስለሆነ፥ ከወደደን ከትልቅ ፍቅሩ የተነሣ በበደላችን ሙታን እንኳ በሆንን ጊዜ ሕይወትን ሰጠን (ኤፌ.2+3-5)።

ትምህርት

የኢየሱስ ክርስቶስ ከሞት የመነሣቱ ማረጋገጫው ምንድነው?

- ከሞት በተነሣበት ቀን አምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስ በግልጥ ታይቷል።
  - ለማርያም መግደላዊት (ዮሐ.20+11)
  - ለሌሎች ሴቶች (ማቴ.28+9)
  - ለሁለቱ የኤማሁስ መንገደኞች (ሉቃ.24+13)

የኢየሱስ ክርስቶስ ከሞት መነሣቱ ለእኛ ለክርስቲያኖች ያለው ጥቅም ምንድነው?

- ከሞት የመነሣታችን ማረጋገጫ ነው።

ኢየሱስ ክርስቶስ እንደሞተና እንደተነሣ ካመንን እንዲሁም በኢየሱስ ያንቀላፉትን እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር ያወጣቸዋልና (ያስነሣቸዋል) (1ኛተሰ.4+13)። አሁን ግን ክርስቶስ ላንቀላፉት በኩራት ሆኖ ከሙታን ተነሥቷል። ሞት በሰው በኩል ስለመጣ ትንሣኤውም በሰው በኩል ሆኗል። (1ኛ ቆሮ.15+21) ሞት ድል በመነሣት ተዋጠ (1ኛ ቆሮ 15+54)።

- የኢየሱስ ትንሣኤ የስብከታችን ማረጋገጫ ነው፦ ትንሣኤ ሙታን ከሌለ ክርስቶስ ከአልተነሣማ፤ ስብከታችን ከንቱ ነው። (1ኛ ቆሮ.15+12)፤
- ትንሣኤው የእምነታችን ማረጋገጫ ነው፦
  ክርስቶስ ካልተነሣማ እምነታችን ከንቱ ነው። (1ቆሮ.15+17)

መልእክት

የኢየሱስ ክርስቶስን ትንሣኤ ስናከብር ምን ማድረግ አለብን?

- ወደ ቅድስት ቤተክርስቲያን በመምጣት፤ በማስቀደስ ያልቆረብን ንስሐ ገብተን ቅዱስ ሥጋውንና ክቡር ደሙን መቀበል ይገባናል። ፋሲካችን ክርስቶስ ታርዷልና (1ኛ ቆሮ.5+6) አሮጌው ማንነታችንን አስወግደን ወደ እርሱ ልንቀርብ ይገባል።
- የተራቡትን፤ የተቸገሩትን፤ የቀን ፀሐይ፤ የሌሊት ብርድ የሚፈራረቅባቸውን በመጎብኘትና ያለንን በማካፈል ማክበር ይገባል።
- በእስር ቤት የታሰሩትን መጎብኘት፤ «ከእነርሱ ጋር እንደታሰረ ሆናችሁ እስረኞችን አስቡ» (ዕብ. 13+3)

የቅዳሴ ምንባብ

2ኛ ቆሮ 15+1-20
1ኛ ጴጥ 1+1-13
የሐዋ 2+22-27

ምስባክ ፦ ዛቲ ዕለት እንተ ገብረ እግዚአብሔር
ንትፈሣሕ ወንትሐሠይ ባቲ
ኦ እግዚኦ አድኅነኒ

ወንጌል ዮሐ 20+1-17
ቅዳሴ (እምቅድመ ዓለም)

እስከ ባለ 50 የሚቆይ የክርስቲያኖች ሰላምታ፤

ክርስቶስ ተንሥአ እሙታን - ክርስቶስ ከሙታን ተነሣ፤
በዐቢይ ኃይል ወሥልጣን - በታላቅ ኃይልና ስልጣን፤
አሠሮ ለሰይጣን፤- ሰይጣንን አሰረው፤

ኃጢአት ወደ ዓለም ገብቶ ሞትን የመጣበን በመብል ምክንያት ነው። (ዘፍ.3+1-24)።

- ሰላምን አግኝተናል!

ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ፥ "ሰላምን እተውላችኋለሁ፥ ሰላሜን እሰጣችኋለሁ፤ እኔ የምሰጣችሁ ዓለም እንደሚሰጥ አይደለም!" ብሎ እንደተናገረ ፍጹም የሆነውን ሰላም የሰጠን በመስቀል ላይ ነው።

- አዲስ ሰው ሆነናል!

በኃጢአት አርጅቶ የነበረው ሰውነታችን አዲስ የሆነው በመስቀል ላይ በተፈጸመው ቤዛነት ነው። "ከእንግዲህ ወዲያ ለኃጢአት እንዳንገዛ የኃጢአት ሥጋ ይሻር ዘንድ አሮጌው ሰዋችን /ሰውነታችን/ ከእርሱ ጋር እንደተሰቀለ እናውቃለን።" (ሮሜ.6+6)

- ከራሱ ጋር አስታርቆናል!

በኃጢአት ምክንያት ከእግዚአብሔር ጋር ተጣልተን እንኖር ነበር። ይሁን እንጂ እኛ በበደልን እርሱ ክሶ በቤዛነቱ መልሶ ታርቆናል። "ጠላቶቹ ሳለን ከእግዚአብሔር ጋር በልጁ ሞት ከታረቅን፥ ይልቁንም ከታረቅን በኋላ በሕይወቱ እንድናለን! ይህም ብቻ አይደለም፥ ነገር ግን አሁን መታረቁን ባገኘንበት በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል በእግዚአብሔር ደግሞ እንመካለን!" (ሮሜ.5+10)።

መልእክት

አንዱ ስለ ሁላችን ሞተ፤ የእኛን ቅጣት ወሰደ፤ እኛ በእርሱ ሞት ወደ ቀደመ ክብራችን እንመለስ ዘንድ ሞተ። መርገማችንንም ወሰደ። የኢየሱስ ክርስቶስን ስቅለት ስናስብ የተማርን መታረቅ አለብን። የኢየሱስ ክርስቶስ

ሞት የሰው ልጆች የጥል ግድግዳ ፈርሶ ፍቅር የተመሰረተበት ዕለት ነውና። ይህን ውለታ እንዳንረሳ።

የቅዳሴ ምንባብ

ዕብ 3፥15
ራእ 12፥2
የሐዋ 10፥30

ምስባክ፦ እግዚአብሔርሰ ንጉሥ ውእቱ እምቅድመ ዓለም
ወገብረ መድኃኒተ በማዕከለ ምድር
አንተ አጽናዕከ ለባሕር በኃይልከ

ወንጌል ማቴ 7፥1
ቅዳሴ /ዘዮሐንስ አፈወርቅ/

ትንሣኤ

የዕለቱ የትምህርት ርእስ
"እንደተናገረ ተነሥቷል"

(ማቴ.28+6)

እነሆም የጌታ መልአክ ከሰማይ ወረደ፤ ታላቅ የምድር መናወጥ ሆነ፤ እናንተስ አትፍሩ የተሰቀለውን ኢየሱስን እንድትሹ አውቃለሁና። እንደተናገረው ተነስቷልና...በዚህ የለም...ኑና እዩ አላቸው። ስለ አምላካችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ትንሣኤ አራቱ ወንጌላውያን በመጽሐፋቸው ስለ ትንሣኤው ምስክርነት በመስጠት አረጋግጠው ጽፈዋል።

አግአዞ ለአዳም - አዳምን ነጻ አወጣው፤
ሰላም - ሰላም፤
እምይእዜሰ - ከዛሬ ጀምሮ፤
ኮነ ፍስሓ ወሰላም። - ደስታና ሰላም ሆነ።

ሚያዝያ ሃያ ሦስት

ዕረፍቱ ለቅዱስ ጊዮርጊስ

የዕለቱ የትምህርት ርእስ
እስከ ሞት ድረስ የታመንክ ሁን

(ራእ.2+10)

ጊዮርጊስ ማለት ኮከብ ብሩህ ሐረገ ወይን ፀሐይ ማለት ነው ሀገሩ ልዳ አባቱ አንስጣስዮስ እናቱ ቴዎብስታ ይባላሉ አባቱ በልጅነቱ አረፈ። ቅዱስ ጊዮርጊስ በልጅነቱ ፈረስ መጋለብ ጦር መወርወር ተለማመደ። ቅዱስ ጊዮርጊስ እግዚአብሔርን እያመሰገነ በመልካም አስተዳደግ አደገ ንጉሡ ዱድያኖስ ጣዖት አስቀርጾ ያመልክና ሕዝቡንም ያስመልክ ነበር። ቅዱስ ጊዮርጊስም ይህንን አይቶ አዘነ በጌታችን በአምላካችን ታመነ። ንጉሡ ግን እርሱ የሚያመልከውን ጣዖት እንዲያመልክ አባበለው። በብዙ ጥቅም ለመያዝ ጥረት አደረገ ቅዱስ ጊዮርጊስ ግን አልተቀበለውም ከምድራዊ ስልጣን ይልቅ የእግዚአብሔር ታማኝ አገልጋይ መሆንን መረጠ።

ንጉሡ ዱድያኖስ ስላልተቀበለው በብዙ ሥቃይ አሰቃየው ቅዱስ ጊዮርጊስ ግን እስከ ሞት የታመነ ስለሆነ ጌታችን ያጸናውና ያበረታታው ነበር። የክብርን አክሊል እንደሚያቀዳጀው አምላካችን ቃል ገብቶለታል። ቅዱስ

ጊዮርጊስ የንጉሡን ቃል ስላልተቀበለ ብዙ መከራ ስቃይ እንግልት ደረሰበት በዚህ ሁሉ ግን ቅዱስ ጊዮርጊስ ከእምነቱ ምንም ሳይቀንስ መርዝ ቢያጠጡት ፈቶ ያበራ ነበር በእሳት ቢያቃጥሉት እግዚአብሔር ያስነሣው ነበር በእርሱ የእምነት ጥንካሬ ብዙ ሰዎች በኢየሱስ ክርስቶስ አምነዋል። ሰማዕቱም እስከ መጨረሻ እስከ ሞት ታምኖ ሰባት አክሊል ተቀብሏል ።

ትምህርት

- **እስከ ሞት ድረስ መታመን (ራእ.2+10)**
- **እስከ መጨረሻ ድረስ በእምነት መጽናት**
  «የመጀመሪያ እምነታችን እስከ መጨረሻው አጽንተን ብንጠብቅ የክርስቶስ ተካፋዮች ሆነናል»(ዕብ.3+14)

መልእክት

ሰማዕቱ ቅዱስ ጊዮርጊስ እስከ ሞት ድረስ በእምነት በመጽናት ለነገሥታቱ ሳይንበረከክ ለአምልኮ ጣዖት ሳይገዛ በዚህ ዕለት በሰማዕትነት አርፏል። የሰማዕቱ ሕይወት ብዙ ነገርን ያስተምረናል። ስለ ስሙ ተሰደደን፤ ተንከራተትን፤ ብዙ ዋጋ ከፍለን ይሆን? እውነተኛ ክርስትና የሚባለው እግዚአብሔርን በመውደድ በቀንና በሌሊት በደስታና በኃዘን በክብርና በውርደት ዘወትር አምላካችንን የትኩረት ማዕከል ማድረግ ነው። የማንችለውን ሊያስችለን የማንሆነውን ሊያደርገልን ነውና የእምነት እጆቻችንን ዘርግተን ከባለጠጋው ከእግዚአብሔር እጅ የተሰጠንን ጸጋ እንያዝ፤ የቆምንበት የማይናወጥ ነውና። የሰማዕቱ አማላጅነት አይለየን። አሜን።

የቅዳሴ ምንባብ

2ቆሮ 1+1
1ጴ 1+6
የሐዋ 14፡1

ምስባክ፡- ወይርአዩ አሕዛብ በቅድመ አዕይንቲሁ
በቀለ ጸሞሙ ለአንብርቲከ ዘተክዕወ
ይባዕ ቅድሜከ ገዐርሙ ለሙቁሓን

ወንጌል ማቴ 10፡16-34
ቅዳሴ /ዘወልደ ነጎድጓድ/

ግንቦት አንድ
ልደታ ለእግዝተነ ቅድስት ድንግል ማርያም

የዕለቱ የትምህርቱ ርእስ

ከሊባኖስ የሚፈስ ወንዝ ነሽ። (መኃ4+15)

ትውልድ ሁሉ ብፅዕት በማለት የምንጠራትና የምናመሰግናት እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም በፈቃደ እምላክ ከአባቷ ከኢያቄምና ከእናቷ ከሐና ነሐሴ 7 ቀን ተጸንሳ ግንቦት 1 ቀን ተወለደች ። እናታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ከመወለዷ በፊት በእናቷ ማኅፀን ውስጥ ብዙ ተአምር ሰርታለች ቅድስት ሐና በርሴባ የምትባል አንድ ዓይና አክስት ነበረቻት ልትጠይቃት መጥታ እግዚአብሔር በቸርነቱ ጎበኘሽ እያለች ሐናን በዳሰሰችበት እጇ የጠፋ ዓይኗን ብታሽው በርቶላታል ። ሁለተኛ ደግሞ የሐና የአትቷ ልጅ ሳምናስ የሚባል ሞቶ ሐና የእሊጋውን ሽንኮር ይዛ ስታለቅስ ጥላዋ ቢያርፍበት ሞቶ የነበረው ተነስቶ ሰላም ለኪ እምሐመቀ ለዘጉብረ ሰማየ ወምድረ ። ሰማይና ምድርን የፈጠረ የአምላክ እያቱ ሐና ሰላም ለአንቺ ይሁን ብሎ መስክሮ ተመልሶ አረፏል ይህንን ድንቅ ነገር

ያ አይሁድ በምቀኝነት ተነሥተውባቸዋል። ቀድሞ ከነዚህ ወገን የሆኑ ዳዊትና ሰሎሞን አርባ አርባ ዘመን ገዙን እሁን ከነዚህ የሚወለደው ሊገዛን ነው በማለት በጣልትንት ተነሱባቸው ቅዱስ ገብርኤል ኢያቄምን ለቅስ ሊባኖስ ይዘሀት ሒድ አለው ኢያቄምም ሐናን ይዟት ሒዷ ከመውለጃዋ ጊዜዋ ደርሶ ነበርና ነቢያት ትንቢት የተናገሩላት ትውልድ ሁሉ ብፅዕት የምንላት እያቶቿ ቴክታ በጥሪቃ በጨረቃ አምሳል ኢያቄምና ሐና በርግብ አምሳል ያዩአት እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ሊባኖስ ተራራ በዚህ ዕለት ተወልዳለች ። (መኃ 4 16)

ትምህርት

- እያቶቿ በፀሐይ በጨረቃ እየመሰሉ ያዩት ትንቢት የተፈጸመበት
- የድኅነታችን ምክንያት የተወለደችበት
- ሐናና ኢያቄም ልባቸው ያረፈበት ዕለት
- ትውልድ ሁሉ እናት ያገኘበት ዕለት ነው።

መልእክት

ዛሬው ዕለት እናታችን ቅድስት ድንግል ማርያም የሰው ልጆች ሁሉ እናት ተወልዳልናለች ትውልድ ሁሉ ብፅዕት ከብዕርት ልዕልት እያልን እናመሰግናታለን። የእመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ምስጋናዋን ለሁላችን ፍቅሯን በልባችን ይሳልብን አሜን ።

የቅዳሴ ምንባብ
ገላ 4+1
1ጴ 1+8
የሐዋ 7+44

ምስባክ፡- መሠረታቲሃ ውስተ አድባር ቅዱሳን
ያበድሮን እግዚአብሔር ለአናቅጸ ጽዮን
እምኩሉ ተዐይኒሁ ለያዕቆብ። (መዝ 86+1)

ወንጌል ሉቃ 1+39-57
ቅዳሴ (ዘእግዝትን)

- በአንድ ልብ ሆነን በጸሎታችን፣ በአገልግሎታችን፣ በዘር፣ በጎሣ ሳንከፋፈል ይኽ እንዲህ ነው፣ ያ ደግሞ እንዲህ ነው ሳንል ከኢየሩሳሌም ቤተክርስቲያን የወጣንም እንመስል፣
- ሰዎች ባይመቹንና፣ ክፉዎች ልባችንን ቢያቆስሉንም፣ ሰዎች እንጂ ያልተመቹን ክርስቶስና ቤተክርስቲያን ሁልጊዜ ይመቹናል። ስለዚህም ከኢየሩሳሌም ቤተክርስቲያን አንውጣ።

መልእክት

አምላካችን የማዳን ሥራውን ካጠናቀቀ በኋላ ለተከታዮቹ ደቀመዛሙርት ምስክሮቼ ናችሁ። እጽናኙን እልክላችኋለሁ። "እንትሙሰ ንበሩ ሀገረ ኢየሩሳሌም እስከ ትለብሱ ሃይለ እማርያም። ኃይልን እስክትለብሱ ድረስ በኢየሩሳሌም ከተማ ቆዩ" ብሎ አዘዛቸው።

በመጨረሻም ወደሰማይ ሲያርግ እጆቹንም አንስቶ ባረካቸው። (ሉቃ 24+51)

በብሉይ ኪዳን ተጽፎ እንደምናገኘው፡- አባታችን አብርሃምን ባርኮ ያበዛ(ዘፍ12+1)፣ ያዕቆብን በያቦቅ ወንዝ ሲባረክ ያደረ (ዘፍ35+9)፣ ያቤጽን ባርኮ ሀገሩን ያሰፋ(1ኛ ዜና 4+9)፣ እምስቱን እንጀራ፣ ሁለቱን ዓሣ አብዝቶ የባረከ ጌታ ዛሬም በኑሯችን አብዝቶ የሚባርከን፣ያጣነውን ደስታ የሚመልስልን፣ ባርኮ በበረከት ወደሚያትረፈርፍልን፣ ጉድለትን ሳይሆን ሙላትን፣ ማጣት ሳይሆን በረከትን ወደሚሰጠን አምላክ እንቅረብ። ደቀመዛሙርቱ ዓይኖቻቸውንም ወደላይ ትኩር ብለው እንደተመለከቱት እንደሐዋርያት ማየት ይጠበቅብናል። እርሱን ማየት ከሁሉም ይበልጣልና ወደሰማይ ያረገውን ጌታ ዐይናችንን እንሥተን እንይ።

በዚህ ዘመን ዐይኖቻችን ምን ይሆን የሚመለከቱት? ገንዘብ፣ ጉግጉጥ ወገኖቻችንን በክፋት የራሳችንን ኃጢአት ሳንመለከት የሌሎችን በማየት

የምንናገር ሥጋዊ ነገሮችን ብቻ የምናይ ከሆነ የክርስቶስ ምስክሮች ሆን አንችልም። እጽናኙም መንፈስ ወደእኛ በፍጹም ሊመጣ ይችልም። በኢየሩሳሌም ቤተክርስቲያን መቆየት እጅግ አስቸጋሪ ነው ሚሆንበን እንደ ደቀመዛሙርቱ ሳንበታተን በአንድ ልብና መንፈስ ሆነን እግዚአብሔርን ኃይልና በረከት እንጠብቅ። እኛም ዐይናችንን ከልባችን ር እንሥተን ምድራዊውን ነገር ማየት ትተን ወደሰማይ ያረገውን ጌታ ርሱን እንድናይ ይርዳን።

የቅዳሴ ምንባብ
(ሮሜ 10+1)
(ጴጥ 3+15)
(የሐዋ 1+11)

ምስባክ፡- ዐርገ እግዚአብሔር በይባቤ
ወእግዚእነ በቃለ ቀርን
ዘምሩ ለአምላክነ ዘምሩ (መዝ 46+5)

ወንጌል ሉቃ 24+45

ግንቦት ዐሥራ አንድ ቀን
ቅዱስ ያሬድ

የዕለቱ የትምህርት ርእስ
ለጌታ በልባችሁ ተቀኙና ዘምሩ
(ኤፌ5 +19)

ዚህ ዕለት ቅዱስ ያሬድ በቤተክርስቲያናችን ታስቦና ተከብሮ ውላል ።

ዕርገት

የዕለቱ የትምህርት ርእስ
"እያዩት ወደሰማይ ዐረገ"
(ሉቃ 24+50 የሐዋ 1+9)

ጌታችን አምላካችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሞትን በሞቱ ድል ነሥቶ የትንሣኤያችን በኩር የሆነው ጌታ መጽሐፈ ኪዳን እያስተማረ ቆይቶ በአርባኛው ቀን እያዩት ወደ ሰማይ ዐረገ።

ዐርገ እግዚአብሔር በይባቤ
ወእግዚእነ በቃለ ቀርን
ዘምሩ ለአምላክነ ዘምሩ
እግዚአብሔር በመለከት ድምጽ ዐረገ፣ዘምሩ ለአምላካችን ዘምሩ፣
ለንጉሣችን ዘምሩ (መዝ 46+5)

ትምህርት

- ምስክሮቼ መሆን። (ሉቃ 24+48) ደቀመዛሙርቱ ያዩትንና የሰሙትን ሞትን አሸንፎ የተነሣውን ጌታ ለዓለም ሁሉ ምስክሮች ሆነ በሕይወት ዘመናቸው ሁሉ የዓላውያንን ነገሥታት፣ የቄሳሮችን ማስፈራሪያ እንዳችም ሳይፈሩ ከምድር ዳርቻ እስከምድር ዳርቻ ሁሉን እያጠኑ መከራ እየተቀበሉ፣ እየታሰሩና እየተገረፉ ምስ ሆንዋል።

ኢየሱስ ክርስቶስ ከዚህ በኋላ ስሙን አትጥሩና በስሙም አታስተምሩ እያሏቸው በሸንጐ ፊት ሲያቀርቧቸው፣ ሲገርፏቸው ደስ እያላቸው ከሸንጐ ፊት ይወጡ ነበር። (የሐዋ 5+40)። ስለ ስሙ ምስክር መሆን መነቀፍና መታሰር፣ መደብደብ እንዴት ደስ ይላል!። እኛም እንደ ደቀመዛሙርቱ ማንንም ሳንፈራ አፋችንን ሞልተን ስለ ስሙ እየመሰከርን ሁሉን ብናጣም ሞታችንን በሞቱ ድል የነሣልንን የሚያወመንን ጠላታችንን በመስቀል ላይ ተሰቅሎ ያስወገደልን፣ ዕረፍትና ሰላም የሰጠን፣ ጨለማውን ገፎ ብርሐንን ያጐናፀፈንን፣ ያለፈውን ታሪካችንን በሰበር ሳይቀረልን ምስክሮች እንሁን።

- አጽናኙን ማወቅና ከእርሱ እርዳታ መጠየቅ
  (ዮሐ.15+26)፡-
- አሕዛብና በዓላውያን ነገሥታት ፊት ሲቆሙ እውነትን እንዲናገሩ የሚያጽናና ኃይል፣

- ከተዘጋ ቤት ወደ ሠገነት እንዲቆሙ የሚያደርግ ኃይል፣
- ልብ ሙሉ ሆነው ከጥርጥር ወደ ፍጹም እምነት፣ ከፍርሃት ወደ ድፍረት እንዲሸጋገሩ የሚያበረታታ አጽናኝ ኃይል እልክላችኋለሁ።

ይህ ኃይል በዘመናችን በጣም ስለሚያስፈልገን በፍፁም መዘንጋት የለብንም። እውነትን ለመናገርና ለመመስከር፣ የሚያስፈልገን ኃይል ነውና።

- ባስልኤልንና ኤልያብን በጥበብ መንፈስ የሞላህ (ዘፀ36+2)
- ሶምሶንን በጽርዓና በኤሽታኦል ያነቃቃህ (መሳ 14+18)

እኛም ሰማያዊ ኃይል ለማግኘት የት እንቆይ?

- በኢየሩሳሌም ቤተክርስቲያን መቆየት

ያሬድ ማለት ሙራድ ማለት ነው ። አባቱ አዳም እናቱ ታውክልያ ሲሆኑ የተወለደው በ505 ዓ/ም በአክሱም ነው ። አባቱ ከሌዋውያን ወገን ሲሆን ካህን ነበረ፣ እድሜው ለትምህርት ሲደርስ ይስሐቅ ለሚባል አጎቱ ወስደው ሰጡት ። ከእርሱ ፊደል አጥንቶ መዝሙረ ዳዊት እንዲማር ለእናቱ ወንድም ለአጎቱ ወስደው ለመምሕር ጌዴዎን ሰጡት። አንዲት ቀለም እንኳ ሳያጠና 7 ዓመት ተቀመጠ። ከዕለታት አንድ ቀን መምህሩ ቀለም ሲጠይቀው መመለስ ስለአልቻለ ሸሽቶ ሲሄድ መንገድ አድክሞት ፀሐይ አቃጥሎት ከዛፍ ጥላ ሥር ተቀመጠ። አንዲት ትል ዛፍ ላይ ጠዋት ለመውጣት ፊልጋ ስድስት ጊዜ እየወጣች ስትወድቅ በሰባተኛው ወጥታ ስትሄድ አየ። «እኔ እስከ መጨረሻው ብተጋ ትምህርት ይገባኝ የለምን» ብሎ ተስፋ ሳይቆርጥ አምላካችን ክብር ምስጋና ይግባውና ብሉይ ኪዳንና አዲስ ኪዳንን ገልጾለታል ቅዱስ ያሬድ የመጀመሪያ የዜማ ደራሲ ነው። የዜማ ደርሰቶቹ ድጓ፣ ጾመ ድጓ፣ምዕራፍ፣ዝማሬ እና መዋሥዕት ናቸው ።

ትምህርት

- ፍጹም ተስፋ አለመቁረጥን
  (2 ጢሞ 5+14)
- የእግዚብሔርን ጊዜ መጠበቅን ያስተምረናል
  (ሰቆቃው.ኤር3+25)
- ሁል ጊዜ አመስጋኝ መሆንን
  መዝ 150+1-6 ፡ 135+1

መልዕክት

ቅዱስ ያሬድ ተስፋ ሳይቆርጥ የእግዚአብሔርን ጊዜ በተስፋ በመጠበቁ ታላቅ የምስጋናና የዝማሬ ጸጋ ተሰጠው እኛስ በሕይወታችን የእግዚአብሔርን ጊዜ ተስፋ ሳንቆርጥ የምንጠብቅ ስንቶች እንሆን? ቅዱስ ያሬድ ለሰባት ዓመት ተስፋ ሳይቆርጥ ተቀምጦ ከእግዚአብሔር ታላቅ የዝማሬ ጸጋ ተሰጠው። እኛም እንደ ቅዱስ ያሬድ እግዚአብሔር ለማመስገን እንድንበቃ አምላካችን ይርዳን ። አሜን ።

የቅዳሴ ምንባባት

ኤፌ 5+15
ያዕ 5+12
የሐዋ. 26፡24

ምስባክ
መድኃኒ ገጽየ እግዚአብሔር ተወከፈኒ
እሴብሖ ለስመ አምላኪየ በማኅሌት
ወእዐብዮ በስብሐት (መዝ 68፡29)

ወንጌል ሉቃ 21+1፡7
ቅዳሴ /ዘዮሐንስ አፈወርቅ

ግንቦት ዐሥራ ሁለት
ፍልሰተ ሥጋሁ ለአቡነ ተክለሃይማኖት

የዕለቱ የትምህርት ርእስ
እግዚአብሔር የጻድቃንን አጥንቶቻቸውን ሁሉ ይጠብቃል
የነሐሴ 24 ታሪክ ይመልከቱ

ከእርሷ ጋር ስለሆነ ከፀሐይ ሰባት እጅ አብርታ ከቤተክርስቲያኑ ጉልላት ላይ በመንበረ ብርሃን ተቀምጣ ሲታን መላእክት ከበው ሲያመሰግኗት ነቢያት፣ ሐዋርያት፣ ሰማዕታት፣ ጻድቃን እጅ ሲነሷት በግልጥ ለክርስቲያንም ለአሕዛብም ለአምስት ቀን ታይታለች። አንድ ወገን አድርጋ ስትባርካቸው ሰንብታለች።

ትምህርት

- እግዚአብሔር ከእመቤታችን ጋር መሆኑን ያወቅንበትና የተረዳንበት ።
- እግዚአብሔር ቃል ኪዳኑን የማይረሳ አምላክ መሆኑን ።
  «ኑ ከቶ በማይረሳ በዘላለም ቃል ኪዳን ተጠጉ » (ኤር 50፡5)

መልእክት

በዘመናችንም ጌታ ከእመቤታችን ጋር ነው ያለው የገባላትን ቃልኪዳንም አይተውም በቃኪዳኗ ይጠብቀናል። አማላጅነቷ አይለየን።

የቅዳሴ ምንባብ

1ቆሮ 6፡9
2ተሰ 21:1
የሐዋ 7:44
ምስባክ፦ ሰወርከኒ በዕለተ ቀትል መልዕልተ ርእስየ
ኢትመጥወኒ እግዚኦ እምፍትወትየ ለኃጥእን
ተማከሩ ላዕሌየ ወኢትኅድገኒ ከመ ኢይዘኀሩ /መዝ 139:7/
ወንጌል ማቴ 18፡6-19

ቅዳሴ /ዘእግዝእትነ/

ሰኔ ዐሥራ ሁለት
መልአኩ ቅዱስ ሚካኤል አፎምያንና ባሕራን የረዳበት ዕለት

የዕለቱ የትምህርት ርእስ
« እስመ ለመላእክቲሁ ይኤዝዞሙ በእንቲአከ »
መላእክቱን ስለ አንተ ያዝዛቸዋል ። (መዝ 90+11)

በዚህ ዕለት ቅዱስ ሚካኤል በኪልቅያ አፎሚያ የምትባል ደግ ሴት ባሏ አስተራኒቆስ ይባላል። ከሀብቷ ከንብረቷ እየመጸወተች በጾም በጸሎት ተወስና ትኖር ነበር። ሰይጣን ለምቀኝነት አያርፍምና ደግ መነኩሴ መስሎ አጋንንትን መነኮሳይት አስመስሎ መጥቶ ከደጅ ሆኖ አስጠራት ከቤት ንብረቱ ወበቅዱስ ሚካኤል ስዕል ፊት ጸልዩልኝ አለቻቸው። "እኛማ በነግህ ጸልየናል" እንደው አንቺ ይህ ሁሉ ጾም ጸሎት ምን ያደርግልሻል? ሲበዛ ያለ ጊዜ እንደ ሚጉዳ አታውቂምን? ሀብትሽን ሰጥተሽ መጨረሻሽ ምንድ ነው ስትደኸሚ የሚረዳሽ የሚጦርሽ ልጅ የለሽ ሁለተኛ ማግባት ኃጢአት መስሎሻልን እነ አብርሃም እነ ዳዊት ከብዙ ሴቶች ብዙ ልጆች ወልደዋል አሁን ባል አግቢ እኔ የምልሽን እሽ በይኝ አለ "ኦ አባ እስኪ ማክ ሠናይ ወቃልከሰ አኩይ" አባ ቃልህ መልካም ነበረ ንግግርህ ግን ክፉ ነው ። አለችውና ባሏ በሕይወት እያለ ያሠራላትን የቅዱስ ሚካኤል ስዕል ከአስቀመጠችበት አውጥታ ብታሳየው ሰኔ 12 ቀን መጥቼ ከተመካሽበት ከዚህ ስዕል ጋር አጠፋሻለሁ ብሏት እንደ ትቢያ በኖ ጠፍቷል። ሰኔ 12 ቀን የብርሃን መልአክ መስሎ መጥቶ ጾም ጸሎትሽ ስግደትሽ ፣ምፅዋዕትሽ፣ አርጓል ። ላድንሽ መጥቻለሁና ስገጅልኝ አላት አንተማነህ? አለችው የመላእክት አለቃ ቅዱስ ሚካኤል ነኝ አላት የንጉሥ

መልእክት

በደግነትና በመልካምነት የታወቀችው አፎምያና በባሕር ውስጥ ተጥሎ የተገኘው ባሕራን በዛሬው ዕለት አምላካችን እግዚአብሔር መልአኩ ቅዱስ ሚካኤልን ልኮ ከጠላት እጅ ታድጓቸዋል ።

እኛም በሕይወታችን እግዚአብሔር ካከበራቸው በቁሎቹ የምንወድቅና የምንሞት ብንመስልም የማይጥለን አምላክ የሞታችንን ደብዳቤ ወደ ሕይወት እንደሚቀይርልን እምነን እንኑር ። የባሕራንንና የአፎምያ ወዳጅ ቅዱስ ሚካኤል በምልጃው ዘወትር ከኛ ጋር ይሁን ። አሜን

የቅዳሴ ምንባብ

ኤፌ 1፡13

ይሁዳ 1፡9

የሐዋ 1፡10

ምስባክ፦ ሰብ ትፈልጦሙ ለጠቢባን ይመውቱ

ወከማሁ ይትኃጕሉ አብዳን ወአልቦሙ ልብ

ወየኃድጉ ባዕድ ብዕሎሙ /መዝ 48:10/

ወንጌል ማቴ25፡14-31

ቅዳሴ /ዘያዕቆብ ዘሥሩግ

ሰኔ ዐሥራ ሰባት
አባ ገሪማ (ዘመደራ)

የዕለቱ የትምህርት ርእስ
እምነት ቢኖራችሁ ይህን ተራራ ወደዚያ
እለፍ ብትሉት ያልፋል!
(ማቴ 17:20)

በዛሬው ዕለት በ4ኛው ክፍለ ዘመን ወደ ኢትዮጵያ ከመጡት ከዘጠኙ ቅዱሳን አንዱ አባ ገሪማ (ዘመደራ) በዓላቸው የሚከበርበት ዕለት ነው። ቀደምት ስማቸው ይስሐቅ አባታቸው መስፍያኖስ እናታቸው ሰፍንግያ ይባላሉ። አባታቸው የሮም ንጉሥ ነበር። ከልጅነታቸው ጀምሮ መንፈሳዊ ትምህርት ሲማሩ በድቁና ሲያገለግሉ አድገዋል። ኋላም የአባታቸውን ሥልጣን ወርሰው ሰባት ዓመት ያህል ገዝተዋል። አባ ጴንጠሌዎን ዘጾማዕት ምድራዊ መንግሥት ያልፋል፤ ይጠፋል የማያልፈውን ሰማያዊ መንግሥት ትወርስ ዘንድ ፈጥነህ ወደ ኔ ና ብለው ላኩባቸው መልካም ባልንጀራ እንዲህ ነው ቅዱስ ገብርኤል በክንፉ ነጥቆ አክሱም አደረሳቸው ማዕረገ ምንኩስናን ተቀብለው በጾም በጸሎት ተወስነው ኖሩ።

ጻድቁ ከሠሯቸው ተአምር ከብዙ በጥቂቱ እንደሚከተለው ተገልጿል። መስከረም 30 ቀን በእድዋ ልዩ ቦታው ሰሩዳ ከሚባለው ተራራ ተአምር ሰርተዋል። ከሱ ትም መካከል በልተው ቀድሰዋል በሚል ሃሜት ሰዎች ሲያሙ ሰው ባይመሰክርልኝ እንጨቱና ድንጋዩ ይመስክር ብለው ሲሄዱ ካላቸው መንፈሳዊ ብቃት የተነሳ ሁለት ምዕራፍ ያህል ዕጽዋቱ እና ድንጋዮችን አስከትለው ተንቀሳቅሷል። ይህንን ታላቅ እና የሚያስደንቅ ተአምር እግዚአብሔር በእርሳቸው ላይ ስለሠራ ይህን የተመለከቱ ሁሉ ገሪማ ብለው ጠርተዋቸዋል። ትርጉሙም ግሩም የሆነ የሚያስገርም

መልእክተኛ ያለማንተም ይሄዳልን በተረ መስቀልህ ወዴት እለ አለችው እርሱም መልስ መስቀል አሊዮ መሳል ልማድ ነው እንጂ እኛ መላእክት አንይዝም አላት ቀኖና /ጠብቀኝ/ ስዕሉን ሳምሚልህ ብላ ወደ ቤቷ ዘወር ስትል መልኩን ለውጦ ጨለማ መስሎ ታያት ቅዱስ ሚካኤል እንደ ዐይን ጥቅሻ መጣ አፎምያን አረድቶ ጾምሽ፣ ጸሎትሽ ስግደትሽ፣ ምጽዋትሽ ቅድመ እግዚአብሔር ደርሷል ዕረፍትሽ ዛሬ ነው። ብሏት ከሷ ተሰወረ ወደ ቤተክርስቲያን ሄዳ ሥጋውንና ደሙን ተቀብላ ገንዘቧን ሁሉ መጽውታ በዚህ ዕለት በክብር አርፋለች።

ሁለተኛው በዚህ ዕለት የሚከበረው ባሕራን ነው

ሀገሩ እስክንድርያ ነው ወላጆቹ የቅዱስ ሚካኤልን በዓል እያከበሩ ይኖሩ ነበር። ባሕራን ተጸንሶ ሳለ አባቱ ሞቶ ባሕራን በተወለደ ጊዜ ሕፃኑን የመላእክት አለቃ ቅዱስ ሚካኤል ባረከው የዚህ የኀረቢትሽን የባለ ጸጋ ሐብት ይወርሳል ሲላት ባለ ጸጋው ኀረቢቷ ሰማ ነገሩን ከልቡ ሲያወጣ ሲያወርድ ቆይቶ ባሕራንን ዐሥር አመት ሲሆነው እናቱ የምታሰባስበው ቀርሳ የምትሰጠው እጥታ በጣም ተቸገረች ባለጸጋውም እኔ ወስጄ ለምን አላሳድገውም አላትና ለርሷ ሃያ ወቄት ወርቅ ሰጥቶ ወስደው ወዲያውም ሳጥን አሰርቶ በአሰራው ሳጥን ከቶ ከባሕር ጣለው ማዕበል እየገፋ ወስዶ ከወደብ አደረሰው አንድ በጎቹን የሚጠብቅ እረኛ አገኘው ከነጋዴ የወደቀ እቃ አገኘሁ ብሎ ከቤቱ ወስዶ ቢከፍተው መልከ መልካም ልጅ ይፈልግ ነበርና በጣም ደስ አለው ስሙንም ባሕራን ብሎ ጠራው ከባሕር የተገኘ ሲል ነው። ከበጎው እያበላ ከጠጣው እያጠጣ አሳደገው ከብዙ ዓመታት በኋላ ባሕር ላይ የጣለው ባለፀጋ ለንግድ ሲሔድ መሽቶበት ባሕራንን ባሳደገው ቤት አደረ ባሕራን ባሕራን እያለ ሲጠራው ባሕራን ማለት ምን ማለት ነው አለው። ከባሕር የተገኘ ማለት ነው መቼ አገኘኸው አለው ጊዜውን ጠቅሶ ሲነግረው በልቡ ለካ አልሞተም አለ ሲነጋ ከቤቱ

የራሳሁት እቃ አለና እባክህ ፍቀድልኝ ልጅህን ባሕራንን ልላከው ። የድካሙን ዋጋ ለአንተ እከፍላለሁ አለው፤ እሺ አለ እንደ ደረሰ ግደሉት ብሎ ደብዳቤ ጽፎ አትሞ ምልክት ነገሮ ስንቁን አስይዞ ላከው ዘጠኝ ቀን በእግሩ ተጉዞ የአንድ ቀን ጎዳና ሲቀረው ቅዱስ ሚካኤል በአምሳለ ሊቀ ሐራ በፈረስ ተቀምጦ መላእክትን እንደ ሠራዊት አስከትሎ ከመንገድ ላይ ተገናኘው አንተ ጎበዝ ወዴት ትሔዳለህ? መልእክት ተልኬ ላደርስ እየሔድኩ ነው። ብሎ መለሰለት እስኪ መልእክቱን አሳየኝ አለው ባሕራንም ደብዳቤውን አሳየው። እፍ ቢለበት የሞቱን ትዕዛዝ አጥፍቶ የሕይወት ትዕዛዝ ጽፎበታል። ደብዳቤውን ለቤቱ ሹም ሰጠው ቢገልጠው ልጄን ለላኩት ሰው ዳሩለት ሐብት ንብረቱን አውርሱት ባሮቼ ይገዙለት የሚል አነበበ ባሕራንም የባለጸጋውን ልጅ አግባ ባለ ጸጋውም ከንግድ ሲመለስ የዘፈን ጨዋታ ድምፅ ሰምቶ የምሰማው ድምፅ ዘፈን ጨዋታ ምን ተገኝቷል?። የላከው ሰው ልጅህን አግብቶ ሐብትህን ወርሶ ይኸው አርባ ቀን ሙሉ ይዘፈናል አለው ወዲያው ደንግጦ ከፈረሱ ወድቆ ሞተአል ባሕራንም የባለፀጋውን ሐብት ወርሶ እግዚአብሔርን እያመሰገነ ቅዱስ ሚካኤልንም እያከበረ ኖረ ።

ትምህርት

- እግዚአብሔር መላእክትን በመንገዳችን እንደሚልክልን (ዘጸ.23+ 20)
- በመልካም ሥራችን እንደማንወድቅ (መዝ.40+1)
- የጾምና የጸሎት የምጽዋት ጠቃሚታን (የሐዋ.9+31)
- የሞት ደብዳቤ ወደ ሕይወት እንደሚቀየር ማመን (መ.አስቴር 7+9 9+1)።

ትምህርት እና ሥራ የሚሠራ ማለት ነው። መጋቢት 17 ቀን በአንድ ቀን ስንዴ ዘርተው ብዕለቱ መከዋዕት አድርሰዋል። ይህንንም ታላቅ ኢትዮጵያዊው ሊቅ ቅዱስ ያሬድ ድጓ በተባለው መጽሐፉ ግንሀ ይዘርእ ኪህነቶ ወበርህ ያርር ገራህተ በማለት ዘምርላቸዋል። ግንቦት 17 ቀን አራቱ ወንጌላትን ጽፈዋል። በብራና ከተጻፉት ወንጌላት ቀዳሚነት አለው። እስከሁን ድረስ በገዳማቸው ይገኛል። ብዙ ተአምራትን እያደረጉ ጻድቁ አባታችን አቡነ ገሪማ ብዙ ድንቅ ድንቅ ነገር በማድረግ ቅዱሳት መጻሕፍትን ከተሰየ ቋንቋ ወደ ግእዝ በመተርጎም ሕመማንን እየፈወሱ በጾም፣ በጸሎት በብሕትውና ለ50 ዓመታት በመሠረቱት ገዳም ከተቀመጡ በኋላ ከፈጣሪያቸው ቃል ኪዳን ተቀብለው እንደነ ኤልያስና ሔኖክ በብሔረ ሕያዋን ተቀምጠዋል።

ትምህርት

- ታላቅ እምነት
  (ማቴ.17+20)
- ስለ እግዚአብሔር ዓለምን መተው
  «ዓለምን መውደድ ለእግዚአብሔር ጥል እንዲሆን አታውቁምን »
  (ያዕ 414)
- ለሚበልጠው ክብርና ለእግዚአብሔር ራስን መስጠት

መልእክት

ጻድቁ አባታችን አቡነ ገሪማ ሕይወታቸውን ሁሉ ለእግዚአብሔር በመስጠት በጾምና በጸሎት ሕይወት ተወስነው እግዚአብሔርን በማመስገን በንጽሕና እና በቅድስና ኖረዋል። እኛም እንደ ጻድቁ የእውነት ሰዎች መሆን ይገባናል። የጻድቁ አማላጅነት አይለየን።

ሰኔ ሃያ እና ሃያ አንድ
ሕንፀተ ቤተክርስቲያን

የዕለቱ የትምህርት ርእስ
ሐነፀ መቅደሶ በአርያም
«መቅደሱን በአርያም (በልዕልና) አነፀ» (መዝ77+69)

ቅዱስ ጳውሎስና በርናባስ ፊልጵስዩስ ገብተው የእግዚአብሔርን ቃል በስፋት አስተማሩ። ሕዝቡም እምነው ተጠመቁ ከዚህ በኃላ ወደ አምልኮ ጣዖት ቤት አትሂዱ አላቸው። እንደዚህ ካላችሁን የጸሎት ቤት ስጡን አሏአቸው። ለቅዱስ ጴጥሮስና ለቅዱስ ዮሐንስ መልእክት ላኩ ።«እልበ ዘትገብሩ ወኢምንተኒ ዘንበለ ትዕዛዙ ወምክሩ ለእግዚእ ኢየሱስ ክርስቶስ »ያለ ጌታችን ፍቃድ ምንም አንዳች ልታደርጉ አትችሉምና እንናተም ጸልዩ እኛም እንጸልያለን ብለው ላኩባቸው ሱባኤ ይዘው ሲጨርሱ አምላካችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በዚህ ዕለት ከሩቅና ከቅርብ ያሉትን ደቀ መዛሙርትን በደመና ጠቅሶ ፊልጵስዩስ ሰበሰባቸው ። በእናቱ ስም ጽንፍ እስከ ጽንፍ ቤተ ክርስቲያናት እንዲታነፁ ፍቃዱ ነውና ሕንፃ ቤተክርስቲያን ሳለያችሁ ሥርዓት ሳስተምራችሁ አላቸው። ይህንን ብሎ ወደ ምስራቅ ወስዷቸው ተራርቀው የነበሩ ሦስት ድንጋዮች በተአምራት አቀራርቦ ቁመቱን 24 ወርዱን 12 ክንድ አድርጎ ለእግዚአብሔር የሚሳነው ነገር የለምና ሦስቱ ድንጋዮች ፤ መቅደስ ቅድስት ቅኔ ማኅሌት ሆነው ተሰርተው ተገኝተዋል ። ይህ የሆነው እመቤታችን ባረገች ከአራት ዓመት በኋላ በዚህ ዕለት ነው ።

ትምህርት

- ለእግዚአብሔር የሚሳነው ነገር እንደሌለ ማመን ዘፍ.18+14፣ ሉቃ.1+37
- የደቀ መዛሙርቱ የእምነት ጥንካሬ 1ቆር.16+13፣ራእ.3+11

መልእክት

ለእግዚአብሔር የሚሳነው ነገር እንደሌለ በዚህ ዕለት ሦስት ድንጋዮችን በቃል ብቻ በማዘዝ ቤተ መቅደስ ተሠርቷል። እርሱ ሲናገር ባሕር፣ ምድር፣ሰማይ፣ ንፋስ በቃል ብቻ ሁሉም ይታዘዛል። ሁሉን የሚፈጽምና የሚያደርግ አምላክ ነውና ሰኔ ሃያ መቅደሱን ከሠራ በኋላ በ21 እመቤታችንን መንበር አድርጎ እርሱ ሠራዒ ካህን ቅዱስ ጴጥሮስን ተራዳኢ ካህን እስጢፋኖስን ሠራዒ ዲያቆን አድርጎ ቀድሶ አቁርቧቸዋል። የአምላክ ቸርነቱ አይለየን። አሜን!

የቅዳሴ ምንባብ

ኤፌ 2+13
1ቆር. 2+4
የሐዋ 1+12

ምስባክ- ቀደሰ ማኅደሮ ልዑል
እግዚአብሔር ውስተ ማዕከላ ኢትትሐወክ
ወይረድአ እግዚአብሔር ፍጽመ /መዝ 45፡4/

ወንጌል ማቴ 16፡13
ቅዳሴ/ ዘእግዚእ/

ሰኔ ሠላሳ

መጥምቁ ዮሐንስ የተወለደበት ዕለት

የዕለቱ የትምህርት ርእስ

«አንተ ሕፃን ሆይ የልዑል ነቢይ ትባላለህ» (ሉቃ1116)

በይሁዳ ንጉሥ በሄሮድስ ዘመን ከአብያ ክፍል የሆነ ዘካርያስ የሚባል ካህን በታማኝነትና በቅንነት እግዚአብሔርን የሚያገለግል ነበር። ሚስቱ ኤልሳቤጥ ከአሮን ልጆች ወገን ነበረች። ሁለቱም የእግዚአብሔርን ሕግ በመጠበቅ ነቀፌታ ያልተገኘባቸው ጻድቃን ነበሩ ሚስቱ ኤልሳቤጥ መካን ነበረች ልጅ አልነበራቸውም ሁለቱም በእድሜያቸው አርጅተው ነበር።

ካህኑ ዘካርያስ የአገልግሎት ተራው ደርሶት ሲያገለግል የጌታ መልአክ ቅዱስ ገብርኤል በዕጣኑ መሰዊያ ቀኝ ታየው፣ ዘካርያስም መልአኩን ባየው ጊዜ ደነገጠ፣ መልአኩም ጸሎትህ ተሰምቷል አትፍራ ሚስትህ ኤልሳቤጥ ወንድ ልጅ ትወልዳለች ስሙንም ዮሐንስ ትለዋለህ ደስታና ተድላ ይሆንልሃል አለው። ኤልሳቤጥም ፀነሰች የመውለጃዋ ጊዜ ደርሶ ዮሐንስን ወለደች ጎረቤቶቿቸውና ዘመዶቻቸውም ጌታም ለኤልሳቤጥ ምሕረቱን እንዳደረገላት ሰምተው ደስ አላቸው ።

ትምህርት

- ያለ ነቀፌታ በቅድስናና መኖር
  «ያለ ነቀፋ እየሄዱ በእግዚብሔር ፊት ጻድቃን ነበሩ" (ሉቃ.1+6)
- በእግዚአብሔር ቤት ደጅ መጥናት

«ቆይቼ እግዚአብሔርን ደጅ ጠናሁት እርሱም ዘንበል አለልኝ »(መዝ3911)

መልእክት

ለሕይወታችን የሚያስፈልገንን ሁሉ በጸሎት አምላካችንን በመጠየቅ ብንጸና ከሁሉ የተሻለ ነገር ከእግዚአብሔር እንቀበላለን ካህኑ ዘካርያስና ኤልሳቤጥ እግዚአብሔርን በማክበራቸው ተጠቅመዋል። እኛም የተዘጋብንን እንዲከፈትልን ያጣነውን ለመቀበል ዘወትር እንድንበረታ የእግዚአብሔር ቸርነት አይለየን። አሜን!

ሐምሌ አምስት

የቅዱስ ጴጥሮስና የቅዱስ ጳውሎስ በዓለ ዕረፍት

የዕለቱ የትምህርት ርእስ

«ስለ አንተ ቀኑን ሁሉ እንገደላለን»

(መዝ 43+22 ሮሜ 8+36)

የቅዱስ ጴጥሮስ ጥሪ

በገሊላ ባሕር አጠገብ አምላካችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሲመላለስ ሁለት ወንድማማቾች ጴጥሮስ የሚሉትን ስምዖንን ወንድሙንም እንድርያስ መረባቸውን ወደ ባሕር ሲጥሉ አየ እነ አጥማጆች ነበሩና እርሱም በኋላዬ ኑና ሰዎችን አጥማጆች እንድትሆኑ አደርጋችኋለው አላቸው። ወዲያው መረባቸውን ትተው ተከተሉት (ማቴ 4+18)

ባለትዳር ነበር

ጴርጥቃ የተባለች ሚስት ነበረችው አምላካችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ወደ ጴጥሮስ ቤት መጥቶ አማቱን በንዳድ ታማ ተኝታ አያት በእጇም ዳሰሳትና ንዳዱም ለቀቃት ተነሥታም አገለገለቻቸው። (ማቴ.8+14)

ቅዱስ ጴጥሮስ ከሚታወቅባቸው ነገሮች

- ቅዱስ ጴጥሮስ በገሊላ ባሕር ጌታ ሆይ አንተስ ከሆንህ በውኃው ላይ ወደ አንተ እንድመጣ እዘዘኝ አለው። እርሱም ና አለው ጴጥሮስም ከታንኳይቱ ወርዶ ወደ ኢየሱስ ሲደርስ በውኃው ላይ ሄደ ነገር ግን የነፋሱን ኃይል አይቶ ፈራ ሊሰጥም በጀመረ ጊዜ ጌታ ሆይ አድነኝ ብሎ ጮኸ ወዲያውም ኢየሱስ እጁን ዘርግቶ ያዘውና አንተ እምነት የጎደለህ ስለምን ተጠራጠርህ? አለው። (ማቴ14+28)
-
- ምሳም ከበሉ በኋላ ኢየሱስም ስምዖን ጴጥሮስን የዮና ልጅ ስምዖን ሆይ ከእነዚህ ይልቅ ትወደኛለህን አለው አዎን ጌታ ሆይ እንድወድህ አንተ ታውቃለህ አለው ግልገሎቼን አሰማራ አለው ሁለተኛም ትወደኛለህን አለው ጌታ ሆይ እንድወድህ አንተ ታውቃለህ ጠቦቶችን ጠብቅ አለው ሦስተኛ ጊዜም ትወደኛለህን ስላለው ጴጥሮስ አዘነና ጌታ ሆይ እንድወድህ ሁሉን አንተ ታውቃለህ አለው በጎቼን አሰማራ አለው (ዮሐ21+16)

ቅዱስ ጴጥሮስ በፊልጶስ ቂሣርያ

- ኢየሱስም ወደ ፊልጶስ ቂሳርያ አገር በደረሱ ጊዜ ደቀመዛሙርቱን ሰዎች የሰውን ልጅ ማን እንደሆነ ይሉታል ብሎ ጠየቀ እነርሱም አንዱ መጥምቁ ዮሐንስ ሌሎችም ኤልያስ፣ ኤርምያስ ወይም ከነቢያት አንዱ ነው ይላሉ አሉት። እርሱም እናንተስ እኔ ማን እንደሆንሁ ትላላችሁ? አላቸው ስምዖን ጴጥሮስ መልሶ አንተ ክርስቶስ የሕያው እግዚአብሔር ልጅ ነህ ብሎ መለሰ (ማቴ 16+17)

ቅዱስ ጴጥሮስ በደብረ ታቦር

- ጌታ ሆይ በዚህ መሆን ለኛ መልካም ነው ብትወድስ በዚህ ሦስት ዳስ እንዱን ለአንተ አንዱንም ለሙሴ አንዱንም ለኤልያስ እንሥራ ። (ማቴ 17+5)

ቅዱስ ጴጥሮስ የጸሎተ ሐሙስ ዕለት

- ደቀመዛሙርቱ ከዘመሩ በኋላ ወደ ደብረ ዘይት መጡ በዚያን ጊዜ ኢየሱስ በዚች ሌሊት ሁላችሁ በእኔ ትሰናከላላችሁ እረኛውን እመታለሁ የመንጋውንም በጎች ይበተናሉ የሚል ተጽፏል። (ማቴ 17+30)
- ደቀመዛሙርቱ ተኝተው አገኛቸው፣ ጴጥሮስን እንዲሁም ከኔ ጋር አንዲት ሰዓት ስንኳ ልትተጉ አልቻላችሁምን ወደ ፈተና እንዳትገቡ ትጉና ጸልዩ። (ማቴ.26+41)

ቅዱስ ጴጥሮስ ጌታን አላውቀውም ስለ ማለቱ

- ጴጥሮስም ከቤት ውጭ ባጥሩ ግቢ ተቀምጦ ነበር አንዲት ገረድም ወደ እርሱ ቀርባ አንተ ደግሞ ከገሊላው ከኢየሱስ ጋር ነበርህ አለችው እርሱ ግን የምትይውን አላውቀውም ብሎ በሁሉም ፊት ካደ (ማቴ26+69)
- ቅዱስ ጴጥሮስ በንስሐ መመለሱ
  (ማቴ 27+75)

ችኩልና (ፈጣን) ነበር

- ጌታችን አምላካችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ስለ ሞቱና ትንሣኤው ሲናገር አይሁንብህ ጌታ ሆይ ይህ ከቶ አይድረስብህ ብሎ ሊገሥጸው ጀመረ (ማቴ 16+26)

ተአምራትን ያደርግ ነበር

- ልምሾ ሆኖ የተወለደውን በኢየሱስ ስም ተነሣና ተመላለስ ብሎ ፈውሶታል (የሐዋ3+8)
- በልዳ ኤንያ የተባለ የስምንት ዓመት የአልጋ ቁራኛ ፈውሷል (የሐዋ 9+23)

- መንፈስ ቅዱስን በገንዘብ እገዛለሁ ያለውን ሲሞን መሰሪን ገስጿል (የሐዋ 8+21)
- ሐናንያና ሚስቱ ሰጲራን ገስጿል (የሐዋ 5+5)

ቅዱስ ጴጥሮስና የስብከት አገልግሎቱ

በዓለ 50 በተባለው ቀን ድምጹንም ከፍ አድርጎ እንዲህ ሲል ተናገራቸው አይሁድ በኢየሩሳሌም የምትኖሩ ሁላችሁ ይህ በእናንተ ዘንድ የታወቀ ይሁን ቃሉንም አድምጡ በማለት ሦስት ሺህ ሕዝብ አስተምሮ አሳምኗል። (የሐዋ 2+14)

በሰማርያ በአንጾኪያ፣ በጳንጦስ፣ በገላትያ፣ በቀጰዶቅያ፣ በቢታንያ አስተምሮ አንደኛና ሁለተኛ መልእክትም ጽፏል።

የቅዱስ ጳውሎስ ጥሪ፣

ቅዱስ ጳውሎስ የመጀመሪያ ስሙ ሳውል በእብራይስጥ ቋንቋ ጸጋ እግዚአብሔር ማለት ነው በሮማይስጥ ቋንቋ ብርሃን ማለት ነው። ጳውሎስ ንዋይ ኅሩይ (ምርጥ ዕቃ) ማለትም ነው። ጌታችን አምላካችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ስለ ጳውሎስ ለሐናንያ ከመሰከረለት ጊዜ- "ይህ በአሕዛብም በነገሥታትም በእስራኤልም ልጆች ፊት ስሜን ይሸከም ዘንድ ለእኔ የተመረጠ ዕቃ ነውና ሂድ፣" (ዮሐ፣ 9+15)። ጳውሎስ ማለት አመስጋኝ፣ ደስታ፣ ምዑዝ ነገር የሚናገር ልሳነ ክርስቶስ፣ ሰላም ፣ ፍቅር ማለት ነው።

የቅዱስ ጳውሎስ የልጅነት ጊዜው፣

ቅዱስ ጳውሎስ የተወለደው በጠርሴስ ነው፣ (የሐዋ 21+39)። በዚያ ዘመን አምስት መቶ ሺህ ሰው ይኖርባት ነበር። ድንኳን መስፋትን የተማረው በዚያ ነው። (የሐዋ 13+3)። የሮም ዜግነትን የወረሰው ከአባቱ ነው። (የሐዋ 22+26)። አባቱ የሮም ዜግነት ይኑረው እንጂ ከብንያም ወገን የሆነ ፈሪሳዊ

ነበረ። (የሐዋ23+6 በፊልጵስዩስ መልእክቱ፡- «በስምንተኛው ቀን የተገረዝሁ ከእስራኤል ትውልድ፣ ከብንያም ወገን፣ ከዕብራውያን ዕብራዊ ነኝ፣ ስለ ሕግ ብትጠይቁኝ ፈሪሳዊ ነበርሁ፣ በሕግ ስለሚገኝ ጽድቅ ያለ ነቀፋ ነበርሁ።» ያለው ለዚህ ነው። (ፊል 3+5)። ከታላቁ መምህር ከገማልያል እግር ስር ሆኖ ሕገ ኦሪትን እና የአይሁድን ወግ ጠንቅቆ ተምሯል።(የሐዋ 22+3)።

የቅዱስ ጳውሎስ አጠራር

የተጠራው ከደማስቆ ጉዳና ነው። በደማስቆ ላሉ ምኩራቦች የተጻፈ የትእዛዝ ደብዳቤ ከሊቀ ካህናቱ ተቀብሎ፣ ወንዶችንም ሴቶችንም እያሰረ፣ ወደ ኢየሩሳሌም ለማምጣት ይተጋ ነበር። (ለሕገ ኦሪት ቀንቶ ክርስቲያኖችን ያሳድድ ነበር)። ወደ ደማስቆ በቀረበ ጊዜ፡- ድንገት በእርሱ ዙሪያ ብርሃን አንጸባረቀ፣ በምድርም ላይ ወደቀ። «ሳውል፣ ሳውል፣ ለምን ታሳድደኛለህ?» የሚለውን ድምፅ ሰምቶም፡- «አንተ ማን ነህ?» አለ። እርሱም፡- «አንተ የምታሳድደኝ እኔ ኢየሱስ ነኝ፣ የመውጊያውን ብረት ብትቃወም በአንተ ይብስብሃል፣ «ጌታ ሆይ፣ ምን አደርግ ዘንድ ትወዳለህ?» አለው። ጌታም «ወደ ከተማ ግባና ታደርገው ዘንድ የሚያስፈልግህን ይነግሩሃል፣» አለው። ሳውል፡- ሦስት ቀን ማየት ተሳነው፣ እንጀራ አልበላም፣ ውኃም አልጠጣም። ጌታም ለሐናንያ በራእይ ተገለጠ፡- «ሳውልን አግኘው፣ እርሱ ይጸልያል፣ ሐናንያ የሚባል ሰው እጁን ሲጭንበት ሲፈወስም አይቷል፣» አለው። ሐናንያም፡- «ጌታ ሆይ፣ በኢየሩሳሌም በቅዱሳንህ ላይ ስንት ክፉ እንዳደረገ ስለዚህ ሰው ከብዙዎቹ ሰምቻለሁ፣ ስምህን የሚጠሩትን ለማሰር ከካህናት ሥልጣን አለው።» አለ። ጌታም፡- «በሁሉ ፊት ስሜን ይሸከም ዘንድ ለእኔ የተመረጠ ዕቃ ነውና፣ አትፍራ፣» አለው። በመጨረሻም ሐናንያ ሳውልን አግኝቶት ሲጸልይለት እንደ እንጨት ቅርፊት ያለ ከዓይኑ ላይ ወደቀለት።(የሐዋ9+1-18) ።

የቅዱስ ጳውሎስ የስብከት አገልግሎቱ

«አይሁድም ደከምሁ፣ ብዙ ጊዜ ተገረፍሁ፣ ብዙ ጊዜም ታሰርሁ፣ ብዙ ጊዜም ለሞት ተዘጋጀሁ። አይሁድ አንዲት ስትቀር አርባ ጊዜ እርባ እርባ ገረፉኝ። ሦስት ጊዜ በበትር ደበደቡኝ፣ አንድ ጊዜ በድንጋይ መቱኝ፣ መርከብ ሦስት ጊዜ ተሰበረችኝ፣ በጥልቁ ባሕር ውስጥ ሌሊትና ቀን ዋልሁ። በመንገድ ዘወትር መከራ እቀበል ነበር፣ በወንዝም መከራ ተቀበልሁ፣ወንበዴዎችም አሠቃዩኝ፣ ዘመዶቼም አስጨነቁኝ፣ አሕዛብ መከራ አጸኑብኝ፣ በከተማ መከራ ተቀበልሁ፣ በበረሃም መከራ ተቀበልሁ፣ በባሕርም መከራ ተቀበልሁ፣ ሐሰተኞች መምህራን መከራ አጸኑብኝ፣ በድካምና በጥረት፣ ብዙ ጊዜም ዕንቅልፍ በማጣት፣ በመራብና በመጠማት፣ አብዝቶም በመጾም፣ በብርድና በመራቆት ተቸገርሁ።» ብሏል። (2ኛ ቆር 9+23) አደራ ይከብደው፣ ኃላፊነት ይሰማው ነበር፣

- «ወንጌልን ባልሰብክ ወዮልኝ፣» (1ኛ ቆር 9+16)
- «ለግሪክ ሰዎችና (ለአረማውያንና) ላልተማሩ ለጥበበኞችና ለማያስተውሉትም ሁሉ እስተምር ዘንድ ዕዳ አለብኝ። ይልቁንም በሮሜ ላላችሁ ለእናንተ ወንጌልን ላስተምራችሁ እተጋለሁ።» ብሏል። (ሮሜ 1+14) የሚያስጨንቀው የአብያተ ክርስቲያናት ጉዳይ ነበር፣ «የቀረውንም ነገር ሳልቆጥር ዕለት ዕለት የሚከብደኝ የአብያተ ክርስቲያናት ሁሉ አሳብ ነው።» ብሏል። (2ኛ ቆር 11+29)። ትሑት ነበር፣

«ፍለጋ የሌለውን የክርስቶስን ባለጠግነት ለአሕዛብ ሁሉ እሰብክ ዘንድ፣ ሁሉንም በፈጠረው በእግዚአብሔር ከዘለዓለም የተሰወረው የምሥጢር ሥርዓት፣ ምን እንደሆነ እገልጥ ዘንድ ይህ ጸጋ ከቅዱሳን ሁሉ ይልቅ ለማንስ ለእኔ ተሰጠ።» ብሏል። (ኤፌ 3+8)።

• ትእግሥተኛ ነበር!

- «እስከዚህ ሰዓት ድረስ እንራባለን እንጠማለን እንራቆታለን እንጎሰማለን እንንከራተታለን፥ በገዛ እጃችን እየሠራን እንደክማለን ሲሰድቡን እንመርቃለን ሲያሳድዱን እንታገሣለን ክፉ ሲናገሩን እንማልዳለን እስከ አሁን ድረስ የዓለም ጥራጊ የሁሉም ጉድፍ ሆነናል።» ብሏል። (1ኛ ቆሮ 4+11)።

ታማሚ ነበር!

«ስለዚህም በመገለጥ ታላቅነት እንዳልታበይ፥ የሥጋዬ መውጊያ፦ (የጎን ውጋትና የራስ ምታት)፦ እርሱም የሚጎስመኝ የሰይጣን መልእክተኛ ተሰጠኝ፥ ይኸውም እንዳልታበይ ነው። ስለዚህ ነገር ከእኔ እንዲለይ ሦስት ጊዜ ጌታን ለመንሁ፤ እርሱም ጸጋዬ ይበቃሃል፥ ኃይሌ በድካም ይፈጸማልና አለኝ።» ብሏል። (2ኛ ቆሮ 12+8)።

የቅዱስ ጳውሎስ የድንግልና ሕይወት!

«ነገር ግን ያላገቡትንና አግብተው የፈቱትን እንደ እኔ ሆነው ቢኖሩ ይሻላቸዋል እላለሁ። (እንደኔ ከሴት ርቀው፥ ንጽሕና ጠብቀው ቢኖሩ ይሻላቸዋል ብዬ እነግራቸዋለሁ)።» ብሏል። (1ኛ ቆሮ 7+8)።

ተአምራትን ያደርግ ነበር!

በልስጥራን አንካሳውን አርትቷል። (የሐዋ 14+8)። አውጤኪስ የሚሉትም አንድ ጎበዝ በመስኮት ተቀምጦ ታላቅ እንቅልፍ እንቅላፍቶ ነበር። ጳውሎስም ነገር ባስረዘመ ጊዜ እንቅልፍ ከብዶት ከሦስተኛው ደርብ ወደ ታች ወድቆ ሞቶም አነሡት። ቅዱስ ጳውሎስም በጸሎት አስነሣው። የሐዋ ፳፡፱። በልብሱም ይፈውስ ነበር። (የሐዋ 19+11)።

ዕለተ ሞቱን ይናፍቅ ነበር!

«በእነዚህም በሁለቱ እጨነቃለሁ፤ ልሄድ ከክርስቶስም ጋር ልኖር እናፍቃለሁ፥ ከሁሉ ይልቅ እጅግ የሚሻል ነውና፤ ነገር ግን በሥጋ መኖሬ ስለ እናንተ እጅግ የሚያስፈልግ ነው። ይህንም ተረድቼ በእናንተ ዘንድ እንደኖር ስለ መሆኔ በእኔ መመካታችሁ በክርስቶስ ኢየሱስ ይበዛ ዘንድ፥ በእምነት ታድጉና ደስ ይላችሁ ዘንድ እንድኖር ከሁላችሁም ጋር እንድቆይ አውቃለሁ።» ብሏል። (ፊል 1+23)።

ዕለተ ሞቱን ያውቅ ነበር!

«ነገር ግን መንፈስ ቅዱስ፦ በየከተማው መከራና እስራት ይጠብቅሃል ብሎ ይመሰክርልኛል። ነገር ግን የእግዚአብሔርን የጸጋውን ወንጌል እንዳስተምር ከጌታችን ከኢየሱስ ክርስቶስ የተቀበልሁትን ሩጫዬን እንድጨርስና መልእክቱንም እንድፈጽም ነው እንጂ ለነፍሴ ምንም አላሳሳትም። አሁንም እነሆ የእግዚአብሔርን መንግሥት የሰበክሁላችሁ እናንተ ሁላችሁ ከእንግዲህ ወዲህ ፊቴን እንደማታዩኝ እኔ አውቃለሁ።» (የሐዋ 20+23)።

- «ስምን እንዲህ ታደርጋላችሁ? እያለቀሳችሁ ልቤን ትሰብሩታላችሁ፤ እኔ እኮ ተስፋ የማደርገው መከራንና እግር ብረትን ብቻ አይደለም፤ እኔ ግን በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ስም በኢየሩሳሌም ለመሞትም የቆረጥሁ ነኝ፤» አለ። (የሐዋ 21+23)።

ቅዱስ ጳውሎስ ከሲላስ ጋር በእስር ቤት!

እየጠንቆለች ለጌቶቿ ብዙ ገንዘብ የምትሰበስብ አንዲት የቤት ሠራተኛ ነበረች። ቅዱስ ጳውሎስን እና ሲላስን እየተከታተለች፦ «የመዳንን መንገድ

የቅዳሴ ምንባብ
1ተሰ 4፥13
2ዕ 1፥1
የሐዋ 23፥10
ምስባክ፦ ወበኃቢየሰ ፈድፋደ ክቡራን አዕርክቲከ እግዚኦ
ወፈድፋደ ጸንዑ እምቀደምቶሙ
እኄልቆሙ እምኆጻ ይበዝኁ /መዝ፣17/
ወንጌል ዮሐ 21፥15-20
ቅዳሴ /ዘሐዋርያት/

ሐምሌ ሰባት

ቅድስት ሥላሴ ወደ አብራሃም

ቤት የገቡበት ዕለት

የዕለቱ የትምህርት ርእስ

በፊትህ ሞገስ አግኝቼ እንደሆን ባሪያህን አትለፈኝ?
(ዘፍ18+3)

አብርሃም ማለት አበ ብዙኃን ማለት ነው። ትውልዱም ከነገደ ሴም ነው አባቱ ታራ ይባላል የእሳም ሃያ አንደኛ ትውልድ ነው። ቤቱን ከተመሳቀለ ጎዳና መርቶ የወጣ የወረደውን ያለፈውን ያገደመውን ሰው በእንግድነት ሊቀበል ይኖር ነበር። ሰይጣን ከዕለታት አንድ ቀን እራሱን በአብርሃም የተደበደበ አስመስሎ ከመንገድ ላይ ወድቆ እምሳል ቀጥ ብሎ እንግዶችን

ወዱት ትጠላላችሁ; እያለ ይጠይቃቸው ጀመር ርቦን እንዲያበላን ጠምቶን እንዲያጠጣን ከአብርሃም ዘንድ ይሉታል። የድሮው አብርሃም መሰላችሁ እንዴ! እኔም እንደናንተ ርቦኝ ያበላኛል ጠምቶኝ ያጠጣኛል ብዬ ብሄድ እራሴን ደብድቦኝና ገምሶ አባረረኝ እያለ ሰዎችን ሁሉ ወደ አብራሃም ቤት እንዳይሄዱ ሦስት ቀን ሙሉ እንግዳ ከለከለበት። አብርሃምም ያለ እንግዳ እህል አልበላም ውሃም አልጠጣም ብሎ ሦስት ቀን ቆየ በሦስተኛው ቀን በቀትር በድንኳኑ ደጃፍ ተቀምጦ ሳለ እግዚአብሔር በመምሬ የአድባር ዛፍ ተገለጠለት አይኑንም አነሣና እነሆ ሦስት ሰዎችን በፊቱ ቆመው አየ። ባያቸውም ጊዜ ሊቀበላቸው ከድንኳኑ ደጃፍ ተነስቶ ሮጦ ወደ ምድርም ሰገደ እንዲህም አለ ገቦሎ አጋዕዝትየ ቤተ ገብርክሙ ከቤት ገብራችሁ ዕረፉ አላቸው ደክመናልና እዘዘን አሉት እንዲያን አዝሎ ቢገባ ሁሉቱ በገበር አምሳያ ገብተው ተገኝተዋል አብርሃምም ሦስት እንደሆኑ አውቆ ሣራን 3 መስፈሪያ ዱቄት ወስደሽ አንድ እንጎቻ አድርገሽ ጋግሪው አላት ሣራም ጋግራ አቀረበች። አብርሃም ሥላሴን በአንድነት በቤቱ ተቀበለ።

ትምህርት

- እንግዶችን በቤታችን ለመቀበል ዘወትር መዘጋጀት
- እንዳንዶች ሳያውቁ መላእክትን እንግድነት ተቀብለዋል (ዕብ13+1)
- እንግዶችን መቀበል ከእግዚአብሔር ዋጋ እንዳለው ማወቅ ሮሜ.4+37
- አብርሃም እንግዳ በመቀበሉ በረከትን አግኝቷል መካን የነበረችው ሚስቱ ሣራም ልጅ ወልዳች (ዘፍ.21+1)

የሚነግሩአችሁ እነዚህ ሰዎች የልዑል አምላክ ባሪያዎች ናቸው፤» ብላ ትጮህ ነበር። ይህንንም እጅግ ብዙ ቀን አደረገች። ጳውሎስ ግን ተቸገረና ዘወር ብሎ መንፈሱን፦ «ከእርሷ እንድትወጣ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም አዝሃለሁ አለው፤» በዚያም ሰዓት ወጣ። ጌቶቿም፦ የትርፋቸው ተስፋ እንደወጣ ባዩ ጊዜ፦ ጳውሎስን እና ሲላስን በሹማምንት ፊት ጉትተው አቀረቡአቸው፤ ወደ ገገርዎችም አቅርበው፦ «እነዚህ ሰዎች አይሁድ ሆነው ከተማችንን እጅግ ያናውጣሉ። እኛም የሮሜ ሰዎች ሆነን እንቀበላቸውና እናደርጋቸው ዘንድ ያልተፈቀደልንን ልማዶች ይናገራሉ፤» በማለት ክሱን ፖለቲካዊ አደረጉት። ሕዝቡም ተባብራቸው፥ ልብሳቸውንም ገፍፈው በበትር ደብድበው ወደ ወኅኒ ጣሏቸው።

በወኅኒም ከግንድ ጋር አጣብቀው አሰሯቸው። መንፈቀ ሌሊትም ሲሆን እየጸለዩ እግዚአብሔርን በዜማ አመሰገኑ፥ እስረኞቹም ያዳምጡአቸው ነበር። በዚህን ጊዜ የወኅኒው መሠረት እስኪናወጥ ድረስ የምድር መንቀጥቀጥ ሆነና ደጆቹ ሁሉ ተከፈቱ፥ የሁሉም እስራት ተፈታ። ጠባቂውም ከእንቅልፉ ሲነቃ እስረኞቹ ያመለጡ መሰለው፦ ራሱን ለመግደል ሰይፉን መዘዘ። ቅዱስ ጳውሎስ ግን፦ «ሁላችን ከዚህ አለንና በራስህ ክፉ ነገር አታድርግ!» ብሎ ጮኸ። መብራትም ለምኖ ወደ ውስጥ ሮጦ፥ እየተንቀጠቀጠም ለጳውሎስና ለሲላስ ሰገደ፤ ወደ ውጭም አውጥቶ «ጌቶቼ ሆይ፥ እድን ዘንድ ምን ማድረግ ይገባኛል?» አላቸው። እነርሱም፦ «በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ እመን፤ አንተና ቤተሰቦችህ ትድናላችሁ፤» አሉት። ወንጌልንም አስተማሩት፤ በሌሊትም በዚያች ሰዓት ወስዶ ቁስላቸውን አጠባቸው፥ ስብራታቸውን አሰረላቸው፥ ከቤተሰቦቹም ሁሉ ጋር ተጠመቀ፥ ማዕድም አቀረበላቸው፤ በእግዚአብሔርም ስላመነ ከቤተሰቦቹ ሁሉ ጋር ሐሴት አደረገ። (የሐዋ.20+16-34)።

ትምህርት

- ሁሉን ትቶ ክርስቶስን መከተል
  (ማቴ.4+18፣ ሮሜ.10+9)
- ስለ ክርስቶስ እየኖሩ መመስከር
  (ሮሜ.10+9)
- ቀንዋዎቻችንን ማሰብ
  (ዕብ.13+7)
- የእግዚአብሔር እጅ ከእኛ ጋር መሆኑን ማወቅ
  1ጴጥ.5+11 ፣1+8
- የማይጠፋ አክሊል እንደሚጠብቀን ማወቅ
  1ቆሮ.9+25

መልእክት

ቅዱስ ጴጥሮስ እና ቅዱስ ጳውሎስ ስለአመኑት ጌታ ስለ እውነት መስክረውና ያላመኑትን በማሳመን ያሕዛብን ጣዖታት በመደምሰስ እውነተኛ የክርስቶስ ታማኝ አገልጋይ ሆነዋል። በሕይወታቸውም ጭምር በማስተማር የኔሮንን ቁጣር ዛቻና ማስፈራራት እንኳን ምንም ሳይፈሩ እውነተኛ ምስክር በመሆን ቅዱስ ጴጥሮስ ቁልቁል ተሰቅሎ ቅዱስ ጳውሎስ አንገቱ ተሠይፎ ሁለቱም በዚህ ዕለት አርፈዋል። እውነተኛ የክርስቶስ ምስክር ከሆኑት ከቅዱስ ጴጥሮስና ከቅዱስ ጳውሎስ ሕይወት የምንማረው እውነተኛ ምስክር መሆንና ስለ ቤተክርስቲያን ማሰብ ይገባናል። ስለ ኑሮ ብቻ እያሰብን ከሆነ እውነተኛ እረኛ ሳንሆን ምንደኞች መሆናችን አይጠቅምምና ወደ እግዚአብሔር ተመልሰን እውነተኛ እረኛ እና ምስክር እንድንሆን አምላካችን ይርዳን።

የቅዱስ ጴጥሮስና የቅዱስ ጳውሎስ በረከታው አይለየን። አሜን !

መልእክት

አባታችን አብርሃም ደግ እንግዶች ወደ ቤቱ ካልመጡ እህል የማይበላና ውኃ የማይጠጣ ሰው ስለነበረ እግዚአብሔር ባርኮታል፤ ዘሩንም እንደምድር አሸዋ አበዝቶለታል። እኛም እንግዶችን በመቀበል ያለንን በማካፈል ወደ ኋላ እንዳንል ያማከውን! የምናገኘው ተስፋ የቆረጠን ተስፋችን የሚቀጥለው አይሳካልንም ያለነው የሚሳካው፤ የተዘጋብን የሚከፈትልን በእምነት ስንኖርና እንደ አብራሃም እንግዶችን በመቀበልና በማስተናገድ የምንጠብቀውን ተስፋ ባዓይናችን የምናየው በእምነት እየኖርን የእግዚአብሔርን እንግዳ ስንቀበል ነው።
የእግዚአብሔር በረከትም እንዳያልፈን አምላካችን በቸርነቱ ይርዳን። አሜን!

የቅዳሴ ምንባብ

ሮሜ 9+1

1ዮሐ 4+11

የሐዋ 11+11

ምስባክ፦ ወሐሠሥኩ ገጸከ

ገጸ ዚአከ እሐሥሥ እግዚኦ

ወኢትሚጥ ገጸከ እምኔየ /መዝ 26+8

ወንጌል ዮሐ 8+51

ቅዳሴ /ዘዲዮስቆሮስ/

ሐምሌ ዐሥራ ዘጠኝ

ቅዱስ ቂርቆስና እናቱ ኢየሉጣ ከፈላ ውኃ
የዳኑበት ዕለት

የዕለቱ የትምህርት ርእስ

አንበሳከነ ማእከለ እሳት ወማይ

በእሳትና በውኃ መካከል አሳፍን (መዝ65+12)

ቅዱስ ቂርቆስ ሀገሩ ሮም/ ጣሊያን/ እንገቤን ነው አባቱ ቆዝሚስ እናቱ ኢየሉጣ ይባላሉ። በዘመነ ሰማዕታት በዉኃንና በአረመኔው በዲዮቅልጥያኖስ ዘመነ መንግስት አዋጅ ታውጆ ነበር

«አብያተ ጣዖታት ይትረኃዋ አብያተ ክርስቲያናት ይትዐጸዋ» ብሎ በ303 ዓ.ም አዋጅ አወጀ። በዚህ ምክንያት ብዙ ክርስቲያኖች ተሰደዱ ቅድስት ኢየሉጣም የ3 አመት ሕፃን ልጇን ቂርቆስን ይዛ ወደ ኢቆንዮን ሸሸች።

ንጉሡ እለእስክንድሮስን አስጠርቶ ክርስቶስን ካጂ ለጣዖት ስገጂ አላት በእጅህ ሠርተህ ላቆምከው ምስል አልሰግድም አለች እንጂ ካልሽ በሰይፍ ትቆረጫለሽ ብሎ አስፈራራት እርሷ ግን ምንም አልፈራችም እምነቷ ጠንካራ ነውና በብረት ጋን ውኃ አፍልታችሁ ከዚያ ውስጥ ጣሏቸው ብሎ አዘዘ «ድምጹ ለጽህርት ከመነጎድጓደ ክረምት» የውኃው ፍላት እንደ ክረምት ነጎድጓድ 15 ክንድ ያክል ወደላይ ይፈላ ነበር! በፈላው ውኃ ሊጨምሯቸው ሲወስዷቸው የኢየሉጣ ልቧ በፍርሃት ታወከ በቂርቆስ ላይ መንፈስ ቅዱስ አድሮ የእናቱን ፍርሓት አስወገደ። እናቱ ሆይ በርቺ ጨክኚ ዘእድኃኖሙ ለአናንያ ወአዛርያ ወሚሳኤል ውእቱ ያድኅነነ አናንያ አዛርያ ሚሳኤልን ያዳነ አምላክ ያድነን የለምን? እያለ እናቱን እያጸናናና

እያጽናና ልብሷንም ቅየንተተ ከእሳቱ ቀረቡ እርሷም ጨክና በፍጹም ልቧ ተያይዘው ከፈላው ውኃ ገብተዋል። የመሰከሩለትንና ያመኑትን የማይተው አምላክ ቅዱስ ገብርኤልን ልኮ በበትረ መስቀሉ እሳቱን አጥፍቶ የፈላውን ውኃ አቀዝቅዞ አዳናቸው።

ትምህርት

- ጽኑዕ እምነት

(1ዮሐ 5+47)

ቅዱስ ቂርቆስ እና ቅድስት ኢየሉጣ በፈላ ውኃ የተጨመሩት በእግዚአብሔር ላይ ጽኑዕ እምነት ስለነበራቸው ነው

«ያለ እምነት እግዚአብሔረን ደስ ማሰኘት አይቻልምና »

(ዕብ11+6)

- የመልአኩ የቅዱስ ገብርኤል ተራዳኢነትን

«ሁሉ መዳንን ይወርሱ ዘንድ ስላሉቸው ለማገዝ የሚላኩ የሚያገለግሉ መናፍስት አይደሉምን» (ዕብ1+14 መዝ33+7)

መልእክት

ቅድስት ኢየሉጣና ሕፃኑ ቂርቆስ በእምነት ሆነው ለጣዖት አንሰግድም በማለታቸው በፈላ ውኃ ውስጥ እንዲጨምሩ ቢታዘዝም እግዚአብሔር መልአኩ ቅዱስ ገብርኤልን ልኮ በፈላ ውኃና በእሳት መካከል አሳልፎ አዳናቸው

- በዚህ ዘመን የምንኖር እኛስ በእምነታችን ጸንተን የምንኖርና የምንመሰክር ስንቶቻችን ነን? እንደ ቂርቆስና ኢየሉጣ ፍጹም እምነት ና ጽዕናት ሊኖረን ያስፈልጋል። የቅዱሳን የእምነታቸው ጽዕናት አይለየን ።

የቅዳሴ ምንባብ
ዕብ 11፡33
1ዕብ 4፡12
የሐዋ 23፡10

ምስባክ፡- ይትኃፈሩ ኵሎሙ እለ ይሰግዱ ለግልፎ
ወእለ ይትሜክሁ በአማልክቲሆሙ
ወይሰግዱ ሉቱ ኵሉሙ መላእክቲሁ /መዝ 97፡10/

ወንጌል ማቴ 11፡25
ቅዳሴ ያዕቆብ ዘሥሩግ

ነሐሴ ሰባት
እመቤታችን ቅድስትድንግል ማርያም
የተፀነሰችበት ዕለት

የዕለቱ የትምህርት ርእስ
አንቺ ከሴቶች መካከል የተባረክሽ ነሽ።
(ሉቃ1+28)

እያቄም ቴክታ፤ በጥሪቃ ይባሉ እጅግ ባለጸጋ ነበሩ። ብዙ የወንድ አገልጋይና የሴት አገልጋይ ነበራቸው። የቀንድ ከብት፤ የጋማ ከብት የነበራቸው ባለጸጎች ነበሩ። ከወርቁ ብዛት የተነሳ እንደቀለበት እንበር እያሰሩ ከበሬውና ከላሙ ቀንድ እያደረጉ ይህንን ያህል የወርቅ ቀንድ ይህን ያህል የብር ቀንድ አለን ይሉ ነበር ሃብታችንና ንብረታችን ብዙ ነው የወለድነው ልጅ የለንም ለማን ይሆናል እያሉ ሲነጋገሩ በጥሪቃ እግዚአብሔር ልጅ ከኔ ባይሰጥህ ከሌላ ይሰጥህ ይሆናል አንዳተህ አትወልድምን፤ አለችው ሕያው እግዚአብሔርን አላደርገውም አለት።

ነሐሴ ዐሥራ ሦስት
ደብረ ታቦር

የዕለቱ የትምህርት ርእስ
በዚህ መሆን ለኛ መልካም ነው (17+4)

የታቦር ተራራ ከገሊላ ባሕር በምዕራባዊ ደቡብ በኩል 10.ኪሜ ርቆ የሚገኝ ተራራ ነው። የተራራው ከፍታ ከባሕር ወለል እስከ 572ሜትር ከፍ ያለ ሲሆን በዚህ ተራራ በባሱይ ኪዳን ባርቅ ሲግራን ያሸነፈበት (መሳ.4+614) ሳኦልም በሳሙኤል ትንቢት መሠረት ከሦስት ሰዎች ጋር የተገናኘበት (1ሳሙ.10+13) ስፍራ ነው። በአዲስ ኪዳን ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ክብሩን የገለጠበት ተራራ ነው።

ከስድስት ቀን በኋላ ጴጥሮስና ያዕቆብ ወንድሙን ዮሐንስን ወደ ረጅም ተራራ ይዟቸው ወጣ ወተወለጠ ራእዩ በቅድሜሆሙ ወአብርሀ ገጹ ከመ ፀሐይ ወአልባሲሁኒ ኮነ ጸዓዳ ከመ በረድ አርአያው ተለውጦ ፊቱ እንደ ፀሐይ አበርቶ ልብሱ እንደ በረዶ ነጭ ሆነ በሲና ተራራ 570 ጊዜ ያነጋገረው ሙሴና ኤልያስ በቀኝ በግራ ሆነው ለደቀመዛሙርቱ ታያቸው ሙሴና ኤልያስን ለምን አመጣቸው ቢሉ ሙሴ 570 ጊዜ ቃል ለቃል ተነጋርረዋል ባይህ እወዳለሁ ብሎ ነበር። አልቦ ዘይሬኢ ገጽየ ወየሐዩ እስተ ሰዓተ እም ዘሕይወቱ በዳበ ምድር ፊቴን አይቶ መቆም ማየት የሚችለው የለም አለው። የአንተ ወዳጅ መባሉ ለምንድ ነው "ድንረለ ትሬኢ ገጽየ" መስዋዕት ሆኜ በምቀርብበት ጊዜ እታይሃለሁ ብሎት ነበርና ቃል ኪዳኑን የማይረሳ አምላክነውና ተገለጠለት (ዘፃ 33+18)

ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እምሳለችን ደቀ መዛሙርቱን በፊልጶስ ቂሳሪያ፦ "ሰዎች ·የሰውን ልጅ ማን ይሉታል?" ብሎ ሲጠይቃቸው፦ "አንዱ መጥምቁ ዮሐንስ፣ ሌሎቹ ኤልያስ፣ ሌሎችም ኤርምያስ ወይም ከነቢያት አንዱ ነው ይሉሃል" ስላሉት በእርሱ እና በባሮቹ መካከል ያለውን ልዩነት እንዲመለከቱት ስለፈለገ የነቢያት አምላክ መሆኑን ለማሳየት ሙሴ እና ኤልያስ ከጌታ ጋር ሲነጋገሩ ታይተዋል። (ማቴ 16+13-14)

- አይሁድ ጌታን እንደ ሕግ ተላላፊ እና የእግዚአብሔርን ክብር ለራሱ የሚያደርግ ሰው አድርገው ይቆጥሩት ስለ ነበረ። (ዮሐ10+33)፤ እርሱ ሕግ ተላላፊ እንዳልሆነ ለማሳየት ሕግ ለሰጠው ለሙሴ ለእግዚአብሔር ክብር ቀናተኛ የነበረውን ኤልያስን አምጥቶ ሲያነጋግራቸው ታየ።
- ጌታ በሞትና በሕይወት ላይ ሥልጣን እንደለው ይታወቅ ዘንድ። ሞቶ ከተቀበረው ሙሴን ሞትንም ካልቀመሰው ኤልያስን አመጥቶ ሲያናጋግራቸው ታየ።
- ጌታችን ስለሚቀበለው መከራ ሲነገራቸው ለቀደመዛሙርቱ ጴጥሮስ "አይሁንብህ አይድረስብህ" ብሎት ስለ ነበረ የመስቀሉ ትርጉም ምን እንደሆነና ምን ክብር እንደሚያመጣ ሊያሳያቸው ስለ ፈለገ ጌትነቱንና ግርማ መንግሥቱን አሳያቸው።
- ሐዋርያት መከራንና ፈተናን ይለማመዱ ዘንድ ወደዚህ ተራራ አምጥቷቸዋል።

ማንም ክርስቶስን መከተል የሚፈልግ መስቀል ሊሸከም ይገባዋልና ደቀመዛሙርቱ እንደ ሙሴ ወደ ፈርዖን እንደ ኤልያስም ወደ አክዓብ ሳይሆን ወደ ዓለም ሁሉ እንደሚላኩ፤ ውጊያቸውም ከነገሥታት ጋር ሳይሆን ከክፉዎች መናፍስት ጋር እንደሆነ፤ አካሄዳቸውም ባሕርን

በጥሪቃ ሌሊት በሕልሟ እንቦሳ ከበረታቸው ስትወጣ አንቦ

ሳይቀ እንቦሳ እየወለደች እስከ ስድስት ስትደርስ ስድስተኛይቱ ጨረቃን ጨረቃ ፀሐይን ስትወልድ አይታ እንዲህ ያለ ህልም አየሁ አለችው ከመተርጎሙ ሕልም ሐላው ቢጠይቁ ደግ ልጅ ትወልጃለችሁ ጨረቃይቱን ከፍጡራን በላይ የምትሆን ልጅ ትወልዳላችሁ የፀሐይ ነገር ግን አልተገለፀልኝም እንደ ነቢይ፤ እንደ ካህን፤ እንደንጉሥም ያለ ይሆናል። እላቸው ጊዜ ይፍታው ብለው ሄደዋል በጥሪቃ ወለደች ስሟን ሪከቡ ሰዕለተየ ስትል ሄኤሜን አለቻት ሄኤሜን ዴርዴን ዴርዴን ቶናን ቶና ሲካርን ሲካር ሄርሜላን ሄርሜላ ሐናን ወለደች ሐናም ልጅ አጥታ ስታዝን ትኖር ነበር ከዕለታት አንድ ቀን ከዛፍ ጥላ ሥር እርፋ አእዋፋት ከልጆቻቸው ጋር ሲጫወቱ በምን ነገር ልጅ ከለከለከኝ ተፈጥሮ ከድንጋይ ነውን፤ ቁላ አዘሮች ከቤት ሲደርሱ ወንድ ልጅ ብንወልድ እንጨት ለትምህርት ተከለ ተከሉ ይርዳን አንልም ለቤተ እግዚአብሔር ምንጣፍ እንጥፍ መጋረጃ ሳፊ ይሆናል ሴትም ብንወልድ እንጨት ሰብራ ውኃ ቀድታ ትርዳን አንልም መሶብ ወርቅ ሰፍታ መጋረጃ ፈትላ ቤተ እግዚአብሔርን ታገለግላለች ብለው ተሳሉ አስቀድሞ በአምላክ ሕሊና ታስባ ትኖር የነበረች እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ነቢያት በብዙ ምሳሌ ትንቢት የተናገሩላት ቅዱስ ገብርኤል ከእግዚአብሔር ተልኮ ኢያቄምን ሚስትህ ሐና ትጸንሳለች ደግ ልጅም ትወልዳለች ብሎ አበሠረው ምንጣፍ ሰይተው ይኖሩ ነበር ፈታዱስ ከሆነ ብለው ከአንድ ምንጣፍ አድረዋል እመቤታችንም በዚህ ዕለት ተጸነሰች።

ትምህርት

- ከሴቶች መካከል ተለያታ የተባረከች እናታችን እንደሆነች (ሉቃ1+33 ገላ 4+2)

- የቤዛ እናት እንደሆነች (መዝ.131+13- ማቴ.1+18)
- የድኅታችን ምክንያት እንደሆነች እንማራለን።

መልዕክት

ሐናና ኢያቄም በንጽሕና በቅድስና እግዚአብሔርም በመፍራት፤በመታዘዝ ስለኖሩ እናታችንን ቅድስት ድንግል ማርያምን ወለዱ እኛም ያማከውን እንድናገኝ እግዚአብሔርን በመፍራት እንድንኖር ቸርነቱ አይለየን ።

የቅዳሴ ምንባብ

ዕብ.9+1

1ዮሐ. 2+6

የሐዋ.10+1

ምስባክ- ብፁዕ ብእሲ ዘአንተ ገሠጽኮ እግዚኦ

ወዘመሀርኮ ሕገከ

ከመ ይትገኃሥ እመዋዕለ እኩያት /መዝ 93፡12/

ወንጌል ማቴ 16፡13-24

ቅዳሴ /ዘእግዚእትነ/

ለመከፍል ሳይሆን ማያታትን ለማፈራረስ እንደ ሆነ ያውቁ ዘንድ ይዟቸው ወጥቷል ከሙሴና ከኤልያስ ጋር ሲነጋገር ታያቸው። በዚህ ለእኛ መሆን መልካም ነው።

ትምህርት

- የሙሴ ተስፋ የተፈጸመበት (ዘፀ 33÷19)
- የአብ ምስክርነት የተሰማበት "በእርሱ ደስ የሚለኝ የምወደው ይህ ነው እርሱን ስሙት (ማቴ5÷17)
- ምሥጢረ መስቀሉን የገለጠበት (ማቴ.17+2)
- የእኔነት ስሜትና ፍርሐት የተወገደበት ዕለት ነው። (ማቴ.7+4)

የቅዳሴ ምንባባት

ዕብ 11÷23
2ኛ ጴጥ.1÷15
የሐዋ.7÷44

ምስባክ፡- ታቦር ወአርሞንኤም በስመ፡ከ ይትፌሥሑ
ወይሴብሑ ለስምከ
መዝራዕትከ ምስለ ኃይል
(መዝ.88+12)

ወንጌል፡- ሉቃ. 9÷28

መልእክት

እኛ ከዚህ ምን እንማራለን? ክርስቶስን ማየት እንፈልጋለን? ደቀ መዛሙርቱ በዚሁ ቅዱስ ተራራ ሳሉ አብ በደመና ሆኖ ሲያነጋግራቸው ሰምተዋል። እኛ ግን አሁን ፈቃደኞች ከሆንን ከእለቱ መልእክት፤ ከሱራፌልና ከኪሩቤል ጋር ጌታ ዳግመኛ እየን

ለማዳን ሳይሆን በፍርድ ወንበር ተቀምጦ ወደ እኛ ሲመጣ በግልጥ እናየዋለን። ለተመረጡትም፡ "እናንተ የአባቴ ብሩካን ኑ ዓለም ከተፈጠረበት ጊዜ ጀምሮ የተዘጋጀላችሁን ውረሱ" (ማቴ 25+34) እኛም ከእግዚአብሔር ጋር ለመኖር በዚህ መሆን ለኛ መልካም ነውና አምላካችን እግዚአብሔር ይርዳን። አሜን

ነሐሴ ዐሥራ ስድስት
ፍልሰተ ሥጋሃ ለማርያም

የዕለቱ የትምህርት ርእስ

ተንሥእ እግዚኦ ውስተ ዕረፍትከ አንተ ወታቦተ መቅደስከ
"አቤቱ ወደ እረፍትህ ተነሥ አንተና የመቅደስህ ታቦት"
(መዝ.113+8)

እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ጥር 21 ቀን ዐርፋለች።
ቅዱሳን ሐዋርያት የእመቤታችንን የክብር ሥጋዋን ገንዘውና ከፍነው ለማሳረፍ ወደ ጌቴሴማኒ መካነ ዕረፍት (የመቃብር ቦታ) ይዘው ሲሄዱ አይሁድ በቅንአት መንፈስ ተነሣሥተው «ቀድሞ ልጇን በሦስተኛው ቀን ከሙታን ተነሣ፤ በዐርባኛው ቀን ወደ ሰማይ ዐረገ እንደዚሁም ተመልሶ ይሆን ዓለም ለማሳለፍ ይመጣል እያሉ ሲያውኩን ይኖራሉ። አሁን ደግሞ እርሷንም እንደ ልጇ ተነሣች፣ ዐረገች እያሉ ሊያውኩን ሊኖሩ አይደለምን?) ኑ ተሰብስበን ሥጋዋን በእሳት እናቃጥላት» ብለው ተማክረው መጡ።

ታውፋንያ የሚባል አይሁዳዊ የክብረ ሥጋዋን የተሸከሙበትን አልጋ (የአልጋ ሸንኮር) በድፍረት ያዙ፡ የእግዚአብሔር መልአክ በእሳት ሰይፍ

ሁለት እጆቹን ቆረጣቸው። እጆቹ ተንጠልጥለው ከቆዩ በኋላ በእውነት የአምላክ እናት ናት በማለት ስለ አመነ እጆቹ ተመልሰው እንደነበሩ ሆነውለታል። ከዚህ በኋላ መልአከ እግዚአብሔር የእመቤታችንን የከበረ ሥጋዋን ከሐዋርያው ዮሐንስ ጋር ነጥቆ ወስዶ በገነት ከዕፀ ሕይወት ሥር አስቀመጠው። ቅዱስ ዮሐንስም ከጥቂት ጊዜ በኋላ ወደ ሐዋርያት ተመልሶ ሲመጣ የእመቤታችንን የከበረ ሥጋ በገነት መኖሩን ነገራቸው። ዮሐንስ አይቶ እኛ እንዴት ሳናይ እንቀራለን ብንጠየቅስ ምን እንመልሳለን በማለት ነሐሴ አንድ ቀን ሱባኤ ጀምረው ሲጾሙና ሲጸልዩ ከሰነበቱ በኋላ በ14 (በሁለተኛው ሱባኤ መጨረሻ) ጌታችን የእመቤታችንን ትኩስ የከበረ ሥጋ አምጥቶ ስለሰጣቸው በታላቅ ዝማሬ፤ ወስደው ቀድሞ በተዘጋጀው መካነ ዕረፍት በጌቴ ሴማኒ ቀበሯት። የእመቤታችን የቀብር ሥነ ሥርዓት በተፈጸመ ጊዜ ከ12ቱ ሐዋርያት አንዱ የሆነው ቅዱስ ቶማስ አልነበረም። ከሀገረ ስብከቱ በደመና ተጭኖ ወደ ኢየሩሳሌም ሲመጣ፤ እመቤታችን በተቀበረች በሦስተኛው ቀን እንደ ልጇ ትንሣኤ ተነሥታ ስታርግ ያገኛታል። ቀድሞ የልጅሽን አሁን ደግሞ የአንቺን ትንሣኤ ሳላይ ቀረሁ ብሎ ቢያዝን እመቤታችን ከእርሱ በቀር ሌሎች ሐዋርያት ትንሣኤዋን እንዳላዩ ነግራው ቅዱስ ቶማስን አጽናናችው። ሄዶም ለሐዋርያት የሆነውን ሁሉ እንዲነግራቸው አዝዛው ለምልክት ይሆነው ዘንድ የተገነዘችበትን ሰበኗን ሰጥታው ወደ ሰማይ ዐርጋለች። ወደ ቀደመ ነገራችን እንመለስና ቅዱስ ቶማስም ሐዋርያት ወደ አሉበት ኢየሩሳሌም በደረሰ ጊዜ «የእመቤታችን ነገር እንዴት ሆነ?» ብሎ ቢጠይቃቸው፤ «እመቤታችንን እኮ ቀበርናት» ብለው ነገሩት። እርሱም ዐውቆ ምስጢሩን ደብቆ «አይደረግም ሞት በጥር በነሐሴ መቃብር እንደምን ይሆናል?» አላቸው። ቅዱስ ጴጥሮስ አንተ መጠራጠር ልማድህ ነው። ቀድሞ የጌታን ትንሣኤ ተጠራጥረህ አሁንም አታምንም ብሎ የእመቤታችን መካነ መቃብር ሊያሳዩት ይዘውት ሔዱ።

መቃብሩን ቢከፍቱ የእመቤታችንን የከበረ ሥጋ አጡት፤ ደነገጡም። በዚህ ጊዜ ቅዱስ ቶማስ «አታምኑኝም ብዬ ነው እንጂ እመቤታችንስ ተነሥታ ዐርጋለች» ብሎ የሆነውን ሁሉ ተረከላቸው። ከዚያም ምልክት እንዲሆን የሰጠችውን ሰበኗን አሳያቸው። እነርሱም ማረጓን አምነው ሰበኗን ለበረከት ከተከፋፈሉ በኋላ ወደየሀገረ ስብከታቸው ሄዱ። በየሀገረ ስብከታቸውም ሕሙማንን ሲፈውሱበትና ገቢረ ተአምር ሲያደርጉበት ኖረዋል።

በዓመቱ ትንሣኤሽን ቶማስ አይቶ እንዴት ይቅርብን ብለው ነሐሴ አንድ ቀን ጀምሮ ሱባኤ ገቡ። በሱባኤው መጨረሻ ነሐሴ 16 ቀን ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የስሙትን ልመና ተቀብሎ እመቤታችንን መንበር፣ ቅዱስ ጴጥሮስን ንፍቅ (ረዳት) ቀስ፣ ቅዱስ እስጢፋኖስን ገባሬ ሰናይ (ዋና) ዲያቆን አድርጎ ቀድሶ አቁርቧቸዋል። ከዚህ በኋላ እመቤታችንን ሐዋርያት በግልጽ ትንሣኤዋን ዕርገቷን እያዩዋት ከጌታችን ጋር በክብር በይባቤና በዝማሬ ወደ ሰማይ ዐርጋለች። ቅዱስ ያሬድ በመዝሙሩ «እመቤታችን ድንግል ማርያም ከምድር ወደ ሰማይ ዐረገች በሰማይም ከልጇ ጋር በክብር በመንግሥት ቅዱስ ቀኝ ተቀመጠች» ሲል ገልጿል።

ስለ ቅድስት ድንግል ማርያም ከመቃብር መነሣት ነሐሴ 16 ቀን የሚነበበው መጽሐፈ ስንክሳር እንደሚያስረዳን አባቷ ዳዊት በገናውን እየደረደረ ጸሐፊው የነበረው ዕዝራም መሰንቆውን ይዞ ቅዱሳን መላእክት ነቢያትና ጻድቃን እያመሰገኗት በብሩህ ደመና ወደ ሰማይ ዐረገች ከዚያም በክብር ተቀመጠች። በዚያም ስፍራ ሁለተኛ ሞት ወይም ሐዘን ጩኸትና ስቃይ የለም የቀደመው ሥርዐት አልፎአልና። (ራዕ 21፥4-5)።

በደብረሊባኖስም 12 ዓመት ኖረዋል። አቡነ ተክለሃይማኖት በ1267 ዓ.ም ደብረ ሊባኖስን በአት ሠርተው ኖሩ። ለ22 ዓመት ቆመው በመጸለይ የአንድ እግራቸው አገዳ ተሠብሮ ደቀ መዛሙርቶቻቸው በጨርቅ ጠቅልለው ቀበሩት። በአንድ እግራቸው ለ7 ዓመት በጸሎት ቆመው በጠቅላላው ለ29 ዓመት በጸሎት ከቆሙ በኋላ በ99 ዓመት ከ10 ወር ከ10 ቀን ነሐሴ 24 ቀን 1290 ዓ.ም አረፉ አባታችን ባረፉ 54 ዓመታቸው በ1354 ዓ.ም ለአባታችን ለአቡነ ሕዝቅያስ ተገልጸው አጽማቸው ከደብረ አስቦ ወደ ደብረ ሊባኖስ ግንቦት 12 ቀን እንዲፈልስ አድርገዋል።

ትምህርት

- በጾምና በጸሎት ተወስኖ እግዚአብሔርን እያመሰገኑ መኖር (ማቴ.21፥22)
- ከሚያልፈው ይልቅ የማያልፈውን መፈለግ (ማቴ.10፥37)

መልእክት

ጻድቁ አባታችን አቡነ ተክለሃይማኖት በዚህ ዓለም ከሚገኘው ደስታ ይልቅ ከእግዚአብሔር የሚገኘውን ዋጋ ለማግኘት እውነተኛ እና ታማኝ አገልጋይ በመሆን በዘመናቸው ሁሉ በጾምና በጸሎት ኖረው እውነተኛ የኢትዮጵያ ሐዋርያ በመሆን አገልግለዋል። እኛስ? ከጻድቁ አባታችን ምን እንማር በጾምና በጸሎት ወንጌልን በማስተማር የተጋን ወይስ ምንደኞች?... የጻድቁ አማላጅነት አይለየን አሜን !

የቅዳሴ ምንባብ
ሮሜ 8፥35
1ዮ 5፥1
የሐዋ 20፥28
ምስባክ ፦ እስመ በእንቲአከ ይቀትሉነ ኩሎ አሚረ
ወኮነ ከመ አባግዐ ዘይጠብሑ
ንቃህ እግዚኦ ለምንት ትነውም /መዝ 43፥22/
ወንጌል ማቴ 10፥16 ቅዳሴ/ግሩም/

ጳጉሜን ሦስት

ቅዱስ ሩፋኤል ጦቢት እና ጦቢያ የረዳበት ዕለት

የዕለቱ የትምህርቱ ርእስ
መልአኬን በፊትህ እልካለሁ
(ዘጸ 23፥20)

ቅዱስ ሩፋኤል የጦቢትን ዓይን ያበራና ወለተ ራጉኤልን ተቆራኝቷት ከነበረው ጋኔን ያላቀቃት መሆኑ በመጽሐፈ ጦቢት በስፋት ተገልጿል። ጦቢት በፋርስ ንጉሥ በስልምናሶር ዘመን የተማረከ ከነገደ ንፍታሌም የተወለደ ጽኑዕ እሥራኤላዊ ነው። እግዚአብሔር በስልምናሶር ፊት የመወደድን ግርማና ባለሟልነትን ስለ ሰጠው አለቃ አድርጎ ሾሞት ነበር። ለወገኖቹ ምጽዋት በመስጠት ሕገ ርትዕን በመሥራት የተጋ ሰው ነበር። ሐና የምትባል ሚስት አግብቶ አንድ ልጅ ወልዷል። ስልምናሶር ሞቶ ሰናክሬም በነገሠ ጊዜ ከሹመቱ ስለሻረው ደግሞ ወደ ምድያም መሔድ አልቻለም።

ሣራ ወለተ ራጉኤል ከፍተኛ ችግር ደርሶባት ነበር። ችግሯም ሕፃናት ወልዳ ቤት ንብረት ይዛ እኖራለሁ በማለት ባል አገባች ነገር ግን በዚች ሴት አስማንድዮስ የሚባል ጋኔን አድሮ ያገባችውን ሰው ገደለባት ሌላም ባል ብታገባ ሞተባት እንደዚሁ እየሆነ በጠቅላላ ሰባት ድረስ ያሉትን ባሎቿን ገደለባት።

የራጉኤል ልጅ ሣራ በዚህ ሁኔታ በኃዘን ተውጣ ስትኖር በነበረበት ጊዜ ጦቢት ሽምግሎ ስለ ነበር ልጁ ጦብያን አብሮት የሚሄደው ሰው ለመፈለግም ቢሄድ

ትምህርት

- የጾምና የጸሎት ውጤት ያማረ መሆኑን ማወቅ
- በአንድ ልብ ሆኖ እግዚአብሔርን መጠየቅ (የሐዋ2፥1)

መልእክት

ልበ አምላክ ቅዱስ ዳዊት የእመቤታችን ትንሣኤ አስቀድሞ በትንቢት መነፅርነት ታይቶት «ተንሥእ እግዚኦ ውስተ ዕረፍትከ አንተ ወታቦተ መቅደስከ፤ አቤቱ ወደ ዕረፍትህ ተነሥ አንተና የመቅደስህ ታቦት» (መዝ.131፥8)። ነቢዩ ዳዊት ይህን ቃል በትንቢት አስቀድሞ ክርስቶስ እንደሚነሣ ከዛሬ በኋላ ቀጥሎ የመቅደሱ ታቦት እናቱ ቅድስት ድንግል ማርያም እንደምትነሣ ይናገራል (ማቴ5፥35፣ ገላ. 4፥26፣ ዕብ 12፥22፣ ራዕ 3፥12)።

ኢትዮጵያዊው ሊቅ ቅዱስ ያሬድም በድርሰቱ ስለ ዕርገቷ ጽፏል። በቃሏ የታመነች በሥራዋም የተወደደች ቅድስት ድንግል ማርያምን መላእክት እያመሰገኗትና በመንፈሳዊ ደስታ እያጀቧት ወደ ሰማይ አሳረጓት ሲል በዘመረው ዝማሬ አስረድቶናል።

የእመቤታችን አማላጅነት የትንሣኤያችን በኩር የሆነው የአምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስ ቸርነቱ ከሁላችን ጋር ይሁን አሜን።

የቅዳሴ ምንባብ
ሮሜ 8፥31
1ዮ 2፥1ዮሐ 2፥1 እምነ ቀሲስ
የሐዋ 1፥12
ምስባክ፦ ቀደሰ ማኅደረ ልዑል

እግዚአብሔር ውስተ ማዕከላ ኢትትሀወክ

ወይረድኣ እግዚአብሔር ፍጽመ /መዝ 45፥4/

ወንጌል ማቴ 26፥26

ቅዳሴ /ዘእግዚእነ/

ነሐሴ ሃያ አራት

ዕረፍቱ ለተክለ ሃይማኖት

የዕለቱ የትምህርት ርእስ

የጻድቅ መታሰቢያ ለበረከት ነው (ምሳ 10፥7)

የአባታችን የአቡነ ተክለሃይማኖት አባት ቅዱስ ጸጋ ዘአብ እናታቸው እግዚእኃረያ ይባላሉ። የተወለዱት በሸዋ ቡልጋ ደብረ ጽላልሽ ነው። አባታቸው የቅዱስ ሚካኤል ቤተክርስቲያን አገልጋይ ካህን ነበሩ። መጋቢት 24 ቀን አባታችን ተክለሃይማኖት ተጸንሰው ታኅሣሥ 24 ቀን በ1190 ዓ.ም አባታችን ጻድቁ አቡነ ተክለሃይማኖት ከእናታቸው ከቅድስት እግዚእኃረያና ከአባታቸው ከቅዱስ ጸጋዘአብ ተወለዱ። በተወለዱ በ40ኛው ቀን ክርስትናን በመነሳት ፍሥሐ ጽዮን "የጽዮን ደስታ" ተብለው ተጠሩ። አባታችን 7 ዓመት እስኪሞላቸው ድረስ ከአባታቸው ከጸጋ ዘአብ ዘንድ እየተማሩ አደጉ። በ15 ዓመታቸው ዲቁናን ከቄርሎስ ዘንድ ተቀበሉ። በ22 ዓመታቸው ከአቡነ ቄርሎስ ዘንድ ቅስናን ተቀበሉ። በከተታ አውራጃ 3 ዓመት ወንጌልን እያስተማሩ ብዙ ድንቅ ነገርን አደረጉ። አባታችን በዳሞት ጸሎት ከነቢያት ምስጋና ሌሊቱን ሙሉ ይተጉ ነበር በያንዳንዱ መዝሙርም 10፣ 10 ስግደትን ይሰግዱ ነበር። በሐይቅ 10 ዓመት

አንድ መልካም ጉበዝ አገኘ ይኸውም መልአኩ ቅዱስ ሩፋኤል ነው።ጦብያ ግን መልአኩ ቅዱስ ሩፋኤል መሆኑን ፈጽሞ አላወቀም ነበር። ቅዱስ ሩፋኤል ‹መራኄ ፍኖት› /መንገድ መሪ/ ይባላል። እርሱ ሲሄዱ ውለው ማታ ጤግሮስ ከተባለው ታላቅ ወንዝ ደረሱና ከዚያም ለማደር ወሰኑ። በዚህ ጊዜ ከድካሙ ጽዕናት የተነሣ ጦብያ ሊታጠብ ወደ ወንዙ ወረደና ልብሱን አውልቆ መታጠብ ሲጀምር አንድ ዓሣ ሊውጠው ከባሕር ወጣ። ወዲያውም መልአኩ ቅዱስ ሩፋኤል ጦብያን ያዘው ፤ ዓሣውን እንዳትለቀው አለው ፤ ጦቢያም ከዓሣው ጋር ግብ ግብ ገጥሞ እየጎተተ ወደ የብስ አወጣው ከዚህ በኋላ ቅዱስ ሩፋኤል ጦብያን እንዲህ ሲል አዘዘው። ዓሣውን እረደው ጉበቱንና ሐሞቱን ተጠንቅቀህ ያዘው እንበላዋለን አለው።

ጦብያም መልአኩ እንዳዘዘው ዓሣውን አርዶ ሐሞቱንና ጉበቱን ያዘ ጦብያም መልአኩ እንዳዘዘው ዓሣውን አርዶ ሐሞቱንና ጉበቱን ያዘ። ጦብያም ያንን የዓሣውን ጉበትና ሐሞት ለምን እንደሚያገለግል ለመረዳት ‹ይህን ያዘው ያልከኝ ለምንድን ነው?› ሲል ጠየቀው ቅዱስ ሩፋኤልም ጋኔን ያደረበት ሰው ሲገኝ ይህንን ከዕጣን ጋር ቢያጤሱበት ጋኔኑ ይለቃል ሲል መለሰለት።

በዚህ ሁኔታ አንድ ባንድ ሲነጋገሩ ከቆዩ በኋላ መልአኩ ቅዱስ ሩፋኤል ጦብያን ‹ሣራ ከራጉኤል ቤት እናድራለን። እርሱ ዘመድህ ነው። የእርሱም ልጅ ሣራ

የምትባል ቆንጆ ልጅ አለችው። እሷን ለሚስትነት ይሰጥህ ዘንድ ለራጉኤል እነግርልሃለሁ› አለው።

ጦብያም ‹ያቺ ልጅ ከዚህ በፊት ሰባት ሰዎች እንዳገቧትና ሰባቱም ባገቧት ሌሊት ደርቀው /ሞተው/ እንደሚያድሩ ሰምቻለሁ። ስለዚህ እኔ ላባቴና ለእናቴ አንድ ልጅ ነኝ እርሷንም እንዳገባት ከዚህ በፊት እንዳገቧት ሰዎች እኔም የምሞት እንደሆን አባቴንና እናቴን የሚረዳቸው የለም ቢሞቱም የሚቀብራቸው አያገኙምና እፈራለሁ› አለው። መልአኩ ቅዱስ ሩፋኤል ግን ‹አባትህ ከዘመዶችህ ወገን ካልሆኑ በስተቀር ሌላ ሴት እንዳታገባ ሲል የነገረህን ረሳኸውን? በል ሰባት ባሎቿ መተውዳታል ስለምትለው እኔ መድኃኒቱን አሳይሃለሁ ፤ አይዞህ አትፍራ አትሞትም የዓሣውን ሐሞትና ጉበቱን ለምን መሰለህ ያዘው ያልኩህ ? እንግዲህ ሐሞቱንና ጉበቱን ከዕጣን ጋር ጨምረህ ስታጤስበት በሣራ አድሮ የነበረው አስማንድዮስ የተባለው ጋኔን ወጥቶ ይሄዳል ፈጽሞም ወደ እርሷ በገባህም ጊዜ ሁለታችሁ ይቅር ባይ ወደ ሆነው እግዚአብሔር ጸልዩ እርሷም የተዘጋጀች ናት። ከእኛ ጋርም ወደ ሀገርህ ይዘናት እንሄዳለን› አለው። ጦብያም ይህንን ቃል በሰማ ጊዜ ደስ አለውና ከእርሷ በስተቀር ሌላ እንዳያገባ በሙሉ አሳቡ ወሰነ።

ከዚህ በኋላ ወደ ራጉኤል ቤት እንደ ደረሱ ሣራ በደስታ ተቀበለቻቸው የሣራ አባትም ጦብያን ገና እንዳየው ሚስቱ አድናን ‹ይህ ልጅ የእኔ ዘመድ ጦቢትን ይመስላል› አለች ከዚያም ጋር አያይዞ ‹ልጆች ከየት ሀገር መጣችሁ?› አላቸው። እነሱም ‹ከነነዌ ሀገር ነው የመጣን› አሉት። ‹ከዚያም ሀገር ጦቢት የሚባል

ወንድም ነበርና ታውቀት ይሆንን ሲል ጠየቃቸው። በዚህ ጊዜ ጦቢያ አባቱን ሲጠራለት ሲያሰወቀዋለን። እኔም ራሴ የጦቢት ልጅ ነኝ አለው። ከዚያ በኋላ ራጉኤል ‹የወንድሜ ልጅ ነህን› ብሎ እቅፍ አድርጐ ሳመው። ጦቢያም ሣራን በዩ እንቱ ኑሮዋችን እንዲቃናልንና ጋብቻችን እንዲባረክልን አስቀድመን ወደ ፈጣሪያችን ጸሎት እናድርግ አላትና አብረው ጸሎት ካደረጉ በኋላ ያገን የያዘውንና የዓሣ ጉበትና ሐሞት ከዕጣን ጋር ጨምሮ ቢያጤስበት በሣራ አድሮ ባሎችዋን ይገድልባት የነበረው አስማንድዮስ የተባለው ጋኔን ከሣራ ለቆ ወጥቶ ሄደ ሁለተኛም ሊመለስ አልቻለም። እነርሱም በሰላምና በጤና አደሩ። የጦቢያንና የሣራን ጋብቻ የባረከ ቅዱስ ሩፋኤል ስለሆነ መልአከ ከብካቦ ይባላል።

የ14 ቀን በዓለ መርገ ከተፈጸመ በኋላ ግን ጥሬ ገንዘብና የከብት ስጦታ አድርጐ መርቆ ወደ ሀገሩ ሰደደው። ወላጆቹ ጦቢትና አድና ግን በመዘግየቱ ልጃችን ምን አገኘተ ይሆንን እያሉ በጊዜው ሳያዝኑ አልቀሩም። ከጥቂት ቀናት በኋላ ሚስቱንና ገመሎቹን ይዞ ሲመጣ በክብርና በደስታ ተቀበሉት። የጦቢያ አባት ጦቢትም ልጁህ መጣ ሲሉት ዓይነ ሥውር ስለ ነበር እርሱን እቀበላለሁ ሲል ሰለ ወደቀ ወዲያው ጦቢያ የዓሣውን ሐሞትና ጉበቱን ይዞ ስለ ነበር የአባቱን ዓይን ቀባው ወዲያውም ዓይኖቹ ተከፈቱ።

የቅዱሳንን ጸሎት ከሚያሳርጉ ከሰባቱ ሊቃነ መላእክት አንዱ እኔ ሩፋኤል ነኝ ሲል ገለጠላቸው። እነርሱም ወድቀው የአክብሮት ስግደት ሰገዱለት በመጨረሻም ከጦቢያ ጋር ሄዶ የነበረው መልአኩ ቅዱስ ሩፋኤልን የድካሙን

ዋጋ ገንዘብ ለመስጠት ጠሩት እርሱ ግን ጦቢትንና ጦቢያን ‹ፈጣሪያችሁን አመስግኑ እናንተ እስከ ዛሬ ድረስ ከየት እንደመጣሁ ማን እንደ ሆንኩ አላወቃችሁኝም። የእግዚአብሔር ምሥጢር ግን በክብር ሊገለጥ ይገባል እንጂ ሊሰውሩት ስለማይገባ የእኔን ተፈጥሮና ስም ልነግራችሁ እፈልጋለሁ ተፈጥሮዬ መልአክ ነኝ፣ ሥራዬም የቅዱሳንን ጸሎት ከሚያሳርጉ ከሰባቱ ሊቃነ መላእክት አንዱ እኔ ሩፋኤል ነኝ› ሲል ገለጠላቸው። እነርሱም ወድቀው የአክብሮት ስግደት ሰገዱለት። የአባቶቻቸውን አምላክ እግዚአብሔርንም አመሰገኑት። /መጽ. ጦቢት/።

ትምህርት

- እግዚአብሔር እንደሚጠብቀን ማወቅ
  ከእምነትህ የተነሣ ቆመሃል (ሮሜ.1+19)
- በወትር መልካም ሥራን መስራት (ሮሜ.12+13)
- በቅዱሳን መላእክት ተራዳኢነት ማመን
  አንዳንዶች ሳያውቁ መላእክትን እንግዶት ተቀብለዋልና። (ዕብ. 13.1-2)።

መልእክት

ጦቢት ከአሁኑ ከዓሣ ስተራብ የሚያበላ ከልብሱ ቀዶ ለተራቆተ ሰው የሚያለብስ እግዚአብሔርን ዘወትር የሚያመሰግን ለወገኖቹ የሚራራ አሥራት በኩራትን የሚያወጣ ሰው ነበር። በመሆኑም በሥራው ሁሉ እንዲረዳው በችግሩ ጊዜ እንዲያጸናው ቅዱስ ሩፋኤል ተልኮለታል። እኛም በሕይወታችን የጐደለብንን ነገር እንዲሞላልን መንገዳችንን እንዲያስተካክልልን ከክፉ ጋኔን እንዲጠብቀን አማላጅነቱ አይለየን። አሜን!

የቅዳሴ ምንባብ

ዕብ 7፡1

ይሁዳ 1፡11

የሐዋ 5፡17

ምስባክ ፡- እግዚአብሔርሰ ገሀደ ይመጽእ

ወአምላክነ ኢያረምም

እሳት ይነድድ ቅድሜሁ /መዝ 49፡2/

ወንጌል ማቴ 25፡31

‹‹ወንድሞቼ ሆይ ስለ እኛ ጸልዩ፡

ከወንድሞች ሁሉ ጋር በተቀደሰ አሳሳም ሰላምታ ተሰጣጡ፡

ይህ መልእክት ለቅዱሳን ወንድሞች ሁሉ እንዲነበብ በጌታ አምላችኋሁ::

የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋ ከእናንተ ጋር ይሁን::››

(1ኛ ተሰ 5+21-28)

ዋቢ መጻሕፍት

- ሉሌ መላኩ (ሊ/ፕሮፌሰር)፣ የኢ/ኦ/ተ/ቤ/ክ ታሪክ፣ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት አ/አ 1997 ዓ.ም።
- ጎሩይ አርምያስ (መምህር)፣ መዝገበ ታሪክ፣ ክፍል አንድና ሁለት እሌኒ ማተሚያ ቤት አ/አ 1995-97 ዓ.ም።
- አክሊለ ብርሃን ወ/ቂርቆስ መጽሐፈ አሜን፣ ትንሣኤ ማተሚያ ድርጅት አ/አ 1946 ዓ.ም።
- አባ ጎርጎርዮስ (ሊቀ ጳጳስ)፣የኢ/ኦ/ተ/ቤ/ታሪክ፣ ትንሣኤ ማተሚያ ድርጅት አ/አ 1991 ዓ.ም።
- አባ ጎርጎርዮስ (ሊቀ ጳጳስ)፣ የቤ/ክ/ታሪክ በዓለም መድረክ፣ ትንሣኤ ማተሚያ ድርጅት አ/አ 1978 ዓ.ም።
- ኪዳነ ወልድ ክፍሌ፣ መጽሐፈ ሰዋስው ወግስ ወመዝገበ ቃላት አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት ዓ.ም።
- የኢ/ኦ/ተ/ቤ/ክ አራቱ ወንጌላት ትርጓሜ፣ ትንሣኤ ማተሚያ ድርጅት አ/አ1988 ዓ.ም።
- የኢ/ኦ/ተ/ቤ/ክ የቅዱስ ጳውሎስ መልእክታት መጽሐፍ ንባብና ትርጓሜው፣ትንሣኤ ማተሚያ ድርጅትአ/አ1988 ዓ.ም።
- የኢ/ኦ/ተ/ቤ/ክ ቅዳሴ ማርያም አንድምታ፣ ትንሣኤ ማተሚያ ድርጅት አ/አ 1983 ዓ.ም።
- የኢ/ኦ/ተ/ቤ/ክ መዝሙረ ዳዊት፣ ንባቡና ትርጓሜ ትንሣኤ ማተሚያ ድርጅት አ/አ 1995 ዓ.ም።

- <u>የኢ/ኦ/ተ/ቤ/ክ ውሳኔ ማርያም አንድምታ</u>፣ ትንሣኤ ማተሚያ ድርጅት አ/አ 1983 ዓ.ም።
- <u>የኢ/ኦ/ተ/ቤ/ክ ስንክሳር</u>፣ ከመስከረም-ጳጉሜ፣ ትንሣኤ ማተሚያ ድርጅት አ/አ፣ 1993/94 ዓ.ም።
- <u>የኢ/ኦ/ተ/ቤ/ክ ገብረ ሕማማት</u>፣ ትንሣኤ ማተሚያ ድርጅት አ/አ 1996 ዓ.ም።
- <u>የኢ/ኦ/ተ/ቤ/ክ መጽሐፈ ግጽዋ</u>፣ ትንሣኤ ማተሚያ ድርጅት አ/አ 1990 ዓ.ም።
- <u>የኢ/ኦ/ተ/ቤ/ክ ትንቢተ ሕዝቅኤል ትርጓሜ</u>፣ ትንሣኤ ማተሚያ ድርጅት አ/አ 1988 ዓ.ም።
- የኢትዮጵያ መጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር፣ <u>መጽሐፍ ቅዱስ</u>፣ 1980 ዓ.ም።
- የኢትዮጵያ መጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር፣ <u>የመጽሐፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላት</u>፣ 1999 ዓ.ም።

ከዚህ በፊት በአዘጋጁ የተዘጋጁ

- በማዕበል ውስጥ ያለ ፀጥታ (ስብከት በቪሲዲ)
- የሰማችሁት ቃል ትዝ ይበላችሁ (ስብከት በሲዲና በካሴት)
- ከአንቺ አልለይም (ስብከት በቪሲዲ)
- የሞዓብ ሽከም ከፍል አንድ (መጽሐፍ)



መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔር ቃል ነው። ስብከት ደግሞ እኛ ከእግዚአብሔር ቃል የምናዘጋጀው ነው። ስብከታችን በሕያው እግዚአብሔር ተቆጣጣሪነት ሕያው የሆነውን የእግዚአብሔር ቃል በአድማጮች ውስጥ ሕይወትን ወደ ሚያቀርብና ለድኅነት ያዘጋጃል። ስብከት ይለውጣል፣ ስብከታችን ውበት ካለውና ደስታ ከሚሰጥ ነገር ይበልጣል። የዘለዓለማዊ ሕይወት ጉዳይ ነውና። በመሆኑም ዕለት በዕለት የእግዚአብሔርን ቃል መስበክ ያቆመ ሰባኪ እየከሣ መሄድ ብቻ ሳይሆን የራሱን ነፍስ ማስራብ እንዲሁም የክርስቶስን መንጋ ለመመገብ ያለውን ብቃት እያጣ ነው። ስለዚህ ደቀመዝሙር ዲ/ን አዲሱ ላቀው ለዘመኑ ትውልድ የሚበጅ መጽሐፍ በመጻፉ ሊበረታታ ይገባዋል። ቀጣዩንም እንጠብቃለን። በርታ እግዚአብሔር ይባርክህ!

አባ ኃይለማርያም መለሰ (ዶ/ር)
በ/ኢ/ኦ/ተ/ቤ/ክ የስብከተ ወንጌልና
ሐዋርያዊ ተልዕኮ መምሪያ ኃላፊ

ቤተክርስቲያናችን ከዓመት እስከ ዓመት የምታከብራቸውን በዓላት፣ በቀናትና፣ በወቅቶች የሚገለጹ ሆነው ምእመናን ሃይማኖታዊ ፍቅራቸውን የሚገልጹባቸው ናቸው። ቀናት ለሰው ልጆች ጥቅም ብሎ እግዚአብሔር ራሱ የሠራው ሥርዓት ሆኖ ድንቅ ሥራዎችን ለሕዝቡ የገለፀባቸው ናቸው። እኛ ሰዎች በነዚህ ቀናት እግዚአብሔር ለእኛ ለሰው ልጆች የሰጠንን በዓላት አስታውሰን የምናልፍበት ብቻ ሳይሆን እግዚአብሔር ለዓለም ሕዝብ የሰጠውን የተትረፈረፈ በረከት እና ቸርነት፣ እርቅንና ሰላም እንዲሁም ምሕረትን የምናገኝበት ነው። በመሆኑም ምእመናን በሙሉ ይህ ‹‹ፍናተ ስብከት በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ከአመት እስከ ዓመት›› በሚከበሩ በዓላት ታሪክ ላይ የተመሠረተ ትምህርታዊ ስብከት በሚል ርእስ በወንድማችን በደቀ መዝሙር ዲ/ን አዲሱ ላቀው የተዘጋጀው መጽሐፍ ከመጀመሪያው እስከ መጨረሻው በማንበብ ተጠቃሚዎች እንድንሆን ስል በዚህ አጋጣሚ ለመግለጽ እወዳለሁ።

መ/ር ፍሥሐጽዮን ደመወዝ(M TH)
በቅ/ሥላሴ ዩኒቨርሲቲ መንፈሳዊ ኮሌጅ
የአካዳሚክ ም/ዲን

ሕፃን ተወልዶ ያድጋል፣ ይመነደጋል፣ከወተት መጋት ወደ ጠንካራው ምግብ ዳቦ ወደ መጮርደም፣ ጥሬ ወደ መቆርጠም ይደርሳል። እንዲሁም ዲ/ን አዲሱ ላቀው በትምህርተ ወንጌል ተወልደህ፣ በተዋሕዶዋ ቤተክርስቲያን በሥርዓት አድገህ ጎሊበ ምሥጢርን ተግተህ እነሆ ዛሬ ከዓመት እስከ ዓመት በሰባክያን አንደበት መሶበ ወርቅ እየቀረበ ምእመናንን ከርሃበ ነፍስ የሚጠግቡትን እንከን የለሽ ምግበ እእምሮ መጽሐፍ አቀረብክልን።
‹‹ስብሐት ለአብ ብያለሁ።›› ይደልዎሙ ለአብ፣ ወወልድ፣ወመንፈስ ቅዱስ በሉ።
እግዚአብሔር ይስጥልን ከብሉይ ከሐዲስ ባሕር ቀድተህ፣ ከውቅያኖስ ምሥጢር ጨልፈህ አስጎነጨኸን፣ በጠለ ምሥጢር ረጨኸን፣ መንገዱ ለጠፋባቸው፣ ቀኑ ላልተገለጠላቸው፣ ሁኔታው ድንግዝግዝ ላለባቸው እነሆ የዕለቱ መንገድ በዲ/ን አዲሱ ላቀው ተዘጋጀ።

መ/ር ደጉ ዓለም ካሣ
በቅ/ሥላሴ ዩኒቨርሲቲ መንፈሳዊ ኮሌጅ
የአዲስ ኪዳን መምህር

አሌኒ ማ.ቤ.ኃ.የተ.የግ.ማ. ዋጋ 25.00 ብር